ዕዝራ
ስነ ጽሑፍ
አገልግሎት

የዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት ግቡና ዓላማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትና ይዘት ያላቸውን ቅዱሳንን የሚመግቡና ከስሕተት ትምህርቶችና ልምምዶች የሚያስጠነቅቁ ከአጫጭር መጣጥፎች እስከ ትልልቅ የማስተማሪያ መርጃዎች በማዘጋጀት ቤተ ክርስቲያንን መደገፍና በዚህም እግዚአብሔርን ማክበር ነው።

ቁጥር ፷፱
መጋቢት ፱ሺህ ፯ ዓመተ ምሕረት
APRIL 2015

ብዙ ሰላም ይህን ለምታነብቡ ሁሉ ይሁን።

አጨብጫቢ በሚል ርእስ ስር የተጻፈው መጣጥፍ ለምንሰማቸው ነገሮች ሁሉ አድናቂና አጨብጫቢ መሆን ወደ ስሕተት የሚመራ ብቻ ሳይሆን የስሕተተኞችን ስሕተትን የሚያበረታታ መሆኑን የሚያሳስብ ነው። ራእ. 13፥3 ምድርም ሁሉ ለአውሬውን እየተከተለ ተደነቀ ይላል። የምናየውንና የምንሰማውን ሁሉ ጉድ እያልን የምንቀበል፥ የምንደነቅና የምናደንቅ ከሆነ ፍጻሜያችንን አያምርም። እንደ ቤርያ ሰዎች መርማሪዎች እንሁን።

እስላምና እና ክርስትና ከዚህ በፊት የተጀመረው የክርስትና እና መጽሐፍ ቅዱስ ነቀፌታና ማንቋሸሻ የሆነው የዶ/ር ዓሊ አልኹሊ መጽሐፍ ምላሽ ነው። ይህ ክፍል ሰባት ነው።

ዛሬ በኢስላምና በቁርኣን ስሕተቶች ላይ መናገር ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱስ ሲንቋሸሽም ለመጽሐፍ ቅዱስ እውነት መቆም የሚያስቆጣና የሚያስፈራ እየሆነ ስለመጣ አካዳሚያዊው ዓለምና ሚዲያው እያፈገፈጉ ያሉ ይመስላል። ይህ ኃላፊነት ወደደችም ጠላችም በቤተ ክርስቲያን ትከሻ ላይ ብቻ ቀርቶአል። በዚህ ጉዳይ ላይ ቤተ ክርስቲያን የምትወስደው የዝምታ ወይም የመግለጥ ኃላፊነት የራሷን ጎልውናም የሚሞግት መሆኑን እያጤንን እናስተውል፤ እያስተዋልንም እናንብብ፤ እያነበብንም ይበልጥ እንመርምር፤ እየመረመርንም እውነትን እንግለጥ፤ እውነትን እየገለጥን ስፍራችንን እንጠብቅ። የጌታ ቃል ቆሻሻ ሲጣልበትና ጢቅ ሲባልበት ዝም አንበል።

እንመላለስ ወደ ፊልጵስዩስ የተላከችውን የጳውሎስን መልእክት ማጥናት የምንቀጥልበት ነው። በዚህም ከምዕ. 3 ሁለት ጥቅሶችን እናጠናለን።

እነዚህንም ሆነ ማናቸውንም በዕዝራ ላይ የምጽፋቸውን ጽሑፎች ባለቤትነቱን ሳትወስዱ በነፃ ማባዛትም ሆነ ማደል ትችላላችሁ። ባለቤትነቱን ሳትወስዱ ያልኩት ለጽሑፎቹ ተጠያቂና ተወቃሽ እንዳትሆኑ ነው።

ጌታ ጸጋውን ሰላሙንም ያብዛላችሁ።

ዘላለም መንግሥቱ / ዕዝራ ስነ ጽሑፍ

ezralit@gmail.com



© 2015

አንሞጾስ

እንግዲህ ፍጹማን የሆንን ሁላችን ይህን እናስብ፤ በአንዳች ነገርም ልዩ አሳብ ቢኖራችሁ፥ እግዚአብሔር ይህን ደግሞ ይገልጥላችኋል፤ ሆኖም በደረስንበት በዚያ እንመላለስ። ፊል. 3፥15-16

ባለፈው የፊልጵስዩስ ጥናታችንን የጨረስነው ሩጫን በትእግሥት ስለመጨረስ በመናገር ነበር። ምልክትን እፈጥናለሁ ሲል ወደሚታየው የግብ ምልክት ወደ σκοπός እስኮፖስ እፈጥናለሁ ማለቱን፤ ይህም 'ከፍ ከፍ ያለውን . . . ምልክትን እፈጥናለሁ' የሚለው ሐረግ አገላለጡ ክርስቶስ ወደ ጠራኝ፥ በላይ ወዳለው የሽልማቴ ስፍራ፥ ወደ ምልክቴ፥ ወደ ግቤ፥ የሩጫዬ መደምደሚያ ወደሆነው ስፍራ እገሰግሳለሁ ማለቱ ነው። ሯጮች ሩጫቸውን የሚጨርሱበት ስፍራ ምልክት አለው፤ ሲጨርሱ የሚበጥሱት ክር ወይ ቀጭን ጨርቅ (ሪበን) ይኖራል። ጳውሎስ ምልክትን የፈጠነው ወይም ወደ ምልክቱ የፈጠነው ይህንን የመጨረስ ምልክት ነው ብለን ነበር።

ሩጫ ሕጋዊ በሆነ ወይም ደንብ በተደነገገለት ሁኔታ ነው መርሮጥ ያለበት። ሩጫን በተመለከተ አጭበርብረውና በአቋራጭ ሊያሸንፉ የጣሩ ብዙ ሰዎች ታሪኮችን ከሩጫው ዓለም እናገኛለን። አንዳንዶቹ አስቂኞች፥ አንዳንዶቹ አሳዛኞች፥ ሌሎቹ አናዳጆች ናቸው። ከመጀመሪያዎቹ (ከ20ኛው መቶ መግቢያ) አሊምፒክ ሯጮች አንድ ሁለት ልጥቀስ፤



በፈረንጆች 1904 (ገና ምኒልክ ሳይሞቱ) የማራቶን ውድድር በአሜሪካ በሴይንት ሉዊስ ከተማ ነበር የተደረገው። የቀኑ ትኩሳት ከባድ ነበር፤ መሮጫው ዳገታማ ነበር፤ የውድድር ተቆጣጣሪዎቹ መኪናዎች አቧራ እያለበሷቸው ነበር የሚያልፉት። ከ32ቱ ሯጮች የጨረሱት 15ቱ ብቻ ነበሩ። አሜሪካዊው ፍሬድ ሎርዝ - Fred Lorz (ቁጥር 31 የለበሰው) ሲመራ ከቆየ በኋላ 9 ማይል ላይ ወደቀ፤ አልቻለም። ሌላው አሜሪካዊ ቶማስ ሂክስ - Thomas Hicks መምራት ጀመረ። እርሱም አልቻለምና ወደቀ፤ አሰልጣኞቹ በጥሬ ዕንቁላል መትተው ከብራንዲ ጋር አጠጥተውን እስትሪክናይን የተባለ መድኃኒት አስውጠውት ተመልሶ እንዲሮጥ አደረጉት። (ዛሬ ቢሆን በወንጀለኝነት ተከስሰው ይቅቀጡ ነበር።) እንደምንም ተነሥቶ መሮጥ ጀመረ ግን አጉል ሆኖበት ነበር። ኋላ ሎርዝ ተነሥቶ እየሮጠና እየመራ መሆኑን ነገሩት። ምን ነበር የሆነው፤ ሎርዝ መሮጥ አቅቶት በመኪና ይዘውት መመለስ ይጀምራሉ፤ እመንገድ ላይ መኪናዋ ትሰበርና ተነሥቶ በእግሩ እየሮጠ ሄዶ ከሂክስ 15 ደቂቃ በመቅደም ወደ ሜዳው አንደኛ ሆኖ ይገባል፤ ግማሽ በመኪና ግማሽ በሩጫ። የወርቅ ተሸላሚ ሊሆን ከቀረበ በኋላ በመኪና ሲሄድ ያዩት ይመሰክሩና ከሽልማት ውጪ ተደረገ።

ከአራት ዓመታት በኋላ ደግሞ (በ1908) ለንደን፥ እንግሊዝ በተደረገው። በማራቶን አንደኛ የሆነው የጣሊያኑ ዶራንዶ ፒዬትሪ - Dorando Pietri ነበር።



ያ ዓመት ማራቶን 25 ማይል መሆኑ ቀርቶ 26 ማይል ተኩል የተደረገበት ነበር። ዶራንዶ አንደኛ ቢሆንም ወደ መጨረሻው ላይ እየወደቀ እየተነሣ፥ እየተዝለፈለፈ የጨረሰው። ብዙ ሳይቆይ አሜሪካዊው ጆኒ ሄይስ - Johnny Hayes ከዶራንዶ በኋላ ገባና ጨረሰ። ጆኒ ሲገባ ቀድሞውኑ አንደኛ ለገባው ለዶራንዶ የጣሊያን ባንዲራ እየተውለበለበ ነበር። ወዲያው በአሜሪካ ስሞታ አቅራቢነት የዶራንዶ አሸናፊነት ተሰርዞ ጆኒ አሸናፊ ተደረገ፤ ሲጨርስ እየተዝለፈለፈ ሳለ ሰዎች ደጋግፈውት ነበር የጨረሰውና ውድቅ ተደረገ። ሕገ ወጥ እርዳታ ዶራንዶን የወርቅ ሜዳይ አሳጣው፤ ለማስተዛዘኛና ለስፖርተኛነቱ ሞራል ሲባል ግን የእንግሊዟ ንግሥት አሌክሳንድራ ዋንጫ ሸልማዋለች።

የሩጫ ምሳሌ ይበቃናል፤ ወደ መመላለስ እንለፍ። የክርስትና ጉዞ በሩጫ እንደተመሰለ በመመላለስም ተመስሎአል። ደቀ መዛሙርት ክርስቲያን የተባሉት በአንጾኪያ ነበር። ክርስቲያኖች ክርስቲያን ከመባላቸው በፊት የሚታወቁት የመንገዱ ሰዎች ተብለው ነበር። ክርስትና መንገድ፥ ደቀ መዛሙርትም የመንገዱ ሰዎች ይባሉ ነበር። በሐዋርያት ሥራ ይህ በግልጽ አልተጻፈም፤ ግን 'መንገድ' ወይም 'መንገዱ' የሚለውን አሳብ ከሐዋ. 9፥2፤ 19፥9 እና 23፤ 22፥4፤ 24፥14 እና 22 ውስጥ ተመልከቱ። ደቀ መዝሙር ማለት ተከታይ ተማሪ ማለት ነው። የሚከተልም መሪው በሚሄድበት መንገድ የሚገኝና የሚሄድ መንገደኛ ነው። የመንገዱ ሰዎች የተባሉት ለዚህና ጌታ መንገዱ እርሱ መሆኑን ከተናገረው ትምህርት የተነሣ ነው። ክርስቲያኖችን ክርስቲያን ብለው የሰየሙትና ለራሳቸው ስም ያወጡት ራሳቸው ክርስቲያኖቹ አይደሉም፤ ሐዋ. 11፥26። ይህ መጠሪያ የተሰጣቸው በሌሎች ነው። ትርጉሙ የክርስቶስ የሆኑ፥ የክርስቶስ ተከታዮች ወይም ደቀ መዛሙርት ማለት ነው።

ልብ እንበል፤ ይህ ጥቅስ፥ *ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ* ነው የሚለው። ክርስቲያን ከመባላቸው በፊት ደቀ መዛሙርት ናቸው። ይህ እንደ ትልቅ ሽክም የከበደ እውነት ነው። ማንም ክርስቲያን ራሱን ክርስቲያን ካለ ወይም ክርስቲያን ተብሎ በሌሎች ከተጠራ ደቀ መዝሙር መሆኑ እርግጥ መሆን አለበት። ደቀ መዝሙር ያልሆነ ክርስቲያን ክርስቲያን ተብሎ ሊጠራ የተገባው አይደለም። መጀመሪያ ደቀ መዝሙር ሆኖ ከዚያ ነው ክርስቲያን መኾን ያለበት ማለት ሳይሆን ክርስቲያን ሁሉ ደቀ መዝሙር ለመሆኑ እርግጠኛ መሆን አለበት ማለት ግን ነው። ይህንን፥ 'ደቀ መዝሙር' የሚለውን ቃል በአማርኛ ለምን 'ደቀ መዝሙር' ብለው እንደተረጎሙት አላውቅም። እኔ እንደተረዳሁት የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ በተተረጎመባቸው ከ19ኛው ኢጋማሽ እስከ 20ኛው ኢጋማሽ ባሉት ዘመናት ደቀ መዝሙር የሚለው ቃል ተማሪን ስለሚወክል ይሆናል ደቀ መዝሙር ያሉት። ከ1879ኙ ትርጉም እስከ ሕያው ቃልና እስከ መደበኛ ትርጉምም ይህን ቃል እንዳለ ወስደውታል። የተለመደና የተወደደም ቃል ነው። ትርጉሙ ግን መታወቅ አለበት። ደቀ መዝሙር በቀጥታ ሲተረጎም የመዝሙር፥ ማለትም፥

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2015

የመዝሙረ ዳዊት ተማሪ ማለት ነው። በደስታ ተክለ ወልድ መዝገበ ቃላት፥ ዳዊት የሚማር ልጅ፥ የዳዊት ተማሪ ተብሎአል። ደግሞም የዳዊት ተማሮች፥ ሐዋርያት፥ አርድእት ብለውታል።[1] የዘመኑ ትምህርት ሃይማኖታዊ ሆኖ ተማሪ ሁሉ በዳዊት ስለሚጀምር ይሆናል ተማሪ ሁሉ 'ደቀ መዝሙር' የመዝሙር ልጅ፥ መዝሙር የሚማር ልጅ፥ የዳዊት ተማሪ የተባለው። ከጠቅላላ ትርጉሙ ስንነሳዘበው መዝሙር ወይም መዝሙረ ዳዊት ይጨመርበት እንጂ ተማሪ ማለት ነው። ይህ ተማሪ የሚለው ቃል ነው መሰመር ያለበት።

ደቀ መዝሙር (μαθητής ማቴቴስ) የሚለው ቃል ቀጥተኛ ትርጉሙ ተማሪ፤ ጠለቅ ካልን ደግሞ ተከታይ ተማሪ ማለት ነው። ደቀ መዝሙር ተከታይ ተማሪ ማለት ነው። በጌታ ዘመን ተማሪዎች እንደ ዛሬው ያሉ ተማሪዎች ናቸው። በተለይ ከአይሁድ ስደት ወይም ብታኔ ዘመን በኋላ የአይሁድ መሠረተ ትምህርትን በምኩራብ የሚማሩ ልጆች ቢኖሩም በመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ μαθητής (ማቴቴስ) መሪውን የሚከተል ተማሪ አብሮት የሚገባ፥ የሚወጣ፥ የሚሄድ፥ የሚመጣ ተከታይ ማለት ነው። ተጓዥ ተማሪ ማለት ነው። ይህ የሆነው መሪው ወይም ጌታው (ረቢው) ቋሚ ትምህርት ቤት ስለሌለው ነው። እነዚህ ተማሪዎች መሪያቸውን የሚከተሉ ተከታዮች፥ አብረውት የሚጓዙ ተጓዥ ተማሪዎች ናቸው።

ስለዚህ ነው በደቀ መዝሙር ትርጉም መከተልና መምማር የተቆራኙት። ደቀ መዝሙር ተከታይ ተማሪ ነው። ተከታይም፥ ተማሪም። የጌታን ደቀ መዛሙርት፥ በተለይም ሐዋርያቱን ስንመለከት ይህንን የተከታይ ተማሪነት ሕይወት እናስተውላለን። ይሰሙት፥ ከእርሱ ይማሩ፥ አብረውት ይኖሩ፥ አብረውት ይወጡ ይገቡ ነበር። ይህ አሳብ ነው ደቀ መዛሙርትን የመንገዱ ሰዎች ያሰኛቸው። ደግሞም ጌታ እርሱ ራሱ መንገድ መሆኑን አስተምሮ የል? ዮሐ. 14፥1-6። ደቀ መዝሙር በዚህ መንገድ፥ በክርስቶስ ትምህርት የሚመላለስ ሰው ነው ማለት ነው። ስለዚህ ክርስትና መመላለስ ነው። በዚህ መንገድ ላይ መጓዝ ነው።

ባለፈው የፊልጵስዩስ ጥናት እንዳየነው ጳውሎስ የሩጫን ምስል በመጠቀም የክርስትናን ጉዞ ያስረዳል። ሩጫ ጥሩ ምስል ነው። ሆኖም፥ ክርስትና እንደ ሙቶ ሜትር ሩጫ ተስፈንጥረው፥ ወይም እንደ ሺህ ሜትር ሩጫ ተምዘግዝገው የሚጨርሱት ብቻ፥ ወይም እንደ ማራቶን 42 ኪሎ ሜትር ያህል ርዝመት ሮጠው የሚቆሙት ሩጫ ብቻ ሳይሆን በመንገዱ በክርስቶስ የሚመላለሱት መመላለስ ነው።

እንግዲህ ፍጹማን የሆንን ሁላችን ይህን እናስብ፤ በአንዳች ነገርም ልዩ አሳብ ቢኖራችሁ፥ እግዚአብሔር ይህን ደግሞ ይገልጥላችኋል፤ ሆኖም በደረስንበት በዚያ እንመላለስ። ፊል. 3፥15-16

ጳውሎስ ፍጹማን ሲል እንከን የለሽ ሁኔታን መናገሩ ሳይሆን መብሰልንና በጌታ ማደግን መናገሩ ነው። ፍጹም አለመሆኑንማ ቀደም ሲል ባየነው ከፍል በቁጥር 12 ላይ *አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደ ሆንሁ አይደለም፥ ነገር ግን ሰለ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግም እይዘለሁ ብዬ እፈጥናለሁ።* ብሎአል። ጌታን የምንመስለው እዚህና አሁንም ጀምሮ ሲሆን ፍጹም የምንሆነው ግን ወደ ጌታ ስንሰበሰብ ብቻ ነው። ስለዚህ ፍጹማን የሆንን ሲል መብሰልን፥ ሙሉ ሰውነትን መናገሩ ነው።

ይህን እናስብ ሲል ይህ ከላይ ባሉት ጥቅሶች የተናገራቸው የመቁጠርና የመምሰል ጉዳይ አመለካከታችንና አስተሳሰባችን ይሁን ማለቱ ነው። *በአንዳች ነገርም ልዩ አሳብ ቢኖራችሁ፥ እግዚአብሔር ይህን ደግም ይገልጥላችኋል፤* በጌታ መብሰል የአሳብ ልዩነት ወይም ልዩ አሳብ እንዳይኖረን አያደርገንም። ሆኖም፥ በአሳብ መለያየት በዓላማ መለያየትን መፍጠር የለበትም።

ስለዚህ አሳብ ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች ደጋግሞ ጽፎአል። በ1፥18 የሰዎቹ አሳብ የተለያየ ቢሆንም ወንጌል መሰበኩን እንደ ግብ አድርጎ ተደስቶበታል። በአሳብ መስማማት መልካም ነው። በፊል. 2፥2 እና 5 ጳውሎስ የክርስቶስን አሳብ የማሰብ ተገቢነት ጽፎታል። በ4፥2 በአሳብ የተለያዩ ሁለት ሴቶችን ስም በመጥቀስ እንዲስማሙ መክሮአል። በአሳብ መስማማት መልካም ነው። በክርስቶስ የነበረ አሳብ በኛም ከኖረ ይህን በአሳብ መስማማት የሚባለውን ነገር ልንቀዳጅ ይቻለናል። በአሳብ ካልተስማማን ግን በዓላማ እንስማማ። በሐዋ. 15፥39 በበርናባስና በጳውሎስ መካከል መከፋፋት እስኪሆን የአሳብ ግጭት መፈጠሩ ተጽፎአል። ይህ መከፋፋት የልብ ጥላቻ ሳይሆን ድንገተኛ ግጭት ሆኖ አቋምን ሳይለቅቁ፥ ፍንክች ሳይሉ መከራከርን የሚያሳይ ቃል ነው። ጳውሎስ ከሲላስ ጋር ወንጌልን እየሰበከ ነው የሄደው። በግልጽ ባይጻፍልንም በርናባስም ከማርቆስ ጋር ወንጌልን እየሰበከና ለመስበክ ወደ ቆጵሮስ እንደሄደ መረዳት እንችላለን። በዓላማ ተለያይቶ በአሳብ መስማማት አይቻልም፤ አሳብ ልዩ ልዩ ሆኖ ግን ዓላማ አንድ ሊሆን ይችላል። በማርቆስ ሳቢያ ቢለያዩም ወንጌልን እያገለገሉ ነበር የሄዱት።

በደረሱበት መመላለስ ሌላ የሚያሳስበው እውነት አለ፤ ያም ማደግንና ባደጉበት መቆየትን ነው። አንዳንድ ጊዜ ያደጉ ሰዎች እንዳላደጉ ሊሆኑ ይችላሉ። ካደጉና ከበሰሉ በኋላ በተለያዩ አካላዊ፥ ስነ ልቡናዊ፥ ከባቢያዊ፥ ኬሚካላዊ እና የሕመም ወይም የሕክምና ምክንያቶች የተነሣ የአንጎል ሴሎቻቸውን ሊያጡ ይችላሉ። ስለዚህ ከነበራቸው የማሰብና አእምሮን የመጠቀም ችሎታ የወረዱ ይሆናሉ። ይህንን ችሎታ አንዳንዶች በጥቂት፥ አንዳንዶች በብዙ ሊያጡ ይችላሉ። በመንፈሳዊ ዕድገት እንዲህ ያለ ነገር ላይመዘገብ ይችላል። ይሁን እንጂ ግን አንዳንድ ክርስቲያኖች ሊያድጉ የተገባቸውን ያህል ሳያድጉ ይቀራሉ። አንዳንዶች ባሉበት ቆመው ይቀራሉ። አንዳንዶች ከነበሩበት ተንሸራትተው ሊወርዱም ይችላሉ። ይህ ያሳዝናል።

በደረሱበት መመላለስ አለማፈግፈግ ነው። አለመንሸራተት፥ ስፍራን አለመልቀቅ ነው። በ2011 ወጣቶችን ለማስተማር በሰነበትኩበት አንድ የበጋ ካምፕ ከነበሩት የተለያዩ መርሐ ግብሮች የአንዱ ቀን ቀጥ ያለ የዓለት ቋጥኝ እየቧጠጡ መውጣት ነው። በጣም እፈራው የነበረ፤ ግን የወደድኩት እስፖርት ነው። ብንንሸራተት ወድቀን እንዳንፈጠፈጥ ከታፋችን እስከ ወገባችን የታሰርንበት ቀበቶና ገመድ አለ። ያ ገመድ ከላይ የታሰረበት የተቸከለ ችካል እና ከታች ደግሞ አብረን የታሰርንበት ቢያንስ የኛን ክብደት የሚያህል መዛኝ ሰው አለ። ብዙዎቻችን ጨርሰን እስከ አናቱ ወጥተን ነበር፤ እኔም ጭምር፤ ለመጀመሪያና ለመጨረሻ ጊዜ! ደስ ይላል ጫፍ ሲደረስ። ያን ቀን ጧት ስልጠናውን ሲሰጡንና ሲያለማምዱን፥ እስከ ጫፍ እየወጡ ለመቀጠል በተቻለ መጠን ወደ ታች አለመመልከት፥ በደረሱበት ተጣብቆ ሚዛን ጠብቆ፥ በደረት ተለጥፎ መቆየትና ከዚያ እንደ አመቺነቱ ወደ ላይ መቀጠል ነው ብለው ነግረውናል። እመካከል ላይ አንድ በጣም አስቸጋሪና ፈታኝ ቦታ ነበረ። እዚያች ቦታ ላይ አንዳንዶቹ የተጣበቀ ሐውልት መስለው ዓለቱ ላይ ተለጥፈው ጡንቻዎቻቸው ተገታትረው ለብዙ ደቂቃ ይቆዩባታል። ጥቂት ወጣቶች ከዚያ ነበር ተንሸራትተው ዝቅዝቅ የሚወርዱት። አንዳንዶቹ ተስፋ ቆርጠው ይወርዳሉ።

ያ የቋጥኝ ቡጥጫ ስፍራ፥ ጳውሎስ፥ በደረስንበት በዚያ እንመላለስ ያለውን ጥቅስ አሳሰበኝ። ወደ ላይ ለመቀጠል እዚያች ስፍራ ላይ ተጣብቀን መቆየት አለብን። መንሸራተት የለብንም። ተጣብቀን የምንቆየው ደግሞ እዚያ ተጣብቀን ለመቅረትና እዚያ ስፍራ ለመኖር ሳይሆን ወደ ላይ ለመቀጠል እስክንችል ድረስ ነው። እንደቻልን እመር ብለን ሽቅብ ከፍ እንላለን። እስክንል ድረስ ግን በዚያ በደረስንበት መቆየት የለፋነው በዜሮ ተባዝቶብን በሄድንበት መንገድ እንደገና እንዳንሄድ ይረዳናል። ከላይ እንዳየነው ክርስትና አንድ ቦታ እንደ ጅብራ መገተር ሳይሆን መመላለስ ነው። በደረስንበት በዚያ እንድንመላለስ ጌታ ይርዳን፤ እርሱ ከአርያም ይባርከን።

ዘላለም መንግሥቱ © 2015 (፪ሺህ፭) ዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት

[1] *ደስታ ተክለ ወልድ፤ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፤ ገጽ 380፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፥ 1962 ዓመተ ምሕረት፥ ዐዲስ አበባ።*

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ © 2015
የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ። 2ጢሞ. 2፥15
ባለቤትነቱን ሳይውስዱ ማባዛትም ማይልም ይፈቀዳል።

አ ጨ ብ ጫ ቢ

(ከሚቀጥሉት ገጾች)

"ላለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት የነቢያት ድምጽ ታፍኖ ነበር። አሁን እግዚአብሔር አምላክ የነቢያትን አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያን በተሃድሶ መንፈስ እየለቀቀ ይገኛል።"

"ቤተ ክርስቲያን ያለ ወንጌላዊ እድገቷ የተገታ እንደሆነ ሁሉ፥ ያለ ነቢይም ኃጢያትን የመቋቋም ኃይሏ ደካማ ነው።"

ነቢይ በላይ፡-አንቺ እናት በእርግጥም የእግዚአብሔር ነቢይ እንደሆንኩኝ እንድታውቂ የባለቤትሽን እህት ስም ልንገርሽ?
ሴቱቱ፡-ንገረኝ የእግዚአብሔር ሰው
ነቢይ በላይ፡-በውኑ የባለቤትሽ እህት ስም አስቴር አይደለምን?
ሴቱቱ፡-አዎ የእግዚአብሔር ሰው ትክክል ነው! . . .

ለሊት ለሊት ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ አንድ ሰው ቢያነስ ለአንድ ዓመት ያህል ፍትፍት በሰሃን እያመጣ ይመግበኝ ነበር። ያንን ሰው እጁን እንጂ አካሉን አላይም ነበር። በመጀመሪያ ሰሞን ህልም ይመስለኝ ነበር። . . .

. . . በአብዛኛው የሚነግረኝ አጠገቤ ዳመና ቆሞ ነው። በቁመቴ ልክ የሚቆም ዳመና አለ፤ . . . እሱ ሲሄድ ነው ምሄደው፤ ከፊቴ ሲሄድ እሄዳለሁ እከተለዋለሁ፤ ጎኔ ላይ ይቆማል፤ ሰው አስመጥቼ አሁን መልክት ስናገር አሁን አጠገቤ ቆሞ ነው ሚነግረኝ፤ ሙሉ መረጃ ያወራልኛል። . . .

ነቢይ በላይ፡- በመንፈስ ሳሎኑን ዘልቄ ወደ መኝታ ክፍልሽ ገባሁ። የባለቤትሽን ፎቶ አየሁ። የባለቤትሽ ፎቶ የሚገኘው በመኝታ አልጋሽ አጠገብ ነው።
ሴቲቱ፡-አዎን የእግዚአብሔር ሰው ፍጹም ትክክል ነው።
ነቢይ በላይ፡- ያንን የባለቤትሽን ፎቶግራፍ አነጋገርኩት። "አንተ የት ነው ያለኸው?" አልኩት። እርሱም እንዲህ ሲል መለሰልኝ "እኔ እኮ ሞቻለሁ" አለኝ። . . .

. . . ይህኛው 'ነቢይ' የሞተና የተቀበረ አንድ ሰውን ጌታችን አልዓዛርን እንዳስነሣው ከሙታን ለማንሣት በመሞከር ከአንድ ጉባኤ ሕዝብ ጋር በተቀበረ በ3ኛው ቀን መቃብር አስቆፍሮ፥ ሳጥን አስከፍቶ፥ ሬሳ አስወጥቶ፥ መነሣቱን ለማረጋገጥ ወደ ሆስፒታል አስወሰደ። . . .
አንዴ የሞተ ሰውን ሁለቴ የሚቀብሩ አሳፋሪ ጉዶች ፈሉ! እነዚህ ያሳፍራሉ እንጂ የሚያፍሩ ግን አይመስሉም።

በግልም ይሁን በጉባኤ፥ በቴሌቪዥን ይሁን ወይም በስልክ፥ የሚነገረው 'ትንቢት' በሙሉ የመሳካት፥ የመሻገር፥ ጠርምሶ የመውጣት፥ የቪዛ፥ የበር መከፈት፥ የተራራ መናድ፥ ልጅ የመውለድ፥ መኪና የመግዛት፥ የሥልጣን ማግኘት፥ የመቀባት፥ የምኑ ቅጡ ነው። ይሄ ሆኗል ወንጌሉ። ይህ ሆነ ቅድስና፥ ይህ ሆነ መስቀሉ። ኃጢአት አይወቀስም። ውስጥ አይፈተሸም፤ የስልክ ቁጥር ይነገራል። . . .

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው ነቢያት <u>ቃሉን ሲገልጡ</u> እንጂ ወደ መድረክ ሰውን ጠርተው <u>ያንን ሰው ሲገልጡና</u>፥ 'የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ልክ ነህ' ሲባሉ አይደለም። . . .

ዛሬም የጋዜጣ ስነ መለኮታውያን ድምጻቸው አጉል ጎልቶ እየወጣ ይገኛል። አጉሉ ነገር ጉልህ አወጣጡ ብቻ ሳይሆን ትምህርቱና ድርጊቱ፥ ውጤቱና መዘዙም ጭምር ነው። እንደ አንዳንድ መድኃኒቶች የጎን ጠንቆቹም ብዙ ናቸው። . . . ተጠንቃቂና አስጠንቃቂ እንሁን።

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2015

የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ። 2ጢሞ. 2፥15

ባለቤትነቱን ሳይውስዱ
ማባዛትም ማይልም ይፈቀዳል።



ጭብጨባ ለተለያዩ ነገሮች ይደረጋል። በጣም የተለመደውና በየቦታው የሚታየው ጭብጨባ የዘፈን ጭብጨባ ነው። የመዝሙርም ጭምር። ይህ የዜማውን ፍጥነት ወይም ምት ለመጠበቅ የሚረዳና ማዳመቂያም ነው። ሌላው ጭብጨባ የአድናቆት መግለጫ ነው። የኳስ ግብ ሲገባ፥ ነጥብ ሲቆጠር ይጨበጨባል። አለቃ ወይም መሪ ወደ አዳራሽ ሲገባም ይጨበጨባል፤ ይህ ለሙሽራም፥ ለአርበኛም ይሆናል። ዲስኩር አድራጊ ኃይለ ቃል ሲናገር ወይም ንግግሩን ሲጨርስም ይጨበጨባል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለጭብጨባ የሚናገሩ ጥቅሶች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጭብጨባ ይናገር እንጂ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታዩት ጭብጨባዎች መላቅጥቸው የጠፋ ሆነዋል። በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጭብጨባ የሚናገርባቸውን ሁኔታዎች እንይ። በጠቅላላው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወደ አሥራ አምስት ጊዜያት ያህል ጭብጨባ ተጠቅሶአል።

በመጀመሪያ ለእግዚአብሔር የተጠቀሱትን ጥቂት እንይ። በመዝ. 98፥8 ያለው፥ *ወንዞችም በእንድነት በእጅ ያጨብጭቡ* የሚል ቃል አለ። በኢሳ. 55፥12 ላይም የሜዳ ዛፎችም እንደሚያጨበጭቡ ይናገራል። ይህ ሰዎችን አይመለከትምና እንለፈው። ምሳሌያዊ አገላለጥ ሆኖ ግን የፍጥረትንና የተፈጥሮን ተገዥነት ያመለክታል። ሌላው በመዝ. 47፥1 ላይ የምናገኘው አሕዛብ ሁሉ አጨብጭበው ለእግዚአብሔር እልል እንዲሉ የተነገረ ቃል ነው። ይህ ጥቅስ ይመስለኛል ዘመነኞች ሰባኪዎች ጉባኤን የሚያስጨበጭቡበት። መዝሙሩን በሙሉው ስናየው ግን እግዚአብሔር ለምድር ሁሉ ንጉሥ ነውና በማስተዋል ዘምሩ የሚለው ስንኝ ያለበት፤ ማስተዋልን የተላበሰ አምልኮን የሚጋብዝ ነው። ባለማስተዋልና ሰባኪዎች ጉባኤው ጭር ያለ ሲመስላቸው አጨብጭቡ የሚሉትን አይመስልም።

ሁለተኛው አሳብ ከላይ ለመሪ ወይም ለአድናቆት እንደጠቀስኩት የመሰለ ጭብጨባ በ2ነገ. 11፥12 እናገኛለን። ጨቅላው ኢዮአስ በነገሰ ጊዜ በዚያ የነበሩት ሰዎች፥ "ንጉሡ ሺህ ዓመት ይንገሥ" እያሉ ያጨበጨቡት ጭብጨባ ነው። የደስታ፥ የይታወቅ፥ የይሰማ ጭብጨባ ነው።

በቀሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ሁሉ ጭብጨባ የተጠቀሰው በአሉታዊ መልኩ ነው። ለምሳሌ፥ በዘኁ. 24፥10 ባላቅ በንዴት አጨበጨበ። በሕዝ. 21፥17 እና 22፥13 የተጠቀሰው ማጨብጨብ እግዚአብሔር ቅጣቱን ሊያሳርፍባቸው እና በቁጣው መነሣቱን ያሳያል። በሌሎችም ስፍራዎችም ቅጣትን፥ ንቀትን፥ በመፍረስ መደነቅን እና የመሰሉትን ያሳያል፤ ኢዮ. 27፥23፤ 34፥37፤ ሰቆ. 2፥15፤ ሕዝ. 6፥21፤ 21፥14-17፤ 22፥13፤ 25፥6፤ ናሆ. 3፥19።

ከዚህ በተለየ መልኩ የሚደረግ ማጨብጨብ ደግሞ አለና ያንን ማየትና ማሳየት እፈልጋለሁና ወደ አጨብጫቢዎችና አጨብጫቢነት ልምጣ። አንድ ነገር ሲደረግ አድራጊዎች አሉ፥ ተደራጊዎች አሉ፥ አስደራጊዎች አሉ፥ አደራራጊዎች አሉ። ይህ የኋለኛው ቃል ይኑር ወይም ልፍጠረው አላውቅም። አደራራጊዎች ያልኩት ሲደረግ አበረታቾችን ነው። አጨብጫቢዎች የምላቸው እነዚህን ነው። ዘፈን በደመቀበት አጨብጫቢ እንዲሉ። የደስታ ተክለ ወልድ መዝገበ ቃላት የአጨብጫቢን አንዱን ትርጉም፥ ያጨበጨበ፥ የሚያጨበጭብ ብሎ ሁለተኛውን ደግሞ የነገር ረዳት አዳማቂ ይለዋል።[2] ሁለተኛውን ትርጉም ነው የፈለግሁት።

አንዳንዶች አዳማቂዎች መልካም ያደርጋሉ። ማበረታታት ነው፥ ማስቀጠል፥ ማስጨረስ። ማጨብጨብ፥ "ቀጥል፥ በል፥ ይመርብህ፥ አድርግ፥ በርታ. . ." ማለት ነው። ማድነቅን፥ እንዲጨርስ ማበርታትን፥ ማደፋፈርን ያሳያል። አጨብጫቢ ሲባል ግን ጊዜ ትርጉሙ አሉታዊ ነው፤ አሉታዊው አተረጓጎሙም ትክክለኛ አተረጓጎም ነው። አጨብጫቢነት ትክክል ያልሆነ ነገር ሲደረግ አውቆ ወይም ሳያውቁ ማበረታታትና ማደፋፈርን ያመለክታል።



ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደ አሸን እየፈሉ ለመጡት የስሕተት ልምምዶች ዋናዎቹ ምክንያቶች ስሕተተኞቹና የሚጎነዱበት መንፈስ እና/ወይም ግፊት ቢሆኑም በሁለተኛ ደረጃ ተመልካችና አጨብጫቢ አድማጮቻቸውም ናቸው። የተመልካቾችና አድማጮች ሚና ቀላል አይደለም። አጨብጫቢነት ትልቅ ጉዳት አለበት። እንዲህ ያሉ ነገሮች የሚከሰቱት አእምሮአቸውን ከቃሉ ጋር በማያቀናጁት እና እየሆኑ ያሉትን ነገሮች በማያስተውሉ ከቃሉ ጋር በማያስተያዩ ሰዎች ዘንድ ነው። አእምሮአቸውን የተቀሙ፥ ሁሌ እየተማሩ እውነትን ወደ ማወቅ የማይደርሱ ሰዎች ያኔ እንደነበሩ ዛሬም አሉ። እነዚህ በቀላሉ አጨብጫቢ የሚሆኑ የአድናቆት ረሃብተኞች ሰለባዎች ናቸው። አጨብጫቢዎች አገልጋዮችን ወደ ጥፋት የሚያነጉዱና አብረዋቸው የሚነጉዱ ናቸው። ዛሬ በአማካይ ቤተ ክርስቲያን አምልኮም እንኳ ጭብጨባ እጅ እጅ እያለ የመጣ፥ ከመስመር የወጣ ነገር እየሆነ ነው።

ሰንበሌጥ ክርስቲያኖች

ይህን ስል የጥንት ክርስቲያኖች ሁሉ ድንቅዬዎች የዘንድሮዎቹ ደግሞ ድንክዬዎች ማለቴ አይደለም። ብቻ እስኪገርም ድረስ ሳይበቅሉና ስር ሳይሰድዱ ከአንድ መደብ እየተነቀሉ በሌላ ቦታ እንደሚተከሉ ችግኞች እየተነቀሉ የሚተከሉ፥ አሁንም እየተነቀሉ የሚተከሉ፥ ስር ሳይኖራቸው ወደ ላይ ብቻ የሚያድጉ የጭንጫ ሰንበሌጥ ክርስቲያኖች በገፍ ተወልደውልናል። ብዙዎች የዘንድሮ ክርስቲያኖች ቆም ብለው እንደ ቤርያ ሰዎች፥ "ነገሩ እንዲሁ ይሆንን?" ብሎ በመጠየቅ ፈንታ፤ ቁሙ ሲባሉ መቆም፥ ተቀመጡ ሲባሉ መቀመጥ፥ አጨብጭቡ ማጨብጨብ፤ አሜን በሉ አሜን፤ ጩኹ ማጓራት፤ ሳቁ ሲሏቸው መንከትከትና መገልፈጥ፤ ገና ሳይገፏቸው መገንደስ፤ ሲገፏቸውማ ከወለሉ በታች መስጠም ይቃጣቸዋል። ዝለሉ ሲሏቸው እንጣጥ፤ የቢልቃጥ ውኃ ግዙ መግዛት፤ የዝተት ጥብቆ ቁራጭ ግዙ፥ መግዛት። "ለምን?" ብሎ መጠየቅ ነውር ይመስላቸዋል። 'እውነት ይህ የእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ሥራ ነው?' ብሎ መጠየቅ መንፈስ ቅዱስን መቃወምና እግዚአብሔርን

---

[2] *ደስታ ተክለ ወልድ፤ ያማርኛ መዝገበ ቃላት፤ ገጽ 598፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፥ 1962 ዓመተ ምሕረት፥ ዐዲስ አበባ።*

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2015

የተገዳደሩ አንገተ ደንዳኖች መሆን ይመስላቸዋል። የሚያሳዝነው **አንዳንዶቹ** እንደዚያ የተማሩ ናቸው። መናፍስትን ለመለየት መጣር መንፈስ ቅዱስን መናቅ ነው ብለው ያምናሉ። ሰይጣን ወይም ሰይጣናዊ አሠራር የቤተ ክርስቲያንን መድረክ የሚረግጥ አይመስላቸውም። **ሌሎች ደግሞ** በፍርሃት፥ በይሉኝታና በአቻዎች ጉንተላ ወይም አቻዎችን ለመምሰል በሚደረግ ግፊት (peer pressure) ነው አጨብጫቢ የሚሆኑት። እነዚህ ራሳቸውም በዋል ፈሰስ የሆኑና እንደ ቦይ ውኃ ወደቀደዱላቸው የሚፈስሱ በመልካሙ መሬት ሳይሆን በመንገድ ዳርና በጭንጫ ላይ እንደወደቀው ፍሬ የሆኑ ክርስቲያኖች ናቸው። እነዚህ ናቸው ዘንድሮ በጣም የበዙልን።

የሚያሳዝነው ጉዳይ ግን ይህ ችግር የራሳቸው ችግር ብቻ ሆኖ የሚቆም ሳይሆን ስለ ክርስቶስ ማወቅ የሚፈልጉና ክርስቶስን ማወቅ የሚፈልጉትን ጠያቂዎችና ፈላጊዎች ከሩቅ እያስቀራቸው መሆኑ ነው። አንዳንዶቹንም የክርስቶስ ተቃራኒ ወደሆነ አቅጣጫ ፈታቸውን እንዲያዞሩ እያደረጋቸው ነው። ይህ ያሳዝናል። እነዚህ ናቸው የሐሰተኛ ነቢያትና ሐዋርያት አሳቢና ቀላቢ፥ መጋቢና አንጋቢ፥ እንዲሁም አጃቢና አጨብጫቢ በመሆን የሚያገለግሉት። የዕድገት ዘመናት እያስቆጠርንም በጥቅሉ ስንታይ ከጭበጨባ ባህል ገና ያልወጣንና ያልጸዳን ዛሬም መፈክራም ትውልድ ነን።



በቅርብ የአንድ 'ነቢይ' የዩቲዩብ ቁራጮች ተላኩልኝና አየሁት።[3] ሌሎችም ይህንን የሚመስሉ በዩቲዩብ የተንጠባጠቡ ብዙ ናቸው። ከተላኩልኝ ሁለቱን ብቻ እንይ። ስፍራዎቹን ከታች ከግርጌ ማስታወሻ ላይ ወስዶ ማየት ይቻላል። ሁለት ሴቶች ወደ ፊት ወጥተው ስለ እነርሱ 'የተገለጠለትን' የቤተ ዘመድ ስሞች፥ ስልክ ቁጥሮችና ወዘተ፥ ነው የሚናገረው። አቀራረቡ ፍጹም ተውኔታዊ ነው። ሴቶቹ ወደ ፊት ወጥተው ንግርቱ ይነገርላቸዋል። እነርሱም፥ 'የእግዚአብሔር ሰው' እያሉና እየተቅለሰለሱ ትክክልነቱን ያረጋግጣሉ። እየተገረሙ ወይም የተገረሙ እየመሰሉ ያረጋግጣሉ። ሕዝቡም ያወካል፥ ያጨበጭባል፤ ብድግ ቁጭ እያለ ይስቃል። እንደ ጳውሎስ ዘመን ዛሬም ሁልጊዜ እየተማሩ እውነትን ወደ ማወቅ ሊደርሱ ከቶ የማይችሉ ሞኞች ሴቶች እልፍ ናቸውና ይህ ብቻ ሳይሆን ብዙ 'ነቢያት' ሴቶች ላይ ነው ትኩረት የሚያደርጉት። እነሆ አንድ ናሙና፤

ነቢይ በላይ፡-የባለቤትሽን ስም ልንገርሽ?
ሴቱቱ፡- አዎን የእግዚአብሔር ሰው
ነቢይ በላይ፡- ጉብረኒዮርኒስ
ሴቱቱ፡- አዎን የእግዚአብሔር ሰው ፍጹም ትክክል ነው
ነቢይ በላይ፡-የባለቤትሽን ወንድም ስም ልንገርሽ?
ሴቱቱ፡-አዎን የእግዚአብሔር ሰው ንገረኝ
ነቢይ በላይ፡-ጉብረክርስቶስ
ሴቲቱ፡ አዎን የእግዚአብሔር ሰው እውነት ነው
ነቢይ በላይ፡-እሺ አንዲት የምትቀርቢያት ጎረቤት አለቺሽ። ስሟን ልንገርሽ?
ሴቱቱ፡-አዎን የእግዚአብሔር ሰው ንገረኝ
ነቢይ በላይ፡-ይህች ጎረቤትሽ መልኳ ቀይ ነው። ስሟ ደግሞ ፀሐይ ይባላል
ሴቱቱ፡- አዎን የእግዚአብሔር ሰው ፍጹም ትክክል ነው (በመገረምና በመደነቅ ውስጥ ሆና አልልታዋን ታቀልጠዋለች)
ነቢይ በላይ፡- ሌላም ነገር ልንገርሽ። ባለቤትሽ ሞቷል። ከዚህ በፊት ምግብ ቤት ነበረሽ። አሁን ምግብ ቤቱ በኪሳራ ተመቶ ተዘግቷል። ሦስት ልጆች አሉሽ፤ አንዷ ድራዳዋ ነው ያለቺው። አንዷ አዲስ አባ ናት፤ አንዱ ደግሞ እዚሁ ናዝሬት ነው ያለው።
ነቢይ በላይ፡- የእኔ እናት በውኑ ይሄ የተናገርኩት ሁሉ ትክክል አይደለምን?
ሴቱቱ፡-የእግዚአብሔር ባሪያ ሆይ ሁሉም ትክክል ነው (ጉባኤውና ሴቲቱ በታላቅ ደስታ ያጨበጭባሉ፣በመገረም ይስቃሉ፣ ይሯሯጣሉ...)
ነቢይ በላይ፡-አንቺ እናት በእርግጥም የእግዚአብሔር ነቢይ እንደሆንኩኝ እንድታውቂ የባለቤትሽን እህት ስም ልንገርሽ?
ሴቱቱ፡-ንገረኝ የእግዚአብሔር ሰው
ነቢይ በላይ፡-በውኑ የባለቤትሽ እህት ስም አስቴር አይደለምን?
ሴቱቱ፡-አዎ የእግዚአብሔር ሰው ትክክል ነው![4]

በቃለ ምልልሱ ውስጥ ያሰመርኩበትን ክፍል እንደገና እናስተውል። ጭብጨባ፥ መገረም፥ ሳቅ፥ ጩኸት። በጉባኤው ውስጥ የጠረጠረ፥ የጠየቀ፥ የመረመረ፥ 'ይህ ከየት መጣ?' ያለ፥ የተቆጣ ይኖር ይሆን? መቼም ያን በሚያህል ጉባኤ ጥቂት አይጠፉም። መገረምና መደነቅ ብቻውን የነቢይ አገልግሎት ምልክት አይደለምም፥ ሆኖም አያውቅም።

ነቢያት ነን የሚሉ ሰዎች ነቢይ የሚለውን ቃል ወይም ተጓዳኙን ትንቢት የሚለውን ቃል፥ ወይም ይህን ሰው የሾሙት ሰዎች በሾሙት ወይም በቀቡት ቀን የጠቀሱትን የነቢያት ቢሮ ያሉትን ቢሮ በግልጽ ተርጉመው አስቀምጠውት ከሆነ አላውቅም። የዚህ 'ነቢይ' ድረ ገጽ ላይ ትንቢትን ወይም ነቢይን ተርጉሞት ከሆነ ብዬ ብፈትሽ የለም። በድረ ገጹ ከጸጋ ስጦታዎች መካከል ያለው አንድ ስጦታ ብቻ ሆኖ ያም፥ 'ያለ መድኃኒት የሚደረግ መለኮታዊ ፈውስ' ተብሎ ተቀምጦአል። ትንቢትን በተመለከተ፥ Prophecy in the Church በሚል ርዕስ ስር የተቀመጠው ሳኑበበው ስላለመሳደብ ወይም አለመራገም፥ ዳንስ ቤት እና ዳንኪራ ቤት የመሳሰሉ ቦታዎች ስላለመሄድ የተጻፈ እንጂ ከቶም ከትንቢት ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ነው። እንዲህ ያለው የዳንስ ቤትና ዳንኪራ ቤት ነገር በእምነት አቋም ውስጥ መጻፉ ራሱ እያስገረመኝ ነው ያነበብኩት። ከዓመታት በፊት ይህ እንኳን ሊጻፍ ሊታሰብም ስፍራ የሌለው ነገር ነበረ። ሰው እንዲህ ገብስ ከሆነ መጻፉ አስፈላጊ ነው ማለት ነው።

እነዚህ የዘመናችን ነቢያትና የነቢያቱ ቧሚዎችም ለራሳቸውና ለሌላውም ሲሉ ይህን ትርጉም ከመጽሐፍ ቅዱስ በመነሣት በግልጽና በማያሻማ ትርጉሙ ሊተረጉሙትና ሊመልሱት የተገባ ነው። የተገባበት ዋና ምክንያት ራሳቸው ይህ አገልግሎት ምን መሆኑን እንዲያውቁት ነው። በግልጽ እንደሚታየው ምንነቱን በማያውቁትና ከሌሎች ሰምተው በተለምዶ በቀሰሙት መስክ ነው እየተንደፋደፉ ያሉት። በዚህ ምክንያት ትርጉሙን አውቀው ካላሳወቁ ግራ ተጋብተው ግራ የሚያጋቡ መሆናቸው ይቀጥላል። ዛሬ ለአንዱ ትንቢት ማለት ምስጢር መግለጥ፤ ለሌላው፥ የዛሬ ወር የሚሆነውን መናገር፤ ለሌላው፥ የሰው ዘመዶች ስም መጥራትና ማስጨብጨብ፤ ለሌላው የስልክ ቁጥር ማውጫ ይመስል ቁጥር መንገር፤ ለዚህ ይህ፤ ለዚያ ያ እየሆነ ማንም የፈለገውን እየሆነና እያደረገ፥ እየቀደደና እየደረተ ሊኖር ወለል ያለ በር መበርገድ ነው። የለም፤ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ነቢይና ትንቢት እንደደፈረሰ ውኃ ያለ መልክ የለውም። በጣም ግልጽ ነው።

የብሉይ ኪዳንም ሆነ የአዲስ ኪዳን ነቢያትን አገልግሎቶች፥ ተግባሮችና ትምህርቶች፥ በእስራኤልም፥ በቤተ ክርስቲያንም በቅዱሳን ላይ፥ በደነዘዙቱ አማኞች ላይ፥ በእግዚአብሔር ጠላቶችም ላይ የፈጠረው ለውጥ ተጽፎልን በቃሉ ውስጥ አንብበናል። ስለዚህ የነቢያት አገልግሎት መልክ ምን መምሰል እንዳለበት ለዚህ ዘመን ክርስቲያኖች እንግዳና ዱብ ዕዳ መሆን አይችልም። ደግሞም የቀደሙት ነቢያት ቀድመው እንዲሄዱ የተደረጉት የኋለኞቹ አዲሶቹ መንገዱን እንዲያውቁት ጭምር ነው። የእግዚአብሔር ማንነት አልተለወጠም። የሰው ባህርይም አልተለወጠም። ቃሉም አልቀጠነም። የኃጢአት ደመወዝም ኃጢአት ቢበዛም አልተቀነሰም። ኃጢአት ረከሰ፤ ዋጋው ግን አልቀነሰም።

[3] http://www.youtube.com/watch?v=ll7CbUeyr7o
https://www.youtube.com/watch?v=3KDQqELnFvw

[4] ዳንኤል፥ ቁ. 12፥ ሰኔ 2006 ዓ. ም.

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ © 2015

ነቢያትና ሐዋርያት ለማስገረምና ለማስጨብጨብ አይደለም የተጠሩት። ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱና አሕዛብን አስገርሙ፥ አስደንቁ፥ አስጨብጭቡ አልተባሉም። ማንም የእግዚአብሔር ነቢይ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ሰዎችን ሲያስገርም አናይም። የተላኩት የእግዚአብሔርን እውነት ለማወጅ ነው። ቃሉን ለመግለጥ ነው። ወንጌልን ለመስበክ ነው። ወንጌል ደግሞ የክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት ለሰው ልጆች የከፈተው የዕርቅና የይቅርታ መንገድ ነው። መስቀሉ የኃጢአት ስርየት የሆነበት ደሙ የፈሰሰበት የመሥዋዕት ሥራ ነው። ከዘላለም የነበረው ቃል ሥጋ የሆነበት ምክንያትም ይህ ነው። ወንጌል ይህንን የዕርቅ የምሥራች ማወጅ ነው። ወንጌል ወንጀል አይደለም።

ክርስቶስ *ሥጋ መሆኑን*፥ በመስቀል *መሞቱን*፥ *ደሙን* ማፍሰሱን የሚያነሳና የሚያውለበልብ ሳይሆን ሰዎችን አደሳስቶና አስቆ፥ አዝናንቶና አስገርሞ ወደ ቤት የሚልክ አገልግሎት ለማገልገል ጌታ ያኔ እነዚያንም አልላካቸውም፤ ዛሬም እነዚህንም እኛንም አልላከንም። እንዲህ የሚያደርጉ የዘመናችን 'ነቢያት' ያልዳኑትን ከጥፋት ጎዳና የማይመልሱ ብቻ ሳይሆኑ የዳኑትንም እውነትን የተቀሙ ሆነው እንዲኖሩ የሚያደርጉ ሐሳውያን ናቸው። ከውጭ ሆነው ለሚታዘቡና የክርስትናን ስም ለማጉደፍ ለሚጠባበቁ ደግሞ ቀዳዳ በመፍጠር የስድብ ምክንያት መሆን ነው።

ይልቅስ ጠንቋዮች ናቸው በማስደነቅና በማስገረም ሰዎችን በመዳፋቸው ውስጥ ማኖር የሚፈልጉ። በሐዋ. 8፥9 *ሲሞን የሚሉት አንድ ሰው ግን፥ እኔ ታላቅ ነኝ ብሎ፥ እየጠነቈለ የሰማርያንም ወገን <u>ሊያስገረመ</u> ቀድሞ በከተማ ነበረ*። ይላል። ሐዋርያት ሰዎችን የማስገረም ስጦታ አልተቀበሉም። ወንጌልን መስበክ አስደናቂ ለውጥ በልብ ውስጥ የሚፈጥር *ሥራ* ቢሆንም የአስደናቂነት *ሙያ* ግን አይደለም። በራእ. 13፥3 *ምድርም ሁሉ ለአውሬውን እየተከተለ <u>ተደነቀ</u>* ይላል። ማስደነቅ ትኩረትንና አድናቆትን ከአድናቂ ወደ አስደናቂ የሚያቀብል ግርግር ነው። የምናየውንና የምንሰማውን ሁሉ ጉድ እያልን የምንቀበል ከሆነ ጉድ እያልን እስከ ሲያል ደጅ ልንሄድ እንችላለን። ፍጻሜያችን አያምርም። እንደ ቤርያ ሰዎች መርማሪዎች እንሁን።

ከላይ የተጠቀሰው 'ነቢይ' ታሪክ የቀረበበት መጽሐፍ ዛሬ አገራችን በነቢያት እየተንበሸበሸች መሆኗንና ይህም የመባረኳ ዋና ምልክት እንደሆነ አድርጎ በማቅረብ፥ 'ላለፉት ሁለት ሺህ ዓመታት የነቢያት ድምጽ ታፍኖ ነበር፤ አሁን እግዚአብሔር አምላክ የነቢያትን አገልግሎት ለቤተክርስቲያን በተሃድሶ መንፈስ እየለቀቀ ይገኛል።' ብሎአል።[5] ጸሐፊው ይህንን አባባል ከሌላ ምንጭ እንደጠቀሰው በቅንፍ አስቀምጦታል። ግን አፋኙ ማን መሆኑና የታፈኑት ነቢያት እነማን መሆናቸው አልተመላከተም። ይህ ጥቅልል አነጋገር ከተሰጣበት ሜዳ የተወሰደ እንጂ በታሪክ ጥናት ያልተደገፈ እንደሆነ በግልጽ ይታያል። ደግሞም፥ "ቤተክርስቲያን ያለ ወንጌላዊ እድገቷ የተገታ እንደሆነ ሁሉ፥ <u>ያለ ነብይም ኃጢያትን የመቋቋም ኃይሏ ደካማ ነው።</u>" ይላል የጽሑፉ አዘጋጅ።

ይህ ማለት እኮ እነዚህ ነቢያት የተባሉ ሰዎች ክርስቲያኖች ኃጢአትን እንዲቋቋሙ የሚያስችል ውስጣዊና የራሳቸው ኃይል አላቸው ማለት ነው። በኢትዮጵያ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ታሪክ ከአንድ ምዕት ዓመት ጥቂት የዘለለው ነው። በነዚህ ዓመታት እንደ አሁኖቹ ያሉት ነቢያት አልነበሩምና ቤተ ክርስቲያን ኃጢአትን መቋቋም ሳትችል ኖራለች ነው የሚለን። በአንጻሩ፥ አሁን ደግሞ፥ ነቢያት እንደ እንጉዳይ እየፈሉ፥ አንጓው ተቆርጦ ሲተከል እንደሚበቅል ሸንኮራ በየማሳው እየበቀሉና እየበዙ ስለሆኑ ቤተ ክርስቲያን ኃጢአትን መቋቋም ችላለችና ምንም ኃጢአት አይሰማም፥ አይደመጥም ማለት ነው? እውነቱ ግን ይህ አይደለም። አንዳንዶቹ (ምን አንዳንዶቹ?) 'ነቢያት' የሰዎችን *መንፈሳዊ* ሳይሆን *ሥጋዊና* ስሜታዊ ፍላጎት እያዳበሩ መሆናቸውን ከሚናገሯቸው ትንቢቶች ማወቅ ይቻላል። የማይጨበጡ የተነገሩ 'በረከቶችን' ለማግኘት ወደ ማጭበርበርና ሥጋዊ ብልሃቶች የገቡና ትንቢቱን በጉልበታቸውና በዘዴያቸው ሊያገኙ በመጣር ይስሐቅን ሳይሆን እስማኤልን እየወለዱ ያሉት ቁጥር ጥቂት አይደለም። የጎሊና መብራታቸውን አጥፍተው አጭበርብረው ያገኙትን ንዋይ እግዚአብሔር እንደባረካቸው እየቆጠሩ ኃጢአትን እየተዳፈሩ ያሉቱ ጥቂት አይደሉም። ማንም ክርስቲያን ከኃጢአት ፈተና እስኪሞት ድረስ የጸዳ አይሆንም። <u>ያለ ነብይም ኃጢያትን የመቋቋም ኃይሏ ደካማ ነው።</u>" ማለት ግን ሽንገላ ብቻ ሳይሆን አሳች ትምህርትም ነው

ቤተ ክርስቲያን ኃጢአትን የምትጋፈጠውና ፈተናን የምትቋቋመው ደግሞ ዘመነኛ 'ነቢያትን' በመማጸን ሳይሆን ክርስቲያኖች ዕለት ዕለት በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ኑሮ በመኖርና ቃሉን በመመርመር መታዘዝን ሲለማመዱ ነው። ቤተ ክርስቲያን ኃጢአትን የምትቋቋመው በነቢያት ከሆነ ነቢያት መንፈስ ቅዱስ ናቸው ማለት ነው? እንደዚህ ያሉ ባለማስተዋል የሚነገሩ የስንፍና ንግግሮች የዘመናችንን 'ነቢያት' ከስፍራ አስፈንጥረው ጣራ የሚያስበረቅሱ የመሆናቸው ጉዳት ቀላል አይምሰለን። 'ነቢያቱ' የሚያደርጉትን ካላወቁ የሚጽፉቱ ተጠንቃቂ እንጂ ልቅ መሆን የለባቸውም። ነቢያት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሲታዩ ኃጢአትን ሲወቅሱ እንጂ ኃጢአትን የመቋቋሚያ ኃይል ሲሆኑ አይደለም። ነቢይ ነን ከሚሉቱ <u>አንድም የወቀሳና የተግሳጽ ቃል የሌለበት የዚህ ዘመን ትንቢት የሚያሳየን እውነትም ኃጢአት ከቤተ ክርስቲያንና ከየክልሉ ውስጥ ተጠራርጎ የወጣ ያስመስለዋል</u>። ስለ ኃጢአት አለመናገራቸው ግን ኃጢአት የለም ማለት ነው ብለን አንሳት።

ይህንን እውነት ሳናስተውለው የቀረን ካለን እገረማለሁ። በግልም ይሁን በጉባኤ፥ በቴሌቪዥን ይሁን ወይም በስልክ፥ የሚነገረው 'ትንቢት' በሙሉ የመሳካት፥ የመሻገር፥ ጠርምሶ የመውጣት፥ የቪዛ፥ የበር መከፈት፥ የተራራ መናድ፥ ልጅ የመውለድ፥ መኪና የመግዛት፥ የሥልጣን ማግኘት፥ የመቀባት፥ የምኑ ቅጡ ነው። ይሄ ሆኗል ወንጌሉ። ይህ ሆነ ቅድስና፥ ይህ ሆነ መስቀሉ። ኃጢአት አይወቀስም። ውስጥ አይፈተሸም፤ የስልክ ቁጥር ይነገራል። የዘመናችን ሰነፍ ነቢያት 'ነርፍ አይመጣም፤ አትስጉ' ብለው ክርስቲያኖች የውሃ ዋና እንዳይማሩና እንዳይለማመዱ የሚያሰንፉ የሰላም ብቻ ሰባኪዎች ናቸው። በሕዝ. 13፥10-15 ሰላም ሳይኖር ሰላም እያሉ ስለሚሰብኩ የተናገረው የነቢዩ ቃል ከዚህ የሚመሳሰል ነው።

ሰላም ሳይኖር፥ ሰላም እያሉ ሕዝቤን ሊታልለዋልና፤ አንዱም ሰው ቅጥር ሲሠራ፥ እነሆ፥ ገለባ በሌለበት ጭቃ ይመርጉታልና። ገለባ በሌለበት ጭቃ ለሚመርጉት ሰዎች፥ ይወድቃል በላቸው። የሚያሰጥም ዝናብ ይዘንባል፥ ታላቅም የበረዶ ድንጋይ ይወድቃል፥ ዐውሎ ነፋስም ይሰነጣጥቀዋል። እነሆ፥ ግንቡ በወደቀ ጊዜ፥ የመረጋችሁት ጭቃ ወዴት አለ? አይሉአችሁምን? ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በመዓቴ በዐውሎ ነፋስ እሰነጣጥቀዋለሁ፥ ያጠፋውም ዘንድ በቍጣዬ የሚያሰጥም ዝናብ፥ በመዓቴም ታላቅ የበረዶ ድንጋይ ይወርዳል። ገለባም በሌለበት ጭቃ የመረጋችሁትን ቅጥር አፈርሳለሁ ወደ ምድርም እጥለዋለሁ፥ መሠረቱም ይታያል። እርሱም ይናዳል በመካከሉም ትጠፉላችሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ። መዓቴንም በግንቡ ላይ ገለባም በሌለበት ጭቃ በመረጉት ላይ እፈጽማለሁ እኔም፥ ግንቡና መራጊዎቹ የሉም እላችኋለሁ።

ገለባ ወይም ጭድ ሳይኖር በጭቃ መምረግ ይቻላል? (ወይም ገለባና ጭድ እና ጭቃ ለማታውቁ፥) ሲሚንቶ በሌለበት አሸዋ መግረፍ ይቻላል? በትክክል ይቻላል። ግን ያ ምርጊት ጊዜያዊ ብቻ ነው። ታላቅ መነቃቃት በነበረባቸው የብሉይ እና የአዲስ ኪዳን ዘመናትም እንኳ፥ እንዲሁም በታሪክ ውስጥ በታዩ መነቃቃቶች ውስጥ በወንጌልና በቅድስና ተግባር ላይ ያላተኮረ ትምህርት ሲሰጥ አልታየም። በኢዮስያስ ወይም በነህምያ ዘመን ስለነበረው መነቃቃት ብናጤን፥ ወይም መንፈስ ቅዱስ በወረደበት የሐዋርያት ዘመን ስለነበረው ብናይ፥ ወይም በተሃድሶው ዘመን፥ ወይም የታላቁ የመነቃቃት ዘመናት ስለሚባሉት፥ ወይም ስለ

[5] *እላይ የተጠቀሰው፤ ገጽ 2።*

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ © 2015
የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ። 2ጢሞ. 2፥15
ባለቤትነቱን ሳይውስዱ ማባዛትም ማደልም ይፈቀዳል።

አገራችን የመጀመሪያ የወንጌል አዝመራ ዘመናት ብንመረምር አገልጋዮቹ ጭድ በሌለው ጭቃ እንዳልመረጉ ማስተዋል አይሳነንም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው ነቢያት ቃሉን ሲገልጡ እንጂ ወደ መድረክ ሰውን ጠርተው ያንን ሰው ሲገልጡ፥ ወይም የአባት፥ የአያትና የምንጅላት ስም እየጠሩ 'የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ልክ ነህ' ሲባሉ አይደለም። በነገራችን ላይ፥ ይህ፥ 'የእግዚአብሔር ሰው' የሚለው አጠራር ቲ. ቢ. ጆሹዋና መሰል የዘመናችን ነቢያት ነን ባዮች እንዲጠሩበት የሚያደፋፍሩት ቃል ነው። ቃሉ በራሱ ምንም ችግር የለበትም፤ በብሉይ ኪዳን ሳሙኤል፥ ኤልያስ እና ኤልሳዕ ተጠርተውበታል። የሶምሶን ወላጆችም መልአኩን እንዲህ ጠርተዋል። ሙሴም ተጠርቷል ግን በእግዚአብሔር ባሪያነት ነው የሚታወቀው፤ በተለይ ከሞተ በኋላ በዘዳግም እና በኢያሱ መጻሕፍት፥ 'የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ' ነበር መጠሪያው። ነገር ግን፥ አንድን ሰው እንደ ማዕረግ አድርጎ 'የእግዚአብሔር ሰው' ማለት ሌላውን ወይም ራስን ከዚያ ያነሰ ማድረግ መሆኑ አይዘንጋን። እንዲህ ያለው የማበላለጥ ወይም የማወራረድ ተግባር የአዲስ ኪዳን ወይም የክርስቲያኖች ቋንቋ አይደለም። ይህ ሐረግ በአዲስ ኪዳን ሁለቴ የተጠቀሰ ሲሆን (1ጢሞ. 6፥11 እና 2ጢሞ. 3፥16-17) በተለይ ሁለተኛው፥ *የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።* ይላል። የእግዚአብሔር ሰው ማለት የክርስቲያን መጠሪያ እንጂ የ'ነቢያት' ማዕረግ አይደለም።

ይህ ከላይ ያነበብነው ዓይነት ለ'ነቢዩ' የተገለጠለት መረጃ ነገር እውነት ነው ቢባል **ምንጩ** ምን ሊሆን ይችላል? በጉባኤው ውስጥ የመደረጉ **ጥቅምስ** ምንድር ነው? ሁለቱንም እንይ።

ምንጩ?

ምንጩ ከነዚህ አንዱ ሊሆን ይችላል፤ አንደኛ፥ ከሰዎቹ ጋር ቀጥታ መመሳጠር ሊኖር ይችላል። ሁለተኛ፥ ሰዎቹ እነርሱ ሳያውቁ በቀጥታ ወይም በሌላ ሰው በኩል ያውቃቸዋል። ሦስተኛ፥ ያልተለመደ ርቆ የሄደ ስነ ልቡናዊ የአእምሮ ማንበብ ችሎታ ሊኖረው ይችላል። በስነ ልቡና ትምህርት ቋንቋ telepathy ይባላል። ይህንን ቃል እዚሁ አብራርቼው ልለፍ። ከሁለት የግሪክ ቃላት የተሠራ ነው፤ τῆλε (ቴሌ) ከሩቅ፥ ከርቀት ማለት ሲሆን πάθος (ፓቶስ) ይህኛው አንድ የአማርኛ አቻ ቃል የለውም፤ በጥቅሉ ስሜትን፥ እውቀትን፥ ልምምድን ጨምቆ የያዘ ቃል ነው።

ቴሌፓቲ በተለምዶ የታወቁ መስመሮችን ሳይጠቀም ከአንድ ሰው Psi ወይም parapsychology እና mind reading በሚሉት መንገድ ከርቀት የእውቀትን፥ የስሜትንና የልምምድ መረጃን መውሰድ ማለት ነው። ይህ ዘመናዊነትን ይላበስ እንጂ ከጥንቆላ ጋር የተቆራኘና አጋንንታዊ አሠራር ያለበትም ነው። ምክንያቱም፥ አንድ ማንም ሰው ስለ ሌላ ማንም ሰው የተዘረዘረ መረጃ ከሜዳ እንደሚታፈስ ነገር እንደማያፍስ 1ቆሮ. 2፥11 እንዲህ በማለት ይነግረናል፤ *በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም።* ይላል። እግዚአብሔር ሊያሳውቅስ አይችልም? የሚል ጥያቄ ሊነሣ ይችላል፤ ወደዚህኛው እመለሳለሁ። ግን ልንቀበለው የተገቡ ሁለት ትልልቅ እውነቶች አንድ ሰው የሌላውን አዕምሮአዊ ማንነት ሊመዘበር አለመቻሉና እግዚአብሔር የሰውን ገመና በመድረክ ላይ የሚያዝረከርክ አምላክ አለመሆኑ ናቸው።

አራተኛ፥ ከአጋንንት የመነጨ ስለ ሰዎቹ በመጠኑ የማወቅ ችሎታ ሊሆን ይችላል። ይህ ከላይ ከተጠቀሰው ከሦስተኛው ጋር የሚቀራረብ ነው። ሰይጣን እውቀቱ ውሱን ይሁን እንጂ ስለ ሰዎች የሚያውቀው እውቀት አለው። ይህንን እውቀት በአንድ መንገድ ወይም በሌላ፥ በቀጥታ ወይም የመንፈስ ቅዱስ እውቀት አስመስሎ ሊሸጥ ቢችል ማስገረም የለበትም። በተለይ ሰይጣን እያስመሰለ የሚያቀርባቸውን ሸቀጦች በውድ ዋጋ የሚገዙ ክርስቲያኖች የበዙበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። ይህ ከሆነ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመድረክ ላይ እየሠራ ያለ አጋንንታዊ አሠራር መኖሩ ሊስተዋልም ሊያስደነግጥም ይገባል። ሊኖር እንደሚችል መገመት ወይም አይኖርም ብሎ መደምደም የዋኅነት ነው። ይህ እንደሚሆን አስቀድሞ ተነግሮናልና አያስደንቅም።

አምስተኛ ብዬ የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ነው አላልኩም። ምክንያት አለኝ። ከቤት ቤት እየዞሩ ከጥንቆላ ያልተናነሰ ሥራ የሚሠሩና በዚህ የሚተዳደሩ የበዙበት ዘመን ላይ ደርሰናል። ከነዚህ ዘዋሪ ዘጋቢዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ለ'ነቢያቱ' እየቀረቡ ንግርት የተነገረባቸውና ከመድረክ የታወጀባቸው ጊዜያት በአገራችንም በምዕራቡም ዓለም ኖረው ያውቃሉ። አንወናበድ። በዚህ ዘመን የምንሰማቸውንና የምናያቸውን ምልክቶች ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ናቸው ብለን ከደምደምን ሰዎች ክርስትና አስነስተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያስገቡት ጥንቆላ ውስጥ እንገባለን።

ይህ ከላይ ያየነው ዓይነት አሠራር ቴሌፓቲያዊና ጥንቆላዊ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ የምንሄድበትን፥ የምናገለግልበትን ፊር የተለመልን መጽሐፍ ነው። አገልግሎት ምን መምሰል እንዳለበት የምናውቀው ቀድመውን ያገለገሉትን ነቢያትና ሐዋርያት (በቃሉ ውስጥ የተጻፉትን ማለቴ ነው) አገልግሎት መልክ በመመልከት ነው። ዛሬ ሙሴና ሳሙኤል ወይም ጳውሎስና በርናባስ ዛሬ ቢኖሩ የባልሽ ስም ጉብረ ጊዮርጊስ፥ የባልሽ ወንድም ጉብረ ክርስቶስ እያሉ አያፌዙም። የአገልግሎታቸው ትኩረትና ሚላማ የተገለጠ ነውና እንዲህ አይቀላምዱም።

ወደዚህ 'ነቢይ' ስንመጣ ግን፥ እንግዳ ነገሮችን ይነግረናል። እነዚህን የሰዎች ምስጢሮች ስለሚያውቅበት ምንጭ ሲናገር አጠገቡ ያለ ዳመና መረጃ እንደሚሰጠው ይነግረናል። ወደዚህ አሳብ ከታች እመለሳለሁ። ይህ ብቻ ሳይሆን "በጾም ፀሎቱ መካከል የእግዚአብሔር መልአክ የሆኑ ሰዎች ይመግቡታል።" 'መልአክ የሆኑ ሰዎች' ማለት ምንድርነው? አልገለጠውም። ሰዎቹ መልአክ ሆነዋል? ወይስ መላእክቱ ሰዎች ሆነዋል? ወይስ ይህ አባባል የሰዎቹን መልካምነት በኢጋኖ ለመናገር ነው? አገላለጡ ግን እንደዚያ አይመስልም።

> ለሊት ለሊት ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ አንድ ሰው ቢያነስ ለአንድ ዓመት ያህል ፍትፍት በሰሃን እያመጣ ይመግበኝ ነበር። ያንን ሰው እጁን እንጂ አካሉን አላይም ነበር። በመጀመሪያ ሰሞን ህልም ይመስለኝ ነበር። ኋላ ግን በእርግጥ እውን እንደሆነ ያረጋገጥኩት ጠግቤ ከእጁ ከበላሁ በኋላ ውሃ እጠጣና አጎሳ ነበር። ያ እጅ በዛ የርሃብ ዘመኔ ያለማንም እርዳታ ራሱ እያነረሰኝ የርሃብ ዘመኔን አሻግሮኛል።

ይላል። እጁ ብቻ የሚታይ ሰው ማለት ምንድር ነው? ይህ ነገር ሰው ባይሆንስ? ሰው መሆኑ በምን ይታወቃል? ይህ ለ5 ዓመታት የሆነ ነው።[6] የማን መሆኑ የማይታወቅ እጅ ስላቀረበ የቀረበው ነገር በሙሉ የጌታ ነው ተብሎ መበላት አለበት?

ይህ ከማይታይ እጅ መብላት የዘመናችንም ትክክለኛ ምልክታዊ ምሳሌ ነው። ከመድረክ ላይ ምንም ነገር ይቅረብ፥ ይህ የማን ትምህርት ነው? ከየት የመነጨ ነው? ያቀበለው እጅ የማን ነው? ሳይባል እጅ ብቻ ታይቶ ትምህርቱ ሁሉ፥ ልምምዱ ሁሉ አፈፍ የሚደርግበት ዘመን ላይ ደርሰናል። ሰዎች ከመድረክ ላይ የሚነገረውን ትንቢት ሁሉ እየበሉ ማግሳትን ተያይዘውታል። ማግሳታቸውንም የምግቡ እውነትነት ማረጋገጫ እያደረጉ ናቸው። መታየት ያለበት ነገር፥ የሚያቀብለው እጅ እጅ መሆኑ ሳይሆን የማን እጅ መሆኑ ነው። ትምህርት ብቻ ሳይሆን የማን ትምህርት ነው? ከሰውና ከቴሌቪዥን የተኮረጀ ነው? ወይስ የመጽሐፍ ቅዱስ ነው? ምንጩ የት ነው? የሚለው ነው። መድረኩ ላይ

---

[6] *እላይ የተጠቀሰው፤ ገጽ 5። እንዲሁም፥ http://www.prophetbelay.com/index.php/about-us/about-prophet-belay*

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ © 2015

ሳይሆን ከመጋረጃው በኋላ ያለው ማን ነው? ብሎ መጠየቅ አጉል ደፋርነት አይደለም። ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ መኖር አለበት።

በዚህ ዘመን የሞተ ሰውን የሚያናግርን ወይም የሞተ ሰው መልስ የሚሰጠውን አገልጋይ ብንሰማ ምን እንል ይሆን? እርግጠኛ ነኝ በቂ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ባይኖረንም እንኳ ብዙዎቻችን፥ 'ይህማ ሙታን ሳቢነት ነው እንጂ ሌላ ምን ይሆናል?' እንላለን። ዘዳ. 18 ውስጥ *ያለው አሰማጭንም፥ መተተኛንም፥ በድግምት የሚጠነቀኘልም፥ መናፍስትንም የሚጠራ፥ ጠንቋይም፥ ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ።* የሚለው ቃል ሳይታሰበን አይቀርም። ይህ 'ነቢይ' የሞተ ሰውንም ካናገረና የሞተው ሰውም ከተናገረውና መልስ ከሰጠውስ? ሌላ ሴትን ወደ መድረክ አውጥቶ ከተናገረው ደግሞ ይህ ይቀነጨባል፤

ነቢይ በላይ፡- ሌላም ዘመድሽን አየሁ። ዳንኤል ይባላል። እርሱም ተመሳሳይ ህመም አለበት።
ሴቲቱ፡-አዎን የእግዚአብሔር ሰው
ነቢይ በላይ፡- በመንፈስ ሳሎኑን ዘልቄ ወደ መኝታ ክፍልሽ ገባሁ። የባለቤትሽን ፎቶ አየሁ። የባለቤትሽ ፎቶ የሚገኘው በመኝታ አልጋሽ አጠገብ ነው።
ሴቲቱ፡-አዎን የእግዚአብሔር ሰው ፍጹም ትክክል ነው።
ነቢይ በላይ፡- ያንን የባለቤትሽን ፎቶግራፍ አነጋገርኩት። ‹‹አንተ የት ነው ያለኸው?›› አልኩት። እርሱምእንዲህ ሲል መለሰልኝ ‹‹እኔ እኮ ሞቻለሁ›› አለኝ።

ሙታንን ማነጋገር የሚችል ማን ነው? በመንፈሱ ዘልቆ ነው ወደ መኝታ ክፍል የገባውና ፎቶውን ወይም ሙቱን የሚያናግረው በመንፈስ ነው ማለት ነው። መቼም የሞተ ስለማይናገር በወረቀትና መስታወት የተሠራ ፍሬም፥ 'እኔ እኮ ሞቻለሁ' አይልም። ሕይወት የሌለው ግዑዝ መጀመሪያውኑ አይሞትምና ሙት ተብሎም ሊጠራ አይችልም። ይህ ስዕል ተናገረ ማለት ተአምረ ማርያም ውስጥ እንዳለው፥ የማርያም ስዕል ድምጽ አውጥታ ተናገረች፥ አለቀሰች፥ ደማች እንደሚባለው ከተረትም የወረደ ነገር ውስጥ መዝቀጥ ነው። ወረቀቱ ካልተናገረ ደግሞ የሞተው ሰው ተናግሮታል ማለት ነው። ይህ ሙታንን ማነጋገር ከአጋንንት ጋር የተቆራኘ መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ የሚያስተምረውና ከቶም እንዳይደረግ የተከለከለው ሙታን ሳቢነት ነው። እንደዚህ ያሉ ነገሮችን በግልጽ የሚናገር ሰውን 'የእግዚአብሔር ሰው' እያሉ ማሞካሸትን ምን ይሉታል? ይህ እኮ ሊያስደነግጥና ሊያስጠረጥር የተገባው ጉዳይ ነው። ይህ የሰዎችን ስምና ምስጢር የሚያውቅ ሙታንንም የሚያናግር 'ነቢይ' ምንጩ ምንድር ነው?

ተናጋሪው በተደረገለት ቃለ መጠይቅ ላይ ይህ የሰዎች ምስጢር እንዴት እንደሚታወቀው ሲናገር፥ አንዳንድ ጊዜ ድምጽ እንደሚሰማ፥ አንዳንዱ ድምጽ በጆሮ የሚሰማው፥ ሌላው በልቡ የሚሰማው መሆኑን ከዘረዘረ በኋላ፥

> *ሌላኛው ግን በጣም በአብዛኛው የሚነግረኝ አጠገቤ ዳመና ቆሞ ነው። በቁመቴ ልክ የሚቆም ዳመና አለ፤ በጣም፥ መዓዛው በጣም ነው ደስ የሚለው፤ እና፥ አንዳንድ ጊዜ እራሱ እንትን አያልኩኝ መጨበጥ እፈልጋለሁ እንደዚህ! ግን አልችልም። እሱ ሲሄድ ነው ምሄደው፤ ከፊቴ ሲሄድ እሄዳለሁ እከተለዋለሁ፤ ጎኔ ላይ ይቆማል፤ ሰው አስመጥቼ አሁን መልክት ስናገር አሁን አጠገቤ ቆሞ ነው ሚነግረኝ፤ ሙሉ መረጃ ያወራልኛል።*

ብሏል።[7] ይህ ሙሉ መረጃ የሚሰጥ በቁመቱ ልክ የሆነ ዳመና ከዳመናነቱና ሙሉ መረጃ የሚያወራ ከመሆኑ በቀር ማንነቱ ወይም ምንነቱ አልተነገረም። ይህ ዳመና የተባለው ማን ወይም ምን የሚሉት ደመና ነው? ይህ የዚህ ነገር ምንነት መጠየቅና ከቃሉ አንጻር መፈተሽ የለበትም? ወይስ ክርስቲያን ሁሉ የሚሆነውን ምልክትና ምትሃት ሁሉ የእግዚአብሔር አሠራር ነው ብሎ በየዋህነት ብቻ መግጋት አለበት?

ቀደም ብዬ እንዳልኩት፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የቀደሙት ቅዱሳን አገልግለው የሄዱበትን ፈር ተከትለን እንድናገለግል ፈር ቀድደውልናል። እንዲህ ያለ ነገር ከመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት ውስጥ ለማን እየታየ የዘመድና የአማቾች ስምና ምስጢር እየተናገረ ነቢይነቱን ማረጋገጫ አደረገ? ብለን ብንጠይቅ አንድም ምሳሌ አናገኝም። የተጻፈው ሁሉ ለከንቱ ሳይሆን ለትምህርታችን ከተጻፈልን ከሕይወታቸውና ከአገልግሎታቸው ልንማርና ልንመስላቸው ይገባናል እንጂ የገዛ ቀዳዳቸውን ቀድደው በቀላሉ የሚወናበዱ ሰዎችን አስከትለው መንጎድ እንደ ዘበት የመሰላቸው ሰዎች በሚሸነቁሩት ሸንቁር ሾልከን መውጣት የተገባ አይደለም።

የዕውር መሪና የጋዜጣ ስነ መለኮት

ዛሬ መሠረታዊ የክርስትና ትምህርትና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሳይማሩ የሚያስተምሩ ብቻ ሳይሆኑ ራሳቸውን እንደ ስነ መለኮት ሊቅ የሚቆጥሩ የተደናገሩ ሰዎች እያደናገሩ ይገኛሉ። ከዘመናችን 'ነቢያት' የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብተው የተማሩ እንዳሉ እስታቲስቲክስ የለኝም። የተማሩ አለመሆናቸውን ግን ከሚያስተምሩት ሰምቶ መናገር ይቻላል። ይህኛው 'ነቢይ' ታሽቶሎጂ በሚባል ኮርስ ከመንፈስ ቅዱስ ኮሌጅ መመረቁን ተናግሯል፤ የመጽሔቱ ዘጋቢም ጽፎለታል። ዶሮን ሲያታልሏት እንደሚሉት ነው? ወይስ አንባቢዎችን ሲያታልለን መሆኑ ግልጽ አይደለም? በዚህ ዘመን፥ ያውም በዚህ ዘመን ላለመማር አእምሮን ዘግቶ መቆለፍና ሌሎችም ቃሉን እንዳይማሩና እንዳይመረምሩ ማድረግ ከሰነፍም የማይጠበቅ ነው። እነዚህ ያልተማሩ አስተማሪዎች ከእነርሱ የባሱ ዕውሮችን የሚመሩ ዕውሮች ናቸው።

በ2008 በአትላንታ ዕውሮችን መረዳት ወይም ስለ ዕውሮች ግንዛቤ ማግኘት ይቻል ዘንድ ፈቃደኛ ሰዎች ለአንድ ሰዓት ፈቃደኛ ዕውር ሆነው ዓይናቸው ሙሉ በሙሉ ተሸፍኖ በከተማው የተለያዩ ክፍሎች ይመላለሱ ነበር። መሪዎቻቸውን አንዳንድ ጥያቄ ከመጠየቅ በቀር ጭላንጭል እንኳ እንዲያዩ አይፈቀድም። ጉዞአቸውን ጨርሰው ከተመለሱ በኋላ የዓይናቸው ሽፋን ሲነሣ ነው ይመራቸው የነበረው ሰው ራሱ ዓይነ ስውር መሆኑን የሚያውቁት። ይህ ማለት መሪው ሰው ከተመሪው የተሻለ ምንም የማያይ የመሆኑ ገላጭ ነው። ይህን የዕውር ዕውርን መምራት ቃል መጀመሪያ የተናገረው ጌታ ነው፤ ማቴ. 15፥14። ይህ ዕውርነት የዓይን ዕውርነት የልቡና ስውርነት ነው።



ራሳቸውን እንደ አላዋቂ ከቶም ሳያዩ እንደ ሊቅ ሊቆጥሩ መሞከራቸው ሊያስገርም አይገባም። አለመማርን በመማር ሊለውጡና ሊያሸንፉት ይቻላል። የመምሰልን ድፍረት ግን በመማርም መለወጥ አይቻልም። ከዓመታት በፊት በአንዲት በማገለግልባት ቤተ ክርስቲያን የነበረች እኅት እንማርበት በነበረ አንድ ርእስ ላይ ተከራክራ፥ ተከራክራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማሳመኛ ቃልና ለምትለው ነገር ማስረጃ ስታጣ፥ "ይሄ ቲዮሎጂ ነው፤ ማንም እኮ ቲዮሎጂ ሊኖረው ይችላል፤ ማንም ሰው ቲዮሎጂያን ነው።" አለች። እኔም፥ "በመጠኑ ልክ ነሽ፥ ግን ቲዮሎጂው ከየት ነው የሚመጣው? ከመጽሐፍ ቅዱስ ወይስ ከጋዜጣ?" አልኳት። ከመጽሐፍ ቅዱስ ካልወጣ ከጋዜጣ መሆኑ አይቀርም። ዛሬም የጋዜጣ ስነ መለኮታውያን ድምጻቸው አጉል ጎልቶ እየወጣ ይገኛል። አጉሉ ነገር ጉልህ አወጣጡ ብቻ ሳይሆን ትምህርቱና ድርጊቱ፥ ውጤቱና መዘዙም ጭምር ነው። እንደ አንዳንድ መድኃኒቶች የጎን ጠንቆቹም ብዙ ናቸው።

አስተምህሮታዊ፥ ስነ መለኮታዊ ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ የትምህርት ጤንነት ላይ ትኩረት ማድረግን አጥብቀው የሚሸሹ አከርካሪ የሌላቸው መሪዎች ቁጥርም እየጨመረ ነው። አንዳንዶቹ ራሳቸውም ያልተማሩና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ጊዜ የሚያሳልፉ ስላልሆኑ ነው። ሌሎቹ ግን ስነ መለኮት አስፈላጊ ሳይሆን አላስፈላጊ፥ ተግባራዊ ሳይሆን ንድፈ አሳባዊ፥ አንድ የሚያደርግ ሳይሆን የሚለያይ፥ የሚታወቅ ሳይሆን እርግጠኛ

[7] https://www.youtube.com/watch?v=3-cUGeqeiFs

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2015

ሆነው ጠንቅቀው የማያውቁት ረቂቅ፥ መንፈሳዊ ሳይሆን መንፈሳዊነት የሌለበት አእምሮአዊ ብቻ ስለሚመስላቸው ነው። በእውነት ግን ስነ መለኮት አላስፈላጊ ቢሆን ጳውሎስ እንደ ሮሜ፥ ኤፌሶን፥ ቆላስይስ ያሉትን መልእክቶች ባልጻፈም ነበር። ደግሞም ስነ መለኮት ተነድፎ የተቀመጠ ንድፍ ሳይሆን ተመርምሮ የሚታወቅ ትምህርት ነው። ስነ መለኮት አይለያይም፤ ከለያየ የሚለየው ስነ መለኮትን ፈርተው የሚሸሹ ጥራዝ ነጠቆችን እንጂ መርምረው የሚነጋገሩበትን አይደለም። ይህ ደግሞ መለየት አይባልም፤ ቀድሞውኑ ፈርተው ሸሹ እንጂ ወደ መድረክ አልመጡምና። ስነ መለኮት ተግባራዊ ነው፤ ችግሮቹ ተግባራዊ ከሆኑ መፍትሔዎቹ እንዴት ተግባራዊ አይሆኑም? ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይሁን ማለትና ማድረግ ተግባራዊ ነው። ስሕተትን ማመልከትና እንከንን ማጥራት ተግባር ነው። ስነ መለኮት መንፈሳዊነት እንደሌለበት የሚያስቡ መንፈሳዊነትን አእምሮን ከመጠቀም የገነጠሉ ናቸው። ስነ መለኮት የማይታወቅ፥ ረቂቅ ነው የሚሉ ጊዜ ወስዶ ቀምሞ ከማብሰል እንደ በሶ በጥብጦ መጠጣትና መጋት የሚፈልጉ ናቸው።

ስለዚህ ዛሬ የተበላሸ ነገር በቤተ ክርስቲያን መድረክ ላይ እየተዝረከረከ ሲታይ ዝምታ ታለፈና ማጨብጨብ እየተለመደ ነው። ብዙ አማኞች የእግዚአብሔርን ቃል ካለማወቃቸው የተነሣ፥ በሥርዓትም ካለመማራቸው የተነሣ እውነትንና ስሕተትን መለየት አይችሉም። ስለዚህ ሁሉ እውነትና የእግዚአብሔር እየመሰላቸው በመደነቅ ያጨበጭባሉ። ምልክትና ተአምራት ሁሉ ከጌታ የተደረገ ይመስላቸዋል። የመጨረሻው ዘመን ምልክት ተብሎ በግልጽ የተነገረን ነገር በክርስቶስ ስምና በኢጋንንታዊ ምትሐት የሚደረጉ ድንቅና ተአምራት እንዲሁም የስሕተት ትምህርቶችና አሳች ሰዎች ናቸው። ሰይጣን የሚሠራቸው ምልክቶች እኮ ጌታ ከሚሠራቸው ከውጪ ሲታዩ ልዩነት የላቸውም። ልዩነቱ ምንጩ ነው። በምልክቶች ምልክትነት ብቻ ለሚወናበድ መንጋ ምልክቶች በቀላሉ ተብትበው የሚጎትቱ ገመዶች ናቸው። ሙሴ በትሩን ሲጥል እባብ ሆነች፤ ኢያኔስና ኢያንበሬስም ያንኑ አደረጉ። ተመሳሳይ ነው። ውኃውንም ደም አድርገዋል። ጓጉንቸሮችንም ቅማልንም አውጥተዋል።

ያደረጉት ድርጊት ተመሳሳይ ነው። አድራጊዎቹ ግን የተለያዩ ናቸው። *ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ* ማቴ. 24፥24። ምልክትና ድንቆች የነቢይነትና የሐዋርያነት ብቸኛ ምልክቶች አይደሉም። ምልክት አይተው ግራ ለሚጋቡ ወይም ለሚከተሉ ሰይጣን ምልክቶችን በገፍ እየፈበረከ ሊያቀርብ ምንም አይሳነውም፤ ችሎታው አለው፤ ፋብሪካውም አለው። ሰይጣን የመንፈስ ፍሬን ነው ማፍራት የማይችለው እንጂ ተአምራትና ድንቆችን መሥራት ይችላል። ሰይጣን የጸጋ ስጦታ የሚመስሉ የተጭበረበሩ ልምምዶችንም በገፍ በማምረትም ብቻውን ያለ ጨረታ ያሸነፈና ተወዳዳሪ የሌለው ነው። ሰይጣን ራሱን እንደ ብርሃን መልአክ አድርጎ፥ አገልጋዮቹን ደግሞ የጽድቅ አገልጋዮች አስመስሎ ወደ መድረክና ወደ ምስባክ መውጣትና ማውጣት ይችላል። በተለይ በዘመን መጨረሻ ያለን እኛ ይህንን እየሰማንና እያየንም ነን።

ጥቅሙስ?

ይህን ያህል በምንጩ ላይ ካልኩ ወደ ሁለተኛው ነጥብ ልምጣ። የዚህ ነገር **ጥቅሙስ** ምንድርነው? የጸጋ ስጦታዎች የተሰጡት ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ነው። ይህ 'ነቢይ' አንዲትን ሴት ወደ መድረክ ጠርቶ ዘመዶቿንና ምስጢሯን መናገሩ ቤተ ክርስቲያንን የሚያንጸው ከቶ እንዴት ነው? ቲ. ቢ፣ ጆሹዋ አንድ የእግር ኳስ ቡድን እንደሚያሸንፍ ወይም አንድ ታዋቂ [ዘፋኝ] እንደሚሞት የተነበየውን ከዚህ ቀደም እንደጠቀስኩት ማለት ነው። ማይክል ጃክሰን መሞቱ ወይም የማንችስተር ቡድን ማሸነፉ ቤተ ክርስቲያንን የሚያንጽበት ምንም ነገር የለም። የሰውየው ትከሻ ላይ ኮከብ ከመጨመሩ ሌላ ማለት ነው።

የአንዲት ሴት ወደ መድረክ ተጠርታ ወጥታ የዘመዶቿ ስምና ገመና መነገሩ በዚያ ለታደመው ጉባኤ የሚፈይደው ከሌለ፥ ቤተ ክርስቲያንን የሚያንጸውና የሚገነባበት መንገድም ከሌለ፥ ጥቅም ቢኖረውና ጥቅሙም ለሴቲቱ ከሆነ የጉባኤው ስሜትና ጊዜ መወሰዱ ለምን አስፈለገ? እንደ አንድ ታዛቢ ብናስተውል ጥቂት ነገሮችን እርግጠኛ ሆነን መናገር እንችላለን። እነዚያም፥ <u>አንደኛ፥</u> በዚያ ድራማ ውስጥ የታየው ነገር ሁሉ 'ነቢዩን' የሚያነሳ፥ ደማቂና ተደናቂ የሚያደርግ ነገር መሆኑ፤ <u>ሁለተኛ፥</u> ማኅበረ ምእመናኑን ወይም ቤተ ክርስቲያንን ከቶም የሚያንጽ ነገር አለመኖሩ፤ <u>ሦስተኛ፥</u> ክርስቶስ አለመታየቱ ናቸው። እነዚህ ቪድዮዎች ተመልካች ቀድቶ ስሕተትን ሊገልጥ የለጠፋቸው ሳይሆኑ በአዘጋጁ ክፍል በጥንቃቄ ተሠርተው ሌሎችን ለማስተማር ወይም ለማስተዋወቅ ሲባል ወደ አየር የተላኩ ናቸው።

ለክርስቲያኑ ማኅበረ ሰብ የዚህ ፋይዳው ምንድር ነው? ጸጋ የተሰጠው ለማኅበር እነጻ እንጂ ለእዩኝ እወቁኝ አለመሆኑ ለምን አይገባንም? ከላይ በጠቀስኩት ቃለ መጠይቅ ይህ ሰው ለምን ይህን እንደሚያደርግና ጥቅሙስ ምን ስለመሆኑ ተጠይቆ ሲመልስ፥ ስም የመጥራቱ ጥቅም አንድ ሰው በጉባኤ ውስጥ ቢኖር ያንን ሰው ብቻ ሳይሆን የዘመዶቹንም ማንነት ነግሮ 'ኬዛቸውን' መንገሩ እነሱንም ማገልገል ነው ብሎ፥ "እኔ ስጸልይለት የሱን ፋሚሊ ስም ከነገርኩት፥ የሱን ስም ከነገርኩት፥ ቤተ ሰቡን ከነገርኩት፥ ጓደኞቹን ከነገርኩት፥ <u>እግዚአብሔርን ከማመን በላይ፥ በወቅቱ የሚገለጠውን የጸጋ ስጦታ ከማመን በላይ እንዲያምኑና</u> ተጠቃሚ እንዲሆን ነው።" ብሎአል።[8] የጉባኤው ድራማ ምክንያቱ እንግዲህ ይህ ነው። እግዚአብሔርን ከማመን በላይ እና የሚገለጠውን የጸጋ ስጦታ ከማመን በላይ ማመን ሲባል እምነትን በነቢዩ ቃል ላይ ማድረግ ይመስላል። ይህ የቃል-እምነት ትምህርት ነው። እምነት በጌታ ላይ ነው ወይስ በቃሉና በስጦታው ላይ ነው መሆን ያለበት?

አንዳንዶች ይህንን ምስጢር የማወቅ ነገር 'የመገለጥ ስጦታ' ብለውታል። እንደዚህ የተባለ ስጦታ ያለ ይመስል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የጸጋ ስጦታዎች በተዘረዘሩባቸው ምዕራፎች (ሮሜ. 12፤ ኤፌ. 4፤ 1ቆሮ. 12፤ 1ጴጥ. 4) መገለጥ የተሰኘ ስጦታ የለም። ከቃሉ ጋር የሚቀራረበው ይህ መገለጥ የተጠቀሰው በ1ቆሮ. 14፥29-30 ነው። ይህም ስለማን እንደሚናገር በቦታው ስናይ ከአንድ በላይ ሆነው በልሳን ስለሚናገሩ ሰዎች ከተናገረ በኋላ ከአንድ በላይ ሆነው ትንቢትን ስለሚናገሩ ነቢያት በተናገረበት ቦታ ነው። *ነቢያትም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ ሌሎችም ይለዩአቸው፤ በዚያ ለሚቀመጥ ለሌላ ግን አንድ ነገር ቢገለጥለት ፊተኛው ዝም ይበል* ይላል። እነዚህ ሰዎች በጉባኤው ያሉ ሰዎች ሲሆኑ የሚናገሩትን ነገር የሚለዩትም (ይለዩአቸው የሚላቸው) እዚያው ያሉቱ ናቸው። እንጂ መገለጥ የሚባል ስጦታ የለም። ሲሉ ሰምተን ወይም ተነግሮን፥ 'እገሌ በመገለጥ የሚያገለግል አገልጋይ' የምንለውም እኛ ነን እንጂ ቃሉ አይደለም።

እንደዚህ የሚያስቡ ክርስቲያኖች፥ ማለት፥ የመገለጥ ስጦታ የሚሉት ነገር ያለ የሚመስላቸው ሰዎች፥ እነዚያ ይህ ስጦታ ያላቸው ሰዎች የሰዎችን ምስጢርና ገመና ገላልጦ የሚያዩበት መነጽረ-መለኮት የተገጠመላቸው ሰዎች እንደሆኑም ይገምታሉ። አንዳንዶቹ፥ 'ከመቼው አጋለጠኝ' ብለውም ይፈራሉ። ከፈሩ ቀድሞውኑ አውቀውታል፤ ካወቁ፥ ላሳወቃቸው መንፈስ ቅዱስ አክብሮትን አቅርበው በጸጸት መመለስ ነበረባቸው እንጂ ያን ሰውረው ልባቸው እየመታ ለፍተሻ መቅረብ አልነበረባቸውም።

መገለጥ የሚለውን ቃል ሐዋርያው ጳውሎስ በሁለት አቅጣጫ ተጠቅሞበታል። አንዱ የክርስቶስን መምጣት በተመለከተ ሲሆን ሁለተኛውን ጳውሎስ የተረዳውን ሰማያዊ ምስጢር ለመግለጥ ነው። ይህኛው ጳውሎስ የሚናገረው መገለጥ ምስጢር ሆነው ኖረው ኋላ የታወቁትን የክርስቶስን ማንነት፥ እግዚአብሔርንና የማዳኑን እውነትና

[8] *ከላይ የተጠቀሰው።*

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2015
የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ። 2ጢሞ. 2፥15
ባለቤትነቱን ሳይውስዱ
ማባዛትም ማደልም ይፈቀዳል።

መንገድ ጠንቅቆ መረዳትን ነው። ይህንን መረዳት ቅዱሳኑ ሁሉ እንዲካፈሉትም ጸልዮአል፤ ኤፌ. 1፥17-19። በ2ቆሮ. 12፥1-7 ስለ ግል ልምምዱም ተናግሮአል። ታዲያ ይህ ሰማያዊ ምስጢር እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን የማዳኑን እውነትና መንገድ መረዳትን እንጂ የሰውን ገመና ማወቅ አይደለም።

አሃ!? በአዲስ ኪዳን ጴጥሮስ የሐናንያንና የሰጲራን ምስጢር ማወቁስ? ጴጥሮስ ብቻ ሳይሆን ከብሉይ ኪዳን ኤልሳዕም ሰዎች በስሜት ሕዋሳት ብቻ ሊያውቋቸው የማይችሉ ነገሮችን ሲያውቅ እናስተውላለን። ኤልሳዕን ብናጤን፥ ለምሳሌ፥ ሎሌው ግያዝ በምስጢር ከሶርያዊው ንዕማን ገንዘብና ልብስ ሲወስድ በዓይኖቹ ሳያይ አይቶአል፤ 2ነገ. 5፥20-27፤ ሶርያውያን የተደበቁበትን ቦታ ለእስራኤል ንጉሥ ይጠቁም ነበር፤ 6፥8-12፤ የከበበውን የማይታይ ሠራዊት አይቶ ነበር፤ ቁ. 16-17። እነዚህ በእግዚአብሔር ላይ ወይም በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ የተቃጡ ጥፋቶች ናቸው። በምንም መንገድ ለራሱ ስም መደነቂያ ያደረጋቸው አይደሉም። ከላይ እንዳየነው፥ *ጳንጥ ጳናት በእርግጥም የእግዚአብሔር ነቢይ እንደሆንኩኝ እንድታውቂ የባለቤትሽን ኢሀት ስም ልንገርሽ?* ብሎ የመታወቂያ ወረቀት እንዳደረገው አላደረጉም።

ወደ ጴጥሮስ ስንመጣ፥ ይህ የጴጥሮስ እውቀት እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን ውስጥ ለሕዝቡ መታነጽ ካደረጋቸው ያልተደገሙ ነገሮች አንዱ ነው። ይህ የጴጥሮስ ድርጊት ከዘመናችን 'መገለጦች' በብዙ የተለየ ስለመሆኑ ከአራት አቅጣጫዎች እንይ።

- አንደኛው <u>ድርጊቱ</u> ራሱ ነው። ጴጥሮስ ይህንን ነገር ቀጥሎ ቀጥሎ፥ ደግሞ ደጋግሞ ሲያደርግ አይታይም። ከዚህ አንድ ቦታ በቀር ሌላ ቦታና ሌላ ጊዜ ይህን አላደረገም። ስለዚህ ይህ የጸጋ ስጦታ ሳይሆን እግዚአብሔር በጊዜው ለአንድ ግብና ዓላማ የከሰተው ነገር ነው። ዛሬ ይህን መሳዩ ምስጢር የመግለጥ ጉዳይ የጸጋ ስጦታ እስኪመስል ድረስ በአንድ ጉባኤ ውስጥም እንኳ በየሳምንቱ፥ ምናልባት ከዚያም በላይ ይደርጋል። የሚገለጡት ጉዳዮች ከቤተ ክርስቲያን ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው የስም፥ የስልክ ቁጥር፥ ወዘተ፥ ነገሮች መሆናቸውም ሳይዘነጋ ነው። የነሐናንያ ድርጊት ተራ ቅጥፈት ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ላይ፥ በእግዚአብሔር ላይ የተቃጣ ሴራና ደባ ነው። ይህ የክብደቱን ያህል፥ በስውርነቱ ልክ ወደ ሜዳ መውጣት ነበረበት።

- ሁለተኛው <u>ተቀባዩ</u> ነው። ጴጥሮስ ይህንን ነገር በቀጥታ የተናገረው ለማን ነው? በመጀመሪያ ራሱን ሐናንያን ነው የጠየቀው። "ሰላም ራሷን ሰጲራን ነው የጠየቃት። የጅምላ ርችት አልተኮሰም። "እዚህ ጉባኤ ውስጥ እርስትህን ሸጠህ ግማሽ ገንዘብ እቤትህ ደብቀህ የመጣህ . . ." አላለም። የኛዎቹ የ'መገለጥ' አገልጋዮች ርችት አርከፍካፊዎች እየሆኑ አንድ ሰው ለመጠቆም ሲሉ ጉባኤውን የሚያንገላቱ መሆናቸውን መረዳት ብዙ ምርምር የሚጠይቅ አይደለም። የአሁኖቹ ስም መጥራት ሲጀምሩም ይህ የጅምላ ተኩስ 'የመገለጥ አገልጋዮቻችን' ዋና መታወቂያ ነው።

- ሦስተኛው <u>ግቡ</u> ነው። በዚህ በነሐናንያ ሥራ ውስጥ የሰይጣን እጅ አለበት፤ መንፈስ ቅዱስን የመዋሸት ነገር አለበት፤ በእግዚአብሔር ላይ የተቃጣና የተሰነዘረ መሳሪያ አለ። ገና የተወለደች ጨቅላ ቤተ ክርስቲያን ከክፉ ንዋያዊ እርሾ መጠበቅ አለባት። ስለዚህ ይህ ጉዳይ ስር ሳይሰድድ መቀጨት ነበረበት። ይህን መሳይ የወቀሳ፥ የተግሳጽ፥ ኃጢአትን የመንቀስ፥ ትምህርት ከመድረክ አይሰማም። ከላይ እንደተባለው በነቢያቱ ኃይል ኃጢአት ተሸንፎ ወይም ዘማሪው እንዳለው ሰይጣን ከአገር ተባርሮ ስለሆነ ይሆን?

- አራተኛ፥ <u>ዓላማው</u> ነው። ምን ነበር? ሐዋ. 5፥11 እንደሚለን፥ *በቤተ ክርስቲያን ሁሉና ይህንም በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ።* በቤተ ክርስቲያንም፥ ከቤተ ክርስቲያን ባሻገርም ፍርሃት። እንዲያው ድንጋጤ አይደለም። አክብሮት ያለበት ፍርሃት ነው። አከታትዬ ካየኋቸው የዚህ ሰውና ሌሎችም በርካታ የዘንድሮ 'ነቢያት' ግርግሮች ውስጥ በሰሙት ሁሉ ላይ ፍርሃትን የሚፈጥር ነገር አላየሁም። በሰሙት ሁሉ ላይ የሚለው ቃል ክርስቲያኖችን ብቻ የተመለከተ ሳይሆን ያኔ የማያምኑትን አሕዛብና ሃይማኖተኛ አይሁድንም የጨመረ ቃል ነው። ዛሬስ? ዛሬማ ቤተ ክርስቲያን በዘንድሮ 'ነቢያት' ማላገጫ እየሆነች ናት። አክብሮትን የተላበሰ ፍርሃት ቀርቶ በወጉ ደንግጦና ሰግጠጥ ማለት እንኳ ተባርሮ እየጠፋ ነው።

ይህን እየጻፍኩ ሳለሁ (በማርች 2015 አጋማሽ) በቤተ ሰብ ጉዳይ ምክንያት ናዝሬት ቆይቶ የተመለሰ ጓደኛዬ፥ ልክ ከሁለት ወር በፊት እዚያ ስለተደረገ የሌላ የአንድ 'ነቢይ' ድርጊት አጫወተኝ። ይህኛው 'ነቢይ' የሞተና የተቀበረ አንድ ሰውን ጌታችን አልዓዛርን እንዳስነሣው ከሙታን ለማንሣት በመሞከር ከአንድ ጉባኤ ሕዝብ ጋር በተቀበረ በ3ኛው ቀን (3ኛ ቀን! እንደ አልዓዛር 4ኛ ቀን አይደለም) መቃብር አስቆፍሮ፥ ሳጥን አስከፍቶ፥ ሬሳ አስወጥቶ፥ መነሣቱን ለማረጋገጥ ወደ ሆስፒታል አስወሰደ። 'ከተነሣ ለምን እራሱ ተነሥቶ አልሄደም? ለምን ወደ ሆስፒታል አመጣችሁት?' ነበር የዶክተሩ ጥያቄ። የፌዝና የምጸት ጥያቄ ነበረ። በመጨረሻ ፖሊስ ተጠርቶ ኖሮ ጣልቃ ገብቶ ሬሳው ከመቃብር ሲወጣና ሳይነሣ ሲቀር አፍረው ተበታትነው ነበርና ያጀቡት ጥቂት አጃቢዎችና ነቢዩ በግዴታ መልሰው እንዲቀብሩት ተደርገዋል።

በሌላው አገር ይህ ድርጊት ሬሳ በመረበሽ ወንጀል የሚያስከስስ እና የሚያስቀጣ ነው። ደህና፥ ከሱና ቅጣቱ ቢቀር የከርስትናና የከርስቶስ ስም መጉደፍ እንደምን ዝም ይባላል? አንዴ የሞተ ሰውን ሁለቴ የሚቀብሩ አሳፋሪ ጉዶች! ያሳፍራሉ እንጂ የሚያፍሩ ግን አይመስሉም። ከዚህ በፊትም አንሞትም ይሉ የነበሩ ሰዎች ቤትና አገልግሎት ውስጥ ሞት ገብቶ ሲደነግጡና መሪው ጉዳዩን ሊደብቅ በማለት ሬሳ ሲያሸሽ ስለተያዘበት ጉዳይ ጽፌ ነበር። ምድራዊ ችግርን ብቻ ሳይሆን ሞትንም በጥሎ ማለፍ ተሻግረው፥ ወይም እንደ ኤልያስ ተነጥቀው አከሊል ባቋራጭ ሊቀበሉ የሚቃጣቸውም ከተነሡ ቆይተዋል። የዛሬ 30 ዓመት አዲስ ክርስቲያን ሳለሁ የሥጋ ሞት አንሞትም ከሚሉት መካከል አንዱ ገጥሞኝ ነበር። ይህ ሰው አሁንም አልሞተም፤ ግን በጣሙን እያረጀ ነው። ቶሎ ካልተነጠቀ የባሰ እያረጀ እዚሁ መኖሩን የሚወድደው አይመስለኝም። ዛሬም አንሞትም የሚሉ አዳዲሶች ተነሥተዋል።

ከየመድረክ የምንሰማቸው 'መገለጦች' በቃሉ ሳይፈተሹም እንኳ ስሜታዊና ግምታዊ መላ ምቶች ካልሆኑ፥ የተሰሉ ልምምዶች መሆናቸው እየተገለጠ የመጣው ቆይቶ ሳይሆን ገና ከጅምሩም ነው። የሚያሳዝነው በስሕተት ነፋስ የሚነዳው አጨብጫቢው መንጋ ነው። አንዳንዱ ውኃ ሲወስድ እንደሚያሳስቀው እየሳቀ ይወሰዳል። በዚህ ዘመን እስከ ሲያል ደጅም እየሳቁ የሚደርሱ ሰዎች በዝተዋል። አንዳንዱ እያጨበጨበ ወደሚሸለትበት መሸለቻ እየተወሰደ ነው። ቀደም ሲል በጠቀስኩት 'ነቢይ' ጉባኤ እየተደመሙ የሚስቁና የሚያጨበጭቡ አጨብጫቢዎች ቤቱን ሞልተው ሲታዩና የተናጋሪው እንቅስቃሴና ሁኔታ የተዋጣለት የመድረክ ተዋናይ ሲያስመስለው ቦታው የሆነ ሰርከስ ወይን ቴያትር ቤት ቦታ እንጂ ቤተ ክርስቲያን ነው ብሎ ለመቀበል ያዳግታል። ክርስቲያኖች በአጠቃላይ የሚነገረንን፥ የምንሰማውንና፥ የሚሆነውን በቀላሉ የምናምን ሰዎች ነን። መመርመርና መጠየቅ ነውርና እምነት ማጣት ይመስለናል፤ አንዳንዶች መጠየቅና መመርመር እምነት ማጣት ነው ተብሎ ተነግሮአቸው ይህን አምነው ተቀብለዋልና በዘመናቸው ሁሉ ከመድረክ የሚሰጣቸውን ሁሉ እንደ ዶክተር መድኃኒት ምንም ሳይጠይቁ ሲውጡ ይኖራሉ።

ይህንን የሚያስደርጉት 'ነቢያት' አውቀው ነው ይህን የሚያደርጉት ወይስ ስተው ነው? የሰውን ልብ መመርመር የእግዚአብሔር ክልል ነው። ወደዚያ ግዛት ማንም ሰው መግባት አይችልም። ማድረግ የምንችላቸው ጥቂት ነገሮች ግን አሉ። <u>አንደኛ</u>፥ የተናገሩትን ቃል መስማትና መመርመር እንችላለን። ይህን የምንችልበት ምክንያት መመርመሪያው ቃል በእጃችን ስለሚገኝ ነው። <u>ሁለተኛ</u>፥ የተነገሩትን ትንቢቶች ዘላቂ ተፈጻሚነት መፈተሽ ነው። ከተነገሩት ፈውሶችና ትንቢቶች ጥቂቱን ወስዶ ትክክለኛ

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2015

ፍጻሚያቸውን መመርመር ነው። ሦስተኛ፥ ትምህርታቸውን ብቻ ሳይሆን ሕይወታቸውንም መታዘብ ነው። ከምንም ነገር በላይ ክርስቶስን ይመስላሉ? አራተኛ፥ ከዚህ በቀደመ ደግሞ ወደ ኋላ በመሄድ ታሪካቸውን፥ በተለይም መንፈሳዊ ዕድገታቸውን፥ ትምህርታቸውን፥ በተለይም መንፈሳዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርታቸውን፥ የተማሩበትን ቦታና ያስተማሯቸውን ሰዎች፥ የነዚህንም ያስተማሯቸውን ሰዎች የራሳቸውንም ምስክርነትና ትምህርት ማጤን ልናደርጋቸው የምንችላቸው ነገሮች ናቸው።

ዛሬ በመድረክ ላይ የሚታዩና የሚሰሙት ነገሮች ስሜትን የመማረክና ጨብጦ የመያዝ ችሎታ ያላቸው ሊመስል ይችላል። ሊኖራቸውም ይችላል። ግን አስፈሪ ችግሮች አሉበት።

አንደኛውና ትልቁ ችግር፥ እነዚህ ልምምዶች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ስለሌላቸው ልዩ ወንጌልና ሌላ ክርስቶስ ሊሰበክባቸው ይችላል። ጳውሎስ በ2ቆሮ. 11፥4 *የሚመጣውም ያልሰበክነውን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክ፥ ወይም ያላገኛችሁትን ልዩ መንፈስ ወይም ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ፥ በመልካም ትታገሡታላችሁ።* ያለው ይህንን ነው። ያኛው ሌላ ኢየሱስ መስበኩ ብቻ አይደለም የሚያስደነግጠው። እነዚህ በመልካም መታገሳቸውም እንጂ! ይህ ነው የማጨብጨብ አንድ ገጽታ። የተሰቀለው ክርስቶስ ሳይሆን አደሳሳቹ ክርስቶስ እየተነገራቸው ብዙዎችም ሊመለሱ ከሚችሉበት መስመር አልፈው ሄደው የማይመለሱበት ደረጃ ላይ ሊደርሱ ይችላሉ። በ1978 ጂም ጆንስ ወደ ጋያና ወስዶ የፈጃቸው ከ900 በላይ ክርስቲያኖች (ከ300 በላይ ሕጻናት ናቸው) ሊያልቁ የበቁት ቀድሞ የሰሙትና ያወቁት እውነት በልዩ ወንጌል፥ በሌላ መንፈስና በሌላ ኢየሱስ ተለውጠባቸው ነው።

ሁለተኛው ችግር ይህ ጉዳይ ስሜት ላይ ብቻ ያተኩርና መንፈስን የማይነካ ይሆናል። አስደናቂና ማራኪ ሆኖ ሊዘገይ ይችላል። ስሜት ደግሞ ከዚያ የበለጠና የተሻለ ነገርን ይፈልጋል፤ አዲስ ልምምድን ይፈልጋል። ለዚህ ነው ልምምዶች አንዱ ሌላውን እየተኩና በቦታቸው አዳዲስ ልምምዶች እየተፈለፈሉ የሚገኙት። ክርስቲያናዊ ልምምዶችም እንደ ወርሃዊ መጽሔት የአፍላና የወረት ብቻ ሆነው እየቀሩ ያሉት ለዚህ ነው። የማይረኩ ክርስቲያኖች ደግሞ እነዚህን እያሳደዱ የማያድጉ ሆነው የሚኖሩትም ከዚህ የተነሣ ነው።

ሦስተኛው ችግር፥ ይህ መንገድ ወንጌል የሚነገርበት ሊመስል ይችላል። ሰዎች ለተለያዩ ግላዊ ግቦች ሊሰበሰቡ ይችላሉ። ሰዎች ወደ ክርስቶስ መምጣት ያለባቸው ክርስቶስን ብለው እንጂ በክርስቶስ ገበታ ላይ ያለውን መብል ፈልገው መሆን የለበትም። ይህኛው ሊኖር ይችላል (ላይኖርም ይችላል)፤ ከኖረም ዋናው ጉዳይ እርሱ አይደለም። ዋና ያልሆነው ጉዳይ ዋና ከሆነ ውሎ አድሮ ክርስቶስ ላይታይ ብቻ ሳይሆን ክርስቶስ ያልሆነው ሊታይ ይችላል። ክርስቶስ ያልሆነው ሲታይ ክርስትና መሰደቢያና መሳለቂያ ብቻ ሳይሆን የሚሸሹትና የሚጠየፉትም ሊሆን ይችላል።

ስተው የሚያስቱ ሰዎች ወደ እውነት እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት እንዲመጡ መጸለይና እውነትን ማሳወቅ አለብን። አንዳንዶች አምርረው ላይመለሱ ይችላሉ። አንዳንዶች የባሰውን በተቃራኒ አቅጣጫ ሊሸመጥጡም ይችላሉ። ከላይ ላየነው 'ነቢይ' በቃለ መጠይቁ ወቅት ከቀረቡለት ጥያቄዎች መካከል አንዱ፥ ባህሪይህ ምን ይመስላል? . . . ቢመክሩህ የመመከር ልቡ አለህ? የመቀበል ልቡ አለህ? የሚል ነው። መልሱ፥

> ባህሪዬ እርጎ ነው [ሳቅ] . . . እኔ ትክክለኛ ባህሪይ የምለው ኃይለኝነትም ወይም ደግሞ ዝምተኛም አይደለሁም። . . . የነቢያት ባህሪ ደግሞ ነቢያት አንድ ኮንስታንት ባህሪ የላቸውም፤ እስጢፋኖስ እንደሚመራቸው ነው ሚነዱት እና . . . ለአባቶችን ለመመከር በእግዚአብሔር ቃል ለማፅናት፥ ለማሳደግ፥ ለማነጽና በውስጤ ያለውን የእግዚአብሔርን ቅባት ለማውጣት፣ እኔን ከመደገፍ አንጻር በሚመጡ ምክሮች በሬም፥ ቢሮዬም ልቤም ከፍት ነው። ግን አንዳንድ ሆነ ብለው ለመስበር ቃል እየጠቀሱ አናት የሚሰብር ነገር ይዘው የሚመጡ ሰዎች አሉ። በፍጹም በሬ ቁልፍ ነው። ትልልቅ ሰዎች ቢመክሩኝ፥ በሕይወታቸው፥ በዕድሜያቸው በዘመናቸው፥ ባሳለፉት ነገር፥ በቆይታ የሚያገኙት ልምድ ስላለ ያንን ነገር ለመቀበል በጣም ዝግጁ ነኝ። ከእግዚአብሔር የሆነ ምክር ሊመክረኝ የሚመጣ ሰው ሁሉ ትንሽ ትልቅ አልልም ለመቀበል ዝግጁ ነኝ።

እኔን ከመደገፍ አንጻር ካልሆኑ በቀር በሬ ቁልፍ ነው የሚል ሰው አቋሙ ግልጽ ነው። እርሱን የሚደግፉ ብቻ ምክር እንዲሰጡት ነው የሚፈልገው። ደጋፊማ ድጋፍ እንጂ ምክር እንደማይሰጥ ምነው ለመረዳት ተሳነው? ምክር የሚሰጥ ደግሞ የግድ ደጋፊ ሊሆን አይጠበቅበትም። ደጋፊ ይሁን ከተባለ ምርጫው አንድና አንድ ብቻ ነው። መደገፍ፥ ማጨብጨብ። እንዲህ ያሉ መሪዎች የሚገዟቸው አብያተ ክርስቲያናት ፍተሻና ጥያቄን እንደ ዓመጽ ስለሚያዩት ዕድሉን ይነፍጉታል። በ'ነቢይ' በላይ ማኅበር ድረ ገጽ የእምነት አቋምም ይኸው ተንጸባርቆአል፤ Rebellion Against Church Authority Forbidden በሚለው ርእስ ስር ማብራሪያው እንዲህ ተጽፎአል፤

> Rebellion against Church Ministers is against the Will of God. Those who rebelled against Moses did not escape unpunished – Num 12:1-10; Num. 16:1-4,32. The Bible teaches that we should obey our Spiritual leaders and submit to them – Heb 13:17; Joshua 1:16-18.

ያሰመርኩት ራሴ ነኝ። ቃሉ ዓመጽ ተብሎ፥ ዓመጹም በቤተ ክርስቲያን መሪዎች ላይ እንደሆነ ነው የተጻፈው። መሪዎች የማይሳሳቱ ተደርገው ታስበዋል፤ ደግሞም ከቤተ ክርስቲያን ጋር እኩያ ተደርገዋል። የስሕተት ሃይማኖቶች የጭቆናና የቁጥጥር ተግባር አንድ ገጽታ ሥልጣንን መመከቻና የሰዎች መቆጣጠሪያ ማድረግ ነው። በኢ-መጽሐፍ ቅዱሳውያን የስሕተት ትምህርቶች ዘንድ በቤተ ክርስቲያን ስም የሚል ሥልጣን ነው እቆጥ ላይ የሚወጣው። ቤተ ክርስቲያን የባለ ሥልጣኑ የክርስቶስ አካል ነች እንጂ ምድራዊ ባለ ሥልጣን አይደለችም። የትምህርቷና የሥርዓቷ ምንጭም የጌታ ቃልና የቃሉ ጌታ የሆነው ክርስቶስ ነውና ቤተ ክርስቲያን የሥርዓት እንጂ የሥርዓት አልባነት ስፍራ አይደለችም። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያንና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች በአስገዳጅነት በሰዎች አካልም ሆነ ኅሊናና አእምሮ፥ ወይም ነፍስና መንፈስ ላይ የሥልጣን ክንድ አያሳዩም። ሊያሳዩም አይግባም። እንደዚህ የሚያደርጉ አብያተ ክርስቲያናት የሉም ማለት አይደለም፤ በብዛት አሉ። እነዚህ በቀረቤታ ሲታዩ ቤተ ክርስቲያን ሳይሆኑ ቤተ ክርስቲያን የሚመስሉና ሃይማኖታዊ መልክ ያላቸው ድርጅቶች ናቸው። ሙሴን የተቃወሙ ሳይቀጡ እንዳላመለጡ እንድታውቁ ብሎ ማስፈራራትና በሙሴ ወንበር መቀመጥ ቤተ ክርስቲያንን እና ክርስቶስን ሳይሆን የማኅበር መሪን አመልካች ነው። ክርስቲያን መሪዎች ወደ ሥልጣኑ ምንጭ ነው እንጂ ወደ ራሳቸው አይደለም ማመልከት ያለባቸው። በቤተ ክርስቲያን ስምም ለራሳቸው መቆም የለባቸውም።

ትኩረትን ወደ ራሳቸው የሚስቡ መሪዎች፥ 'ቃል እየጠቀሱ አናት የሚሰብር ነገር ይዘው ለሚመጡ ሰዎች በሬ ቁልፍ ነው' ማለት ሳይሆን የአገልግሎታችን ሥልጣን ምንጭ በሆነው የእግዚአብሔር ቃል አናት እንደማይሰበር ማወቅ አለባቸው። ገና ለገና አናታቸው በቃሉ እንደሚሰበር ፈርተው በቃሉ መፈተሽን መጥላት የሚያገለግሉት ቃሉንና እንደ ቃሉ ያለመሆኑ ምልክት ነው። የቃሉ አገልጋይ ከሆኑ በቃሉ አናታቸው አይሰበርምና በቃሉ መፈተሽን በመፍራት ለምክር በር መቆለፍ ተገቢ አይደለም። ካልሆነ ደግሞ የቆሙበትን መፈተሽ አለባቸው። በዚህ ዘመን ከበር መቆለፍ የሚያልፉ አይጠፉም። ወይም አስገብተው የሚቆልፉም አይታጡም። ባለፈው ሕያሴን ጠልቶ አንድ ዘማሪ በሥጋ እንደሚገለጥብኝ እንደዛተብኝ ጠቅሼ ነበር። ከክርስቲያኖችም በሥጋ ክንድ ሊያደባዩ ታጥቀውና ጡንቻ አፈርጥመው የሚነሡ የሚያቅራሩበት ጊዜ ላይ መሆናችን ያስገርማል።

በዚህ ወር አጋማሽ (March 2015) የዲትሮይት ነዋሪ የሆነ ባሴል ሰዓድ (Bassel Saad) የተባለ ሰው የ15 ዓመት ጽኑ እስራት ተፈረደበት። ይህ ፍርድ እንዲፈረድበት ምክንያት የሆነው ክስ እንዲህ ነው። ባለፈው በጋ ወራት በአንድ የወዳጅነት እግር ኳስ ግጥሚያ ወቅት ጥፋት በማጥፋቱ ምክንያት ዳኛው ጆን ቤኔዊትዝ (John Bieniewicz) ቀይ ካርድ ሊያሳየው በመዘጋጀት ላይ ሳለ ባሴል በቦቅስ የዳኛውን መንጋጋ መትቶ

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ © 2015

ከዘረረው በኋላ ዳኛው እንደተዘረረ ቀረ። ወደ ሆስፒታል በፍጥነት ቢወሰድም የ44ቱ ዓመት የኳስ ዳኛ በሁለተኛው ቀን ሞተ።

በፍርዱ ቀን የጆን ሚስት ክሪስ ቤኔዊትዝ ቃሏን ስትሰጥ ቀይ ካርድ በእጇ ከፍ አድርጋ ይዛ ነበር የጉዳት ቃሏን (impact statement) የተናገረችው። በዚህ ቃሏ፥ "የአንድ ሰው የታመቀ ቁጣና ንዴት፥ በልቡ ውስጥ የታመቀ በቀል የባለቤቴን ሕይወት መውሰድና በሂደቱ ውስጥ ደግሞ የኔን ቤተ ሰብ ብቻ ሳይሆን የራሱንም ቤተ ሰብ ሕይወት ሊያፈርስ በቃ" አለች።[9] ገና ለገና ቀይ ካርድ ሊያሳየኝ ነው ብሎ እስከ መደብደብና መግደል መድረሰም አለ።



አጨብጫቢዎች? ወይስ ዐቃቢዎች?

ጥፋት ሲፈጸም ሳያውቁ የሚከተሉ ጀሌዎች ቢኖሩም ጥፋት መሆኑ እየተረዱ በተለያዩ ምክንያቶች የሚተባበሩና የሚያበረታቱ ሰዎች ደግሞ አሉ። አንዳንዶች ተሰማምተው ሲሆን ሌሎች በተጽዕኖ ነው። ተጽዕኖው ከይሉኝታ ጀምሮ እስከ ፍርሃት ይደርሳል። እንደ ጌዴዎን ሠራዊት ማለት ነው። በመሳ. 7፥3 *የፈራ የደነገጠም ከገለዓድ ተራራ ተነሥቶ ይመለስ ብለህ በሕዝቡ ጆሮ አውጅ አለው። ከሕዝቡም ሀያ ሁለት ሺህ ተመለሱ፥ አሥርም ሺህ ቀሩ* ይላል። 70% ጀሌ ከልብ ያይደለ ሠራዊት ነበር። እንዲህ ያለ ሠራዊት ቢያፈገፍግ ወይ ቢሸነፍ፥ ወይ ከመንገድ ቢቀር ወይ ቢመለስ ምን ያስገርማል? ለሰልፍ መውጣታቸውን ግን ልብ እንበል። እነዚህ ተዋጊዎች ሳይሆኑ ከአጨብጫቢም የወረዱ አጃቢዎች ናቸው። መጣራት ስለነበረባቸው ነው ከ32 ሺህ ወደ ሦስት መቶ እስኪመነምኑ የተራገፉት።

አቤሴሎም የአባቱን መንግሥት በገለበጠ ቀን ተጠርተው የመጡና አጅበውት የወጡ አባሪዎች ነበሩ። 2ሳሙ. 15፥11 *የተጠሩትም ሁለት መቶ ሰዎች ከአቤሴሎም ጋር በየዋህነት ከኢየሩሳሌም ሄዱ የሚሆነውንም ነገር ከቶ አያውቁም ነበር* ይላል። ለምን እንደተጠሩና እንደታደሙ ሳያውቁ አጅበዋል። በሐዋ. 19 ውስጥ፥ "*የኤፌሶን አርጤምስ ታላቅ ናት!*" እያሉ ሁለት ሰዓት ያህል የጮኹ ሰዎች ተጠቅሰዋል። ቁጥር 32 እንደሚነግረን በጉባኤው ከነበሩት የሚበልጡቱ ለምን እንደተሰበሰቡ እንኳ የማያውቁ ነበሩ። ስለሚሆነው ነገር የማያውቅ ትርምስ እንዴት ነው ሁለት ሰዓት ሙሉ አንድ ነገር እየደገመ የሚጮኸው? መልሱ ቀላል ነው፤ ዓለማቢስ ትርምስ (mob) ማሰቢያ አዕምሮ የለውም። ክርስቲያኖች ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ከመነሣታቸው በፊት የሚሄዱት ከቅዱሳን ጋር ለማምለክና የተጻፈው ቃሉ ሲገለጥ ለመማር እንጂ ስሜታቸውን ለማስኮርኮርና ወደ መዝናኛ ስፍራ እንደሚሄዱት ያለ መሄድ አለመሆኑን አውቀው ካልሄዱ የማጨብጨብና የመገረም ሰለባ መሆናቸው የማይቀር ነው።

በታሪክም ውስጥ ለውሸት ያጨበጨቡና በውሸት የተዋጡ ጥቂት አይደሉም። ሒትለር ወደ ሥልጣን በመጣበት ዘመን የጀርመን ሕዝብ በአብዛኛው፥ የይስሙላ ክርስቲያኖች ቢኖሩበትም 66% ወንጌላዊ አማኝ 33% ደግሞ ካቶሊክ ነበሩ። እንዲህ ባለ ኅብረተ ሰብ ውስጥ ያ ክፋትና ጭካኔ እንዴት ሊንሰራፋ ቻለ? በሂትለር ልብ ውስጥ የሰለጠነ ሰይጣን ቢኖርም ሌላው ምክንያት 'ሰፊው ሕዝብ' ለጅርመን ብሔራዊ ሶሻሊዝም ወይም ለናዚ ፓርቲ ፍልስፍና አጨብጫቢ ስለሆነ ነው። ኋላ ደግሞ ፍርሃት አግግቶ ሰለባ አደረጋቸው። ሂትለር ዙፋኑ ሥልጣኑን ካደላደለ በኋላ ከጥያቄ በላይ ሆነና ማን ይናገረው?

በመጨረሻው ዘመን ለብዙዎች በምድር ላይ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የሚንሰራፋበት ይመስላቸዋል። ይህ አሳብ ሲሰበክ ደጋግመን ሰምተን ይሆናል። የዶሚኒየን ቲዮሎጂ እና ይህን መሰል የስሕተት ትምህርቶች የሚያስተምሩት ቤተ ክርስቲያን አይላ፥ ወራሪ ሆና ዓለምን ሁሉ ትወርሳለች የሚል ነው። ቃሉ የሚያስተምረን ግን የዚህን ተቃራኒ ነው። ቤተ ክርስቲያን የስሕተት ሙሉ ሰለባ ባትሆንም፥ ወንጌል እየገፋ ቢሄድም በመጨረሻው ዘመን የስሕተትና የሐሰት ሥራ ይዛመታል። ሐሰተኞች ክርስቶሶች ይበዛሉ። ሐሰተኛ ድንቆችና ምልክቶች የተለመዱ ክስተቶች ይሆናሉ። ሰይጣን የሚያምኑትን እንኳ የማሳት ሙከራው የጠነከረ ይሆናል። *መንፈስ ግን በግልጥ፥ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የኢጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላልና* 2ጢሞ. 4፥1። ይህ ቃል የተነገረው ለማያምኑ አይደለም፤ የተጻፈው በኤፌሶን መጋቢ ሆኖ ሳለ ለጢሞቴዎስ ነው። ክርስቲያኖች ጌታንና ቅድስናን ሳይሆን ምልክቶችንና ተአምራትን እያሸተቱ የሚሄዱ ከሆኑ በቀላሉ ሊጠለፉ ይችላሉ። ምልክትና ተአምራት ለሰይጣን ርካሽና የሚሠሩ ሸቀጦቹ ናቸው። ስለዚህ ተጠንቃቂዎችና አስጠንቃቂዎች እንሁን።

እንደ ቤርያ ሰዎች መጻሕፍትንና ትምህርቶችን ለመጠየቅና ለመመርመር (ሐዋ. 17፥11) እንዲሁም ሌሎች ሌሎች ስለምንታመንበት ተስፋ ሲጠይቁንም መልስ ለመስጠት ሁሌም የተዘጋጀን እንሁን። *በእናንተ ሰላብ ተሰፋ ምክንያትን ለሚጠይቁአቸሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን* እንዲል 1ጴጥ. 3፥15።

እነዚህ አዳዲስ 'ነቢያትና ሐዋርያት' ማኅበራዊ የግንኙነት አውታሮችን (social media) በሚያስደንቅ ፍጥነትና ቅልጥፍና እየተጠቀሙት ነው። ስለዚህ እስከሚያሳዝንና እስከሚያሳፍር ድረስ ክርስትናን ከቲቪ ወይም እንደ ዩቲዩብ ካሉ ቦታዎች ብቻ የሚያውቁት አእላፍ ናቸው። ከሚዲያ ሠሪዎቹም ብዙዎቹ የገንዘብ ሠሪዎች ብቻ እንጂ መንፈሳዊነትና መጽሐፍ ቅዱሳዊነት ቀርቶ የኅሊና ዳኝነት እንኳ የሌላቸው ናቸው። ስለዚህ ገፈቱንም አተላውንም አብረው ለተመልካች ያቀርቡታል። አንዳንዱ መሳለቂያና መዘበቻ ነው። አንዳንዱ ግን አሳች ነው። *በነውን ማን ያሳየናል?* የሚሉ *ብዙ* ናቸው ይላል መዝ. 4፥6። ይህ ዛሬም እውነት ነው። እውነተኛውን እውነት የሚፈልጉትን እውነት በሚባል ቁርበት የተጠቀጠቀ ውሸት፥ ወይም ጭራሹኑ ቆዳውም ሥጋውም ውሸት ከሆነ ስሕተት ጋር የሚያስተዋውቁም ብዙ ናቸው።

እና ምን ይሁን? እኛስ ምን እንሁን? ደግሞስ ምን እንሁን? ከላይ እንዳልኩት፥ መርማሪዎች፥ ፈታሾች፥ መላሾች እንሁን። እውነትን መናገር ካልቻልን የውሸት አጨብጫቢ አንሁን። የሐሰተኛ ነቢያት መጋቢነትና ቀላቢነት ይራቀን። አዳናቂና አዳማቂ አንሁን። ይህን በማድረጋችን አጥፊዎችን ማበረታታችን ብቻ ሳይሆን እውነት ፈላጊዎችን ከእውነት መግፋታችንና ማራቃችንም ነው። ከዘላዩ ጋር ዘላይ፥ ከጨፋሪው ጋር ጨፋሪ፥ ከመሐል ሰፋሪው መሐል ሰፋሪ አንሁን። አጀብ አጀብ የሚል አጃቢ አንሁን። ይልቅስ አጃቢ ሳይሆን ዐቃቢ እንሁን። ዐቃቢ ጠባቂ ማለት ነው። ዘበኛ እንደ ማለት ነው። ለእውነትና ለቃሉ ጠባቂነት ዘብ እንቁም። ለመጽሐፍ ቅዱሳዊው እምነት እንቁም። አሰስ ገሰሱ ወደ መድረክ እንዳይወጣና ታሪካዊውንና መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ክርስትና መልክ እንዳያቆሽሽ ለሰዎችም ክርስትና ያ እንዳይመስላቸው ዘብ እንቁም። ሰባኪዎችን በጭብጨባ አንሸንግል፤ ራሳችንንም የጭብጨባ ታጋቾችና እስረኞች አድርገንን ወደ ጥፋት አንጓዝ። በማስተዋል እንዘምር፥ እናምልክ፥ ቃሉንም እንስማ እንጂ ሰባኪ ሲያጓራና ሲስት ስሕተትን እያየናት ርካሽ ጭብጨባ አናጨብጭብ። ሐሳዊ ነቢይ የሐሰት ትንቢት፥ በክርስቲያናዊ ቋንቋና በክርስቶስ ስም የታጀበ የጥንቆላ ቃላት ሲናገር ዐቃቢ እንጂ አጨብጫቢ አንሁን። እባካችሁ አንሁን።

[9] *Copyright © 2015, Los Angeles Times; March 13, 2015.*

ዘላለም መንግሥቱ © 2015 (ፀሺህ፭) ዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት


ዕዝራ ስነ ጽሑፍ © 2015

እስላም እና ክርስትና

(ንጽጽራዊ አቀራረብ)

የመጽሐፍ ሒስና ግምገማ

ክፍል ሰባት



ባለፈው የተመለከትነው ዶ/ር ሙሐመድ ዓሊ በመጽሐፉ ምዕራፍ ሁለት የሥላሴ አስተምህሮ የተሳሳተና እንደሆነ ለማሳየት ሙከራ ማድረጉን ነው። ከዚያ በፊት ባሉት ክፍሎች የመጀመሪያው የመጽሐፉ ምዕራፍ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያነጣጠረ ነበረ። በሁለተኛው ምዕራፍ የክርስቲያኖች አምላክ በኮሚቴ የተዋቀረ መሆኑን እያጥላላ ይግለጥ እንጂ ቁርኣን ሥላሴን የተረዳበትን መረዳት አላቀረበም። ቁርኣን ሥላሴን የሚያስረዳው እንደ ሦስት አማልክትና ሦስቱ አማልክትም አላህ፥ ኢየሱስና የኢየሱስ እናት ማርያም መሆናቸውንም ተመልክተናል። ደግሞም ሥላሴ ወይም አንድ አምላክ በሦስት አካላት መገለጡ ሦስት አማልክት ማለት አለመሆኑንና ቁርኣን ይህን አበክሮ ተረድቶ የነቀፈ አለመሆኑንም አይተናል። ደግሞስ፥ እግዚአብሔር ሉዓላዊ አምላክ ነውና እርሱ የሆነውን እርሱነት፥ የገለጠልንን ማንነት እንቀበላለን እንጂ ሦስት በአንድ ከሎጂክ የወጣ ነውና አንቀበልም እንላለን? ፈጣሪ እግዚአብሔር ፍጡሩ የሚፈልገውን መሆን አለበት? ወይስ ፍጡሩ ፈጣሪው የሆነውን እርሱነት ግልጥልጥ ብሎ ቢገባውም ባይገባውም መቀበል አለበት? እንኳን ፈጣሪን ፍጥረትንስ መቼ በሎጂክ መምረን ጨረስን?

ይህ መጽሐፍ በ3ኛው ምዕራፍ ከኢስላማዊ መረዳት አንጻር ስለ ኢየሱስ ሊያትት ይሞክራል። ስለ ኢሳ ከሚተነትን ከዶ/ር ሙሐመድ ዓሊ ጋር ተመሳሳይ ከሆነ ከሌላ አንድ ዲቪዲ ምንጭ ልጀምር፤ "ኢየሱስን አይሁድ ዲቃላ፥ እድብ፥ ጠንቋይና ሐሰተኛ ነቢይ ነው ይሉታል። ክርስቲያኖች አላህ ከሰጠው የነቢይነት ደረጃ ደረጃውን ከፍ በማድረግ ክብሩን በማላቅ አምላክ፥ የአምላክ ልጅና ከሥላሴዎች አንዱ ነው ብለው ያምናሉ" ይልና ሙስሊሞች ግን በትክክል የአላህ ባሪያና ነቢይ መሆኑን ይገልጣሉ" ብሎአል።[10] አይሁድ ኢየሱስን እንደ ማርያምና ዮሴፍ ልጅ ነበር የሚያዩትና ዲቃላ ሊሉት አይችሉም። ዲቃላ ያሉበት ታሪክም በወንጌላት ውስጥ የለም። ዲቃላ የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን አንድ ቦታ በቀር አይገኝም። እርሱም ስለ ኢየሱስ የተነገረ አይደለም። ሐሰተኛ ነቢይም አላሉትም። አበደ ያሉት ዘመዶች ነበሩት፤ አጋንንት አለበት እና በአጋንንት አለቃ አጋንንት ያወጣል ያሉ ፈሪሳውያን ነበሩ፤ አሳቡ ሊቀራረብ ቢችልም ጠንቋይ ግን አላሉትም። ይህ የአይሁድን ስም የማጉደፍና እነርሱን አጥላልቶ የማቅረብ ዘመቻ ይመስላል። ክርስቲያኖች ደግሞ ኢየሱስን ከደረጃው የማላቅ ወንጀል ተሰንዝሮባቸዋል። ይልቅስ ኢየሱስን ከደረጃው አዋርዶ ፍጡር የማድረግ ኃጢአት እንደምን ሊዘነጋ ይገባል? <u>አምን አምላክ ያልሆነ ሰውን አምላክ ማሰኘት ኃጢአት የመሆኑን ያህል አምላክን ፍጡር ብቻ ማድረግም እኩ የዚያን ያህል ኃጢአት ነው።</u>

በመጀመሪያ ስለ ኢየሱስ ያዩት፥ የሰሙትና የዳሰሱት የጻፉት ምን አሉ? በኋላ ከተጻፈው ይልቅ ቀድሞ የተጻፈው ምን ይላል? የሚለውን ማየት አለብን። ከዚህ በፊት እንዳየነው ዶ/ር ሙሐመድ ዓሊ ቀድሞ የተጻፈው (ብሉይም አዲስ ኪዳንም) ተሳስቷል፥ ተበርዟል፥ ዋናው ጠፍቷል፥ ወዘተ፥ ብሎ የምንጩ ምንጭነት ዋጋ አጣጥሎአል። ይሁን እንጂ ቁርኣን በተጻፈበት ዘመን የነበረው ቃል አሁን ካለው ቃል ጋር አንድ መሆኑ የተረጋገጠ መሆኑም ተወስቶአል። ስለዚህ ኢየሱስን ለማወቅ የሚፈልግ ሰው መሄድ ያለበት ስፍራ ምንጩ እንጂ ከምንጩ የስሚ ስሚ ሰምቶ ከቀዳ ኩሬ አለመሆኑ ግልጽ ነው። ኦርጂናሌ ዕቃ ለመግዛት ወደ ቸርቻሪና አትራፊ ሳይሆን ሠሪው ኩባንያ መሄድ የተረጋገጠለት፥ የተጨበጨበለት ዕቃ ያስገኝልናል። ማንም ምሑርና ሊቅ ሰው፥ ማንም ጥናታዊ ሥራ ሊሠራ የሚወድ ሰው ስለ ኢየሱስ ለማጥናት ፈልጎ ወደ ቁርዓን የሚሄድ ካለ የተሳሳተ ሰው ነው። አንድ ሰው የኢትዮጵያን ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ፕሬዚደንት ለማየት ቢወድድ ወደ ቤተ መንግሥት ነው መሄድ ያለበት፤ እንዲያው መግባት ባይችልና ምናልባት በአጋጣሚ የማየት ዕድል ቢኖረኝ ብሎ ቢያስብ መሄድና መመላለስ ያለበት ከመስቀል አደባባይ ጀምሮ እስከ አራት ኪሎ ባለው መንገድ ነው እንጂ ሱማሌ ተራ ወይም ቅቤ በረንዳ ቢሄድ ከንቱ ልፋት ነው። የማግኘት ዕድሉ ምናልባት ምንም ነው።

ኢየሱስን ለማወቅ ወደ ምንጩ ነው መኬድ ያለበት! ምንጩ ከክርስቶስ ልደት፥ ሞትና ትንሣኤ በኋላ 600 በላይ ዓመታት ቆይቶ፥ ከምንጩ ሳይሆን ከሌሎች መጻሕፍትና የስሚ ስሚ ከተነገረው ተነሥቶ የተነገረውና ከተነገረው ተሰምቶ የተጻፈው ሳይሆን ያዩትና የሰሙት የተረኩት ነው። ስሙም ወንጌል ይባላል።

ዶ/ር ሙሐመድ ዓሊ ስሕተቱን የሚጀምረው እንዲህ በማለት ነው፤

> በኢየሱስ ማንነት ላይ ሐዲስ ኪዳን ግልጽ የሆነ የጠራ አቋም የለውም። አራቱ ወንጌሎች ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ፣ የዳዊት ልጅ፣ የአብርሃም ልጅ፣ የማርያም ልጅና የዮሴፍ ልጅ ብለው ይጠቅሳሉ።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ የኢየሱስን ማንነት እስኪያውቁትና ያላወቁት ሰዎች እንጂ ያወቁት ተከታዮቹና የወንጌላቱ ጸሐፊዎች የዮሴፍ ልጅ አላሉትም። ፊልጶስ መጀመሪያ ሲያገኘው ለናትናኤል ይህን አለ፤ ዮሐ. 1፥46። ናትናኤል ግን ኢየሱስን ካገኘው በኋላ የእግዚአብሔር ልጅ ብሎ መሰከረ። አይሁድ በመገረም የዮሴፍ ልጅ አይደለም ወይ? አሉ፤ ሉቃ. 4፥22፤ ዮሐ. 6፥42። ሉቃስ ሲጽፍም 'እንደመሰላቸው' የሚል ቃል ማስገባቱ የዮሴፍ ልጅነቱን ሳይሆን የመሰላቸው ያ መሆኑን መግለጡ ነው፤ ሉቃ. 3፥23።

የአብርሃም፥ የዳዊት ልጅ መባሉ በሥጋ የመጣበትን የተስፋ ቃል ዘር ሐረግ ለመግለጥ ሲሆን የተለያዩ ሰዎች ልጅ መሆኑን አያሳይም። ኢየሱስ በዚህ የዘር ሐረግ መጠቀሱ፥ የአብርሃም፥ የይስሐቅ፥ የያዕቆብ ልጅ መሆኑ የተስፋውን ዘር መስመር አመልካች ነው። አብርሃም ከይስሐቅ ሌላ ልጅ አለው። ኢየሱስ የመጣው ከዚያ (ከእስማኤል) አለመሆኑን ለማሳየት ነው። ይስሐቅ ከያዕቆብ ሌላ ልጅ አለው። ኢየሱስ ከዚያ (ከዔሳው) ያልመጣ አለመሆኑን ያመለክታል። ለዳዊት የዘላለማዊ ዙፋን ተስፋ ተሰጥቶታል ኢየሱስ የዳዊት ሥርና ዘር መሆኑ ዘላለማዊ ንጉሥ መሆኑን ያሳያል።

በአይሁድ ዘንድ ልጅን በአባት ብቻ ሳይሆን በአያትም በቅድመ አያትም ከዚያ በፊት በነበሩ ታዋቂ ሰዎች ጠርቶ የእገሌ ልጅ ማለት የተለመደ ነው። ለምሳሌ፥ ኢዮሳፍጥ የዳዊት ልጅ አይደለም። የልጁ የልጅ ልጅ፥ ልጅ፥ ልጅ ነው። ግን በ2ዜና 17፥3 በአባቱ በዳዊት መንገድ መሄዱ ተጽፎለታል። ይህ ለአይሁድ የተለመደ አገላለጥ ነው። ሉቃስና ማቴዎስ እንደዚያ ቢጽፉ አስደንጋጭ አይደለም። ይህ ማለት ግን ኢየሱስ በሥጋ የተገለጠው የተስፋው ዘር መሆኑን እንጂ የዮሴፍ ወይም የሌላ የማንም ወንድ ዘር መሆኑን መናገሩ አይደለም። ወደ ቀጣዮቹ የዶ/ር ሙሐመድ ዓሊ ስሕተቶች ከመዘለቃችን በፊት እዚህ ላይ ቆም ብለን የቁርኣኑ ኢሳ ከአዲስ ኪዳኑ ኢየሱስ ፈጽሞ የተለየ እንደሆነ ማስረዳት እሻለሁ። በዚያውም ዶ/ር ሙሐመድ 'አባቱ ማን ነው? ልጁ ማን ነው?' የሚለውን እናያለን።

ክርስቶስ በወንጌላት ስለ ራሱ የተጠቀመበት ተደጋጋሚ መጥሪያ፥ 'የሰው ልጅ' የሚለው ነው። የሰው ልጅ የተሰኘውም ሥጋን ስለለበሰና ሰው

---

[10] ኢሳ በቁርዐንና በወንጌል፤ ሳዲቅ መሐመድ፤ አል-ኢማሙ አሻፊዒ አዲዮቪዥዋል ፕሮዳክሽን፤ አዲስ አበባ። በተጨማሪ በYouTube ለማየት፥ https://www.youtube.com/watch?v=KDphfk-A3tQ ተመልከቱ።

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ © 2015

ስለሆነ ብቻ ሳይሆን በብሉይ ኪዳንም ይህ ስያሜ ለመሢሑ የተሰጠ ቃልም ስለሆነ ነው። ጥቂት ዝቅ ብለን ዳን. 7ን ስንቀስ እንመለከተዋለን። ክርስቶስ የአዳም ልጅ፥ የአብርሃም፥ የዳዊት ልጅ ቢባል ሰውነቱን ወይም ሥጋ መልበሱን እና የተሰፋውና የቃል ኪዳኑ ልጅ መሆኑን የሚያሳይ በሥጋም የመጣበትን ዘር መስመር የሚያሳይ እንጂ የእግዚአብሔር ልጅ አለመሆኑን የሚገልጥ አይደለም። እንዲያውም እነዚህን ሁለት አሳቦች አጣምሮ የያዘ አንድ ክፍል እንመልከት።

በማር. 12፥28-30 ከትእዛዛት ሁሉ ፊተኛ ስለሆነችው ጥያቄ ኢየሱስ የሰጠውን መልስ እናገኛለን። ቃሉ የሚለው ይህን ነው፤ *ከጻፎችም አንዱ ቀርቦ ሲከራከሩ ሰማና መልካም አድርጎ እንደ መለሰላቸው አስተውሎ ከሁሉ ፊተኛይቱ ትእዛዝ ማናቸይቱ ናት? ብሎ ጠየቀው። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ፥ እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፥ አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት። ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።*

ይህ ክፍል እንዲያውም ብዙ ሙስሊሞች ኢየሱስ አምላክ ላለመሆኑና አንዱ አምላክ (እነርሱ እንደመሰላቸው፥ አላህ) ብቻ አምላክ መሆኑን የተናገረበት ነው ብለው እንደ ጠንካራ መረጃ የሚያቀርቡት ነው። በትክክል ይህ ክፍል እግዚአብሔር አንድ መሆኑን የሚያረጋግጥ ክፍል ነው። አይሁድ ይህን ክፍል፥ ዘዳ. 6፥4ን በቃላቸው እንዲሉት ከትንሽነታቸው ጀምሮ በቃል የሚያጠኑት ጥቅስ ነው።

שְׁמַע יִשְׂרָאֵל יְהוָה אֱלֹהֵינוּ ׀ יְהוָה אֶחָד׃

ሽማዕ ይስራኤል፤ የሆዋህ ኤሎሄይኑ፤ የሆዋህ ኤካድ።

ሰማ እስራኤል፥ የሆዋህ አምላካችን አንድ የሆዋህ ነው። የሚል ቃል ነው። ባለፈው ክፍል እንደተመለከትነው ክርስቲያኖች ሦስት አማልክት አያመልኩም። ሥላሴ ማለት እና ሦስት አማልክት ማለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው። ዶ/ር ሙሐመድ እንዳፈዘው ቤተ ክርስቲያን አምላክ ቁጥር አንድ፥ አምላክ ቁጥር ሁለት እያለች አማልክት አልደረደረችም። ጌታ ያስተማረው ይህ ክፍል ስለ እግዚአብሔር አንድ መሆን ይመሰክራል።

ከዚያው ከማርቆስ ወንጌል ሳንወጣ፥ ጌታ ይህንን ከላይ ያየነውን ጥያቄ መልስ ከሰጠ በኋላ እርሱ ደግሞ ሌላ ጥያቄ አቀረበላቸው። ማር. 12፥35-37 እንዲህ ይላል፤ ኢየሱስም በመቅደስ ሲያስተምር መልሶ እንዲህ አለ፦ ጻፎች ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ነው እንዴት ይላሉ? *ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ፥ ጌታ ጌታዬን፥ ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው አለ። ዳዊትም ራሱ ጌታ አለው፤ እንዴትስ ልጁ ይሆናል?* ብዙ ሕዝብም በደስታ ይሰሙት ነበር። እዚህ ያቀረበው ጥያቄ የእግዚአብሔር አንድ መሆን እንደተጠበቀ የእግዚአብሔርን ሥላሴነትና የክርስቶስን የዳዊት ልጅ ሆኖ ሳለ የዳዊት ጌታ መሆን የሚያሳይ ነው። ቀደም ሲል የዳዊት ልጅ መሆኑ በዚሁ ወንጌል ተጠቅሶአል፤ 10፥47-48፤ እና 11፥10።

ያሰመርኩበት ክፍል፥ *ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ፥ ጌታ ጌታዬን፥* ይላል። ተናጋሪው ዳዊት ሲሆን የተናገረው በመንፈስ መሆኑ ተጽፎአል። መንፈስ የተባለው መንፈስ ቅዱስ ነው። ይህ ቃል የተወሰደው ከመዝ. 110፥1 ሲሆን መዝሙሩ በሙሉው ስለ መሢሕ የሚናገር ነው። ቁጥር 1 የሚለው፥ *እግዚአብሔር ጌታዬን፦ ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው።* ነው። יְהוָה ׀ לַאדֹנִי የሆዋህ ለአዶኒይ፤ ያህዌህ ወይም እግዚአብሔር ለአዶናዬ ወይም ለጌታዬ ነው የሚለው። በዚህ ደግሞ እግዚአብሔር እና ጌታ የተባለው መሢሑ ይታያሉ። በዚህ አንድ ጥቅስ ውስጥ እግዚአብሔር አብ፥ መሢሑ፥ እና መንፈስ ቅዱስ ይታያሉ። ጌታ የእግዚአብሔርን ኤካድ (አሐድ) ወይም አንድ መሆን በጠቀሰበት ትምህርት ወዲያውኑ የመሢሕን ማንነት ከመግለጥ ጋር አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስን መግለጡ ግልጽ ነው።

በቀኜ መቀመጥ ማለት ደግሞ ዙፋንን መጋራት ወይም በዙፋን ከተቀመጠው ጋር እኩል መሆን ነው። የእግዚአብሔር ዙፋን በስፍራ የተወሰነ አድርገን ማሰብ የለብንም። ለዙፋኑና ለግዛቱ ወሰንና ዳርቻ የሌለው የሌለው አምላክ ነው። መዝ. 103፥19 *እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አዘጋጀ፥ መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች* ይላል። ኢየሱስ በአብ ቀኝ ተቀመጠ ማለት ይህንን ዙፋን ተጋራ ማለት ነው። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ዙፋንን መጋራት አይችልም። ኢየሱስ ይህን ዙፋን ከተጋራ ሰው ሆነ እንጂ ሰው ብቻ አይደለም ማለት ነው።

ይህ ብቻ አይደለም፤ ዳን. 7 የሰው ልጅ ብሎ ስለሚጠራው ሲያይ በተለይ ቁጥር 9-19 ላይ *ዙፋኖችም እስኪዘረጉ ድረስ አየሁ፥ <u>በዘመናት የሸመገለውም</u> ተቀመጠ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ፥ የራሱም ጠጕር እንደ ጥሩ ጥጥ ነበረ ዙፋኑም የእሳት ነበልባል ነበረ፥ መንኰራኵሮቹም የሚነድድ እሳት ነበሩ። የእሳትም ፈሳሽ ከፊቱ ይፈልቅና ይወጣ ነበር ሺህ ጊዜ ሺህ ያገለግሉት ነበር፥ እልፍ አእላፋትም በፊቱ ቆመው ነበር ፍርድም ሆነ፥ መጻሕፍትም ተገለጡ።* ይላል። በዘመናት የሸመገለውም የሚለው ቃል וַעֲתִיק יוֹמִין ወአቲይቅ ዮሚን ከቀድሞ የነበረው፥ ለዕድሜው ጅማሬ የሌለው፥ ከዘላለም የነበረው ማለት ነው። ይህ የእግዚአብሔር መግለጫ ነው። 13-14 ላይ ደግሞ፥ *በሌሊት ራእይ አየሁ እነሆም፥ <u>የሰው ልጅ</u> የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ ወደ ፊቱም አቀረቡት። ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው፥ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው።* የሚል ቃል እናገኛለን። እዚህ የሰው ልጅ የሚመስል የተባለው በአዲስ ኪዳን ራሱን የሰው ልጅ እያለ የጠራው ኢየሱስ ነው። ለተራ ሰው ሁሉ የሚገዛለት የማያልፍ ዘላለማዊ ግዛትና የማይጠፋ መንግሥት ሊሰጠው አይቻልም። ዘላለማዊነት የመለኮት ባህርይ ነውና ዘላለማዊ መንግሥት ከኖረ የዚህ መንግሥት ባለቤት ዘላለማዊ ነው ማለት ነው። ኢየሱስ በአብ ቀኝ ከተቀመጠ፥ ዙፋኑን ከተጋራ፥ ዙፋኑ በሰማይ ከተዘረጋ፥ መንግሥቱ ዘላለማዊና ሁሉን የምትገዛ ከሆነች ሰው ብቻ አለመሆኑን ለመረዳት አይከብድም።

የቁርኣኑ ኢሳ በእውነት ጌታ ኢየሱስ ነው?

ከሙስሊሞች ጋር ስለ ክርስትናና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ስንወያይ ስለ ኢየሱስ ካነሣን ስለ አንድ ኢየሱስ የምናወራ ይመስለን ይሆናል። አንሳሳት፤ ፈጽሞም አይምሰለን። በቁርዓን የተጻፈው ኢሳ በወንጌል ከተጻፈው ኢየሱስ የተለየ ነው። በዶ/ር ሙሐመድ ዓሊ መጽሐፍ እና በሌሎችም ኢሳ ሳይሆን ኢየሱስ እየተባለ ስለተጠቀሰ ስለ ጌታችን ኢየሱስ እንደሚናገር አድርገን እንውሰድ እንጂ ኢሳና ኢየሱስ ከስም ጀምሮ አንድ አይደሉም። ቁርአን የአዲስ ኪዳን ነቢያት ከሚላቸው ሦስት ነቢያት የሁለቱን ስሞች እንደ ገመድ ገምዶ ነው የሚጠራቸው። ዮሐንስን ያህያ ይለዋል፤ ዐረብኛ ተናጋሪ ክርስቲያኖችና መጽሐፍ ቅዱሳቸውም ዩሐና ይሉታል። ወደ ኢየሱስ ስም ስንመጣም እንዲሁ ነው፤ እናየዋለን። የአዲስ ኪዳኑ ኢዬሱ ወይም ኢዬሱስ Ἰησοῦς የሚለው ስም ከዕብራይስጡ יְהוֹשֻׁעַ ዬሆሹዋዕ ከሚለው ቃል የተወሰደ ነው። ይህ ስም ኢያሱ ከሚለው የብሉይ ኪዳን ስም ጋር አንድ ሲሆን እግዚአብሔር አዳኝ ወይም የሚያድን አምላክ ማለት ነው። ስሙ ሥራውን መግለጡ ከመወለዱ በፊት ስለ ስሙ በተነገረው ትንቢት ግልጽ ሆኖአል፤ ማቴ. 1፥21። በብዙ ቋንቋዎች የኢየሱስ ስም የፊደል ወይም የድምጽ መራራቅ የሌለበት ተቀራራቢ ነው።

ኢሳና ኢየሱስ ከስም ጀምሮ አንድ አይደሉም ሲባልም በዐረብኛ አዲስ ኪዳን ወይም በዐረብኛ ተናጋሪ ክርስቲያኖች የኢየሱስ ስም ኢሳ ሳይሆን የሱ' ወይም የሱዋ በመሆኑ ነው። የአንድ ሰው ስም በተለያዩ ቋንቋዎች በተለያዩ አጠራሮች ሊጠራ ይችላልና ስም ሳይሆን ስሙ የወከለው አካል ላይ ነው ማተኮር ያለብን ሊባል ይችላል። ይህ እውነትነት አለው። ኢሳ የሚለው ስም የወከለው ኢየሱስ ግን የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2015

አይደለም። ስለዚህ ነው ኢሳና ኢየሱስ ከስም ጀምሮ አንድ አይደሉም ያልኩት።

ዛሬም ዐረብኛ ተናጋሪ ክርስቲያኖች ኢየሱስን ኢሳ አይሉትም። ከላይ እንዳልኩት ስም ወካይ ብቻ ነውና ቢሉም እንኳ የቁርኣኑን ኢሳ አይደለም። ኢየሱስ ክርስቶስ ወይም መሢሑ ኢየሱስ ሲሉም የሱዋ አል መሲህ ነው የሚሉት። ኢሳ የዐረብኛ ተናጋሪ ክርስቲያኖችም ሆነ የዐረብኛ መጽሐፍ ቅዱስ የኢየሱስ ስም አይደለም። ስሙ ብቻ ሳይሆን የቁርኣኑ ኢየሱስ በወንጌል እንደተጻፈው የእግዚአብሔር ልጅ ወይም እግዚአብሔር ወልድ አይደለም። በኢስላም ትውፊት ወደ 124 ሺህ ነቢያት አሉ ይባላል፤ በቁርኣን ወደ 25 ያህል በስም ተጽፈዋል (3ቱ ከአዲስ ኪዳን ናቸው፤ ዘካርያስ፥ መጥምቁ ዮሐንስ እና ኢሳ) ኢሳ ከማናቸውም የማይበልጥ ነቢይ ነው። ኢሳ ፍጡር ብቻ እንጂ በሥጋ የተገለጠው ፈጣሪ አምላክ አይደለም። የቁርኣኑ ኢሳ በቀጣዮቹ ገጾች እንደምናየው <u>አልተሰቀለም፤ አልሞተም፤ ከሙታንም አልተነሣም</u>። የቁርኣኑ ኢሳ ከሌሎቹ ከእርሱ በፊት ከተነሡት ነቢያት በምንም የማይበልጥ ነቢይ ብቻ እንጂ ሌላ ያልሆነ ሰው ነው፤ 5፥75፤ 4፥171። ስለዚህ ቁርኣን የሚናገረው ኢሳ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘው ኢየሱስ መስሎን አንታለል። አንድ ሰው፥ 'ዘላለምን አውቀዋለሁ፤ የቆዳው መልክ አረንጓዴ፥ ጠጉሩ ሰማያዊ፥ ቁመቱ 12 ሜትር ነው፤ ከአንገቱ በላይ ግመል ሆኖ ከታች የነብርና የዐዞ ቅይጥ ነው' ቢል እኔን የሚያውቁኝ ይህ ሰው ውሸቱን እንደተናገረ ለማስተዋል አይሳናቸውም።

ኢሳን የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ አሰኝቶ ኢየሱስ በተለይ በመስቀል ላይ አልተሰቀለም፥ አልሞተም፤ ስላልሞተ ከሞትም አልተነሣም የሚባለው ሞቱንና ትንሣኤውን ከስዕሉ ውጪ ለማድረግ ነው። የኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ ዋናውና ቁልፉ የክርስትና ትምህርት ነው። ክርስቶስ ከዘላለም የነበረ አምላክ ሳለ ሰው የሆነው፥ ሥጋ የለበሰው የናን ተውላጣዊ ሞት ለመሞትና ኃጢአታችንን ተሸክሞ ኃጢአት ያላወቀው እርሱ ስለ እና ኃጢአት ሆኖ እኛ የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ነው። ሰው አይደለም አምላክ የተደረገው፤ አምላክ ነው አምላክነቱን ሳይተው ሰው የሆነው። ተገለጠ ማለት በሥጋ ከመገለጡ በፊት በሥጋ ባልተገለጠበት ማንነቱ ነበረ ማለት ነው፤ ያም ፍጹም የሆነ መለኮትነቱ ነው።

ኢየሱስ በሥጋ <u>ተገለጠ</u> ወይም ሥጋ ሆነ ማለት ሙስሊሞች ክርስቲያኖችን የተሳሳቱ እንደሆነ የሚያስቡበት የእግዚአብሔርና ማርያም የሥጋ ተራክቦ ውጤት ሳይሆን መለኮትነቱ ሳይለወጥና ሳይቀነስ የሰውነትን ባሕርያት ተገናዘበ ወይም ገንዘብ አደረገ ማለት ነው። ይህ ትሥጉት የምንለው ስነ መለኮታዊ ቃል ነው። ዮሐንስ ቃል ሥጋ ሆነ የሚለው (ዮሐ. 1፥14)። ይህንን፥ 'በሥጋ ተገለጠ' የተባለውን ነገር የሆነ አንድ ብቻ ነው፤ እርሱም ክርስቶስ ነው። ሌላ ማንም ይህንን የሆነ የለም። ይህንን አሳብ ነው አዲስ ኪዳን 'አንድያ ልጅ' የሚለው።

አንድያ ልጅ (ሞኖጌኔስ)

አንድያ ልጅ የሚለው ቃል ለክርስቶስ መግለጫ ሲሆን መሳይ ወይም ቀዳሚና ተከታይ የሌለው መሆኑን የሚያሳይ ቃል ነው። በብሉይ ኪዳን ቋንቋ ለሰዎችም የተጠቀሰ ቃል ሆኖ ብቸኛ ልጅን ያመለክታል፤ ለምሳሌ፥ ኤር. 6፥26፤ አሞ. 8፥10፤ ዘካ. 12፥10። ቃሉ יָחִיד ያሺይድ አንድና ብቸኛ መሆንን እንዲሁም የተወደዱ መሆንንም ያሳያል። በመዝ. 22፥20 ብቻነት፥ በመዝ. 68፥6 ብቸኞች የሚለውም ቃል ከዚህ አንድ ነው። በዘፍ. 22፥2፥12፥16 ብቸኛ ሳይሆን ልዩ ወይም የተወደደ ልጅነትን ያሳያል። ይህንኑ ታሪክ የዕብራውያን ጸሐፊ በአዲስ ኪዳን አንድያ ልጅነት አድርጎ ያቀርበዋል፤ ዕብ. 11፥17።

መሳ. 11፥34 ብቸኛ ወይም አንድ ብቻ ልጅነትን ያሳያል። ይህ ቃል ብሉይ ኪዳን ወደ ጽርዕ በተመለሰበት የሰባ ሊቃናት ትርጉም ልክ በአዲስ ኪዳን ስለ ክርስቶስ የተጻፈው μονογενής (ሞኖጌኔስ) የሚል ቃል ነው። ይህ ቃል በአዲስ ኪዳንም ለሌሎችም ብቸኛ ልጆች ተጠቅሶአል፤ ለምሳሌ፥ ሉቃ. 7፥12፤ 8፥42፥ 9፥38። እነዚህ የሉቃስ ጥቅሶች ልጆቹ ብቸኞች ወይም ቀዳሚና ተከታይ የሌላቸው መሆናቸውን አያስረዳንም። በዕብ. 11፥17 ላይ ያለው ቃልም ሞኖጌኔስ ነው። ይህ ቃል የሚናገረው ስለ አብርሃም ሲሆን ልጁ ይስሐቅ ሞኖጌኔስ ተብሎአል። አብርሃም በኋላ ሌሎች ልጆች እንዳሉት የታወቀ ነው። እዚህ ላይ ንጽጽሩ ከእስማኤል ጋር ነው። ይስሐቅ አንድያ የሆነው በብቸኛነት ሳይሆን የተስፋው ቃል ልጅ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ሞኖጌኔስ ብቻነትን ሳይሆን ልዩነትን የያዘ ቃል ነው።

የኢየሱስን አንድያ ልጅነት (ሞኖጌኔስነት) በተመለከተ የተጠቀሱትን ጥቅሶች እንይ።

- *በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን (μονογενής) እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።* ዮሐ. 3፥16
- *በእርሱ በሚያምን ላይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ (μονογενής) ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።* ዮሐ. 3፥18
- *ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም (μονογενής) ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን።* ዮሐ. 1፥14
- *መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ሰንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ (μονογενής) እርሱ ተረከው።* ዮሐ. 1፥18
- *በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፥ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን (μονογενής) ወደ ዓለም ልኮታልና።* 1ዮሐ. 4፥9

ኢየሱስ አንድያ ልጅ የሆነው ወይም የተባለው ታሪክን የሚያጣርሱ እንደሚናገሩት በኒቅያ ጉባዔ አይደለም። የዮሐንስ ወንጌል ከኒቅያ ጉባዔ በፊት መኖሩን ካልካድን በቀር 'አንድያ ልጅ' የሚለውን ቃል ከኒቅያ ጋር ልናቆራኝ ከቶም አንችልም።

ለክርስቶስ ስለተነገረው ስለዚህ ቃል ስንመጣ ግን ይህ ቃል ክርስቶስ ብቸኛ፥ መሳይ የሌለው፥ በዓይነቱ ልዩ፥ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አመልካች ነው። ሞኖጌኔስ በሁለት ቃላት የተሠራ ጥምር ቃል ሲሆን እንደ አማርኛው አንድያ ልጅ ማለት ነው። ሞኖ አንድ ብቻ ማለት ሲሆን ጌኔስ የተወለደ፥ ልደት፥ ልደት ያገኘ ማለት ነው። ካልተንዛዛ በቀር ጌኔስ ልጅ ማለት ነው። በአማርኛ እየተነጋገርንና እየተጻፈም በእንግሊዝኛ በርካታ ትርጉሞች 'only begotten' ተብሎ ስለተተረጎመና beget ደግሞ በሥጋ መውለድ ስለሆነ፥ በሥጋ መውለድ ደግሞ ወሲባዊ ግንኙነትን ስለሚያስገድድ ኢየሱስ 'only begotten' ሲባል በወሲብ ፈቃድ የተወለደ ልጅ ነው ማለት ነው የሚል ስንካላ መከራከሪያ ይቀርባል። በቅርብ ከአንድ ሙስሊም ጋር ስንነጋገር beget የሚለውን ቃልና ትልቅ የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት ነበር ይዞ የመጣው። የቃሉን ምንነት ለመረዳት ወደ ሌላ ቋንቋ ከተሄደ ከአማርኛ ተዘልሎ ወደ እንግሊዝኛ ሳይሆን ወደ ምንጩ ነው መኬድ ያለበት። መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ በአማርኛ ወይም በእንግሊዝኛ አይደለም የተጻፈው።

ሌሎች የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው የተጠሩ አሉ፤ ለምሳሌ፥ እስራኤል እንደ አንድ ሕዝብ በዚህ ስም ተጠርተዋል፤ ዘጸ. 4፥23። እኛም የክርስቶስ ተከታዮች የእግዚአብሔር ልጆች ነን፤ ዮሐ. 1፥12፤ 11፥52፤ ሮሜ 8፥14-21፤ ገላ. 3፥26፤ ፊል. 2፥14-15፤ 1ዮሐ. 3፥2። ይህ ልጅነት እኛ በክርስቶስ በኩል ያገኘነው ልጅነት ሲሆን ብቸኛና መሳይ የለሽ ልጅነት አይደለም። የክርስቶስ μονογενής ወይም አንድያ ልጅ መሆን ብቸኛና መሳይ የለሽ ልጅነት ነው። የአብ አንድያ ልጅ ሲባል በሥላሴ ውስጥ ያለው ዘላለማዊ ስፍራና ባህርይ እንጂ ልጅ ከአባት በኋላ እንደሚገኝ

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ © 2015
የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ። 2ጢሞ. 2፥15
ባለቤትነቱን ሳይውስዱ ማባዛትም ማደልም ይፈቀዳል።

አብ ቀዳሚ ወልድ ተቀዳሚ ማለት አይደለም። አብ አስቀድሞ የነበረ፥ ወልድ ቀድሞ ሳይኖር ቆይቶ ኋላ መኖር የጀመረ ማለት አይደለም።

ወልድ ወልድ የተሰኘው ከድንግል ተወልዶ ሥጋ በመልበሱ ምክንያት፥ ጽድቅን ሁሉ ለመፈጸም በመፍቀዱ፥ ራሱን ዝቅ በማድረጉ፥ ራሱን ለምትካዊ ሞት አሳልፎ በመስጠቱ፥ በመታዘዙ ነው እንጂ ኋላ በመገኘቱ ከቶም አይደለም። በጎልውና ወልድ ከአብ፥ ወይም መንፈስ ቅዱስ ከወልድ አይተናነሱም። አይቀዳደሙም። ኢየሱስ በሥጋ የተገለጠ አምላክ በመሆኑ ከመወለዱ በፊትም ነበረ። የት? ዓለማትን ሲፈጥር በእግዚአብሔር ዘንድ ወይም ከአብ ጋር ነበረ፤ ዮሐ 1፥1-2፤ 17፥5።

ጸሎት ከጸለየ ምኑን አምላክ ሆነ?

ጸሎት በሚል ንዑስ ርእስ ስር የኢየሱስ መጸለይ አምላክ ያለመሆኑ ምልክት ሆኖ ቀርቧል።

ኢየሱስ በፊቱ ወድቆ የጸለየ ወይም የሰገደ መሆኑ ተገልጿል (ማቴ.26፥39)። ይህም ማለት ኢየሱስ በማንባራቸው ተደፍተው መስገዳቸውን ያሳያል። ለማነው ተደፍተው የሰገዱት? በዚህ ሁኔታ መስገዳቸው ራሱ ለእግዚአብሔር ራሱን ዝቅ አድርጉና አዋርዶ የሚያስገዛ ሰው መሆናቸውን ያረጋግጣል። ለእግዚአብሔር የሚጸልይና በፊቱ ተደፍቶ እግዚአብሔርን የሚያነጋግል ሰብዓዊ ፍጡር ተመልሶ በራሱ እግዚአብሔር ሊሆን ፈጽም አይችልም። ቤተክርስቲያን ግን ኢየሱስ ከቶውንም ብለው ወይም ፈልጉት የማያውቁ ቢሆንም ቅሉ ነቢዩን አምላክ የማድረግ ግፊቷን ቀጥላበታለች። በዚህም ቤተክ

ባለማወቅ ወይም ሆን ብሎ ለማሳሳት ተብሎ ግን ርእሱ ጸሎት ሆኖ ሳለ ጉዳዩ መስገድ ተብሎ ቀርቦአል። በወንጌላት ውስጥ <u>ኢየሱስ ሲሰገድለት እንጂ የአምልኮ ስግደትን ሲሰግድ አናይም።</u> መጸለይና መስገድ ፈጽሞ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ኢየሱስ እንደ ሰብእናው ወደ አብ ሲጸልይ ይታያል፤ ሲያመልክ ግን አይታይም። መስገድ ከአምልኮ ጋር የተያያዘ የሰውነት አቋም ሲሆን በጸሎት ጊዜ ምንም የሰውነት አቋም ሊሆን ይችላል። ቆሞ፥ ተቀምጦ፥ አጎንብሶ፥ ተንበርክኮ፥ በግንባር ተደፍቶ፥ ዓይን ከፍቶ ወይም ዘግቶ፥ እጅ አጥፎ ወይ ዘርግቶ መጸለይ ይቻላል። በክርስቲያን ጸሎት ዋናው ቁም ነገር የአካል አቋም ሳይሆን የልብ በእግዚአብሔር ፊት መውደቅ ነው። በማር. 14 ኢየሱስ በምድር ወድቆ መጸለዩ ተጽፎአል፤ ታዲያ ይህ ሰው በመሆኑ ያቀረበው ልመና እንጂ ወደ አምላክ የቀረበ ስግደት አይደለም። ኢየሱስ ሰው እንደ መሆኑ መጠን ሰው የሚያደርጋቸውን ነገሮች ሲያደርግ የአምልኮ ስግደትን ግን አላደረገም፤ ይህ የአምላክነቱ ምስክር ነው።

ኢየሱስ ፍጹም ሰው በመሆኑ ግን <u>ከኃጢአት በቀር</u> ሰዎች የሆኑትን ሁሉ ሲሆን፥ ያደረጉትን ሲያደርግ፥ የሆነባቸው ሲሆንበት ይታያል። ሲፈተን፥ ሲበላ፥ ሲጠጣ፥ ሲራብ፥ ሲጠማ፥ ሲደክም፥ ሲተኛ፥ ሲቆጣ፥ ሐሴት ሲያደርግ፥ ሲፈራ፥ ይታያል። ሲጸልይም ይታያል። በዚህ በዶ/ር ሙሐመድ መጽሐፍ እንደሚነበበው ሁሉ ሙስሊሞች፥ አምላክ እንዴት ይራባል? እንዴት ይደክማል? እንዴት ይተኛና እንቅልፍ ይወስደዋል? እንዴት ይጸዳዳል? እያሉ የፌዝ ጥያቄ መደርደርን እየለመዱ መጥተዋል።

በመጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠው እኛ ክርስቲያኖች የምናመልከው አምላክ ሥላሴ መሆኑን ከዚህ በፊት የተመለከትን ሲሆን ኢየሱስ ሰው ባይሆንም ኖር እንኳን ከአብ ጋር በዘላለማዊ አንድነት ግንኙነት አለውና ጸሎትም ባይሆን ኅብረት ማድረግ ይችላል። ሰው ስለሆነ ደግሞ ጸለየ። የሥላሴን አስተምህሮ ስንቀበል የወልድና የአብ ግንኙነት ከባድ አይሆንም። የክርስትና ስነ መለኮት ወይም ነገረ እግዚአብሔር ሥላሴያዊ ነው። ወልድ ወደ አብ ቢጸልይ፥ ወይም አብ ለወልድ ቢመልስ፥ ወይም መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን ቢመስክር ለሥላሴያዊ ስነ መለኮት የሚከብድ እውነት አይደለም። የሥላሴን አስተምህሮ ለማይቀበልና እግዚአብሔር አንድ አካል፥ አንድ ባህርይ ብቻ ብሎ ለሚቀበል እንደ ኢስላም ላለ ሃይማኖት ኢየሱስ አምላክ ሆኖ ቢጸልይ እውነትም መልስ የሌለው ነገር ነው። ለምሳሌ፥ የቁራኣኑ አላህ ቢጸልይ እንደማለት ነው። ወይም እግዚአብሔር አብ ቢጸልይ እንደማለት ነው። ይህ መልስ የሌለው ጉዳይ ይሆናል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ወደማንም ሊጸልይ አይችልም፤ አይገባውምም። ኢየሱስ ግን አምላክ ሳለ ሰው የሆነ ነውና እንደ ሰው ወደ አብ ጸለየ። ይህ ትምህርት ሥላሴን ለምናምን የሚከብድ አይደለም።

ይሁን እንጂ ግን፥ ይህ ደግሞ አላህ ሲጸልይ በቁርኣን ውስጥ ተጽፎ ይገኛልና እንየው። ለምሳሌ፥ ሱራ 33፥56 እንዲህ ይላል፥

አላህና መላእክቱ በነቢዩ ላይ አክብሮት እዝነትን ያወርዳሉ፤ እላንተ ያመናችሁ ሆይ በርሱ ላይ የአክብሮት እዝነትን አውርዱ፤ የማክበርንም ሰላምታ ሰላም በሉ።

በዚህ አንቀጽ እዝነት የተባለው ቃል ጸሎት ነው። ምንጩ ሰላት የሚለው ቃል ነው። አላህና መላእክቱ በነቢዩ ላይ እዝነትን ያወርዳሉ፤ ሰላትን (ጸሎትን) ያወርዳሉ ነው። Noble Quran ሲተረጉመው፥

56. Allah sends His *Salat* (Graces, Honours, Blessings, Mercy, etc.) on the Prophet (Muhammad) and also His angels too (ask Allah to bless and forgive him). O you who believe! Send your *Salat* on (ask Allah to bless) him (Muhammad), and (you should) greet (salute) him with the Islamic way of greeting (salutation i.e. *As-Salamu 'Alaikum).*

ይላል። ሰላትን በቅንፍ ጸጋ፥ ክብር፥ በረከት፥ ምሕረት ወዘተ ብሎ ሲተረጉም ጸሎት ግን አላለም። ዋናው የሰላት ወይም ሶላት ትርጉም ግን ክብር፥ በረከት ወዘተ ሳይሆን ጸሎት ነው። ለነዚያ ክብር በረከት ወዘተ፥ ለተባሉት ቃላት ሌላ ትርጉሞች አሏቸው። ብዙ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች በረከት ብለው ሲተረጉሙት ለበረከት ራሱን የቻለ ቃል ሳይጠፋለት ነው። ጥያቄው አላህ ከጸለየ ወደማን ነው የሚጸልየው? የሚል ሲሆን መልስ የለውም። እግዚአብሔርን እንደ ሥላሴ ለምንቀበል የኢየሱስ መጸለይ ለመረዳት አይከብድም።

ወደ ኢየሱስ ስንመለስ <u>የኢየሱስ መጸለይ አምላክ ያለመሆኑ ሳይሆን በትክክል ፍጹም ሰው የመሆኑ ገላጭ ነው።</u> ኢየሱስ ሰው ሲሆን የሙከራ ሰውነትን ሳይሆን ሰው የሆነው እውነተኛና ፍጹም ሰውነትን ነው። እንደ ሰው ማንም ሊሆን የሚችለውን ሊሆን በፈቃዱ ተገደደ። ማንም አላስገደደውም። ይህን ያደረገው ደግሞ ለዓላማ ነው። ዓላማውም የደኅንነት ሥራ ነው። ይህ ወደሚቀጥለው ነጥብ ይመራናል።

እንግዲህ አምላክ ከሆነ ለምን ጸለየ የሚለው ጥያቄ የሥላሴን ማንነት በመረዳትና በመቀበል የሚመለስ ነው። ኢየሱስ ወደ አብ የጸለየው ሥጋ የለበሰ ሰው ስለሆነ ነው።

ወንጌሎች ብዙ ቦታ ላይ ኢየሱስን እንደ ነቢይ ያቀርባሉ። ለምሳሌ ያህል (ሉቃ. 7፥16)። የናዝሬቱ ነቢይ (ማቴ.21፥11)። ቤተክርስቲያን ግን ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳንንም እንዲሁ በመጻረር በምታራምደው በእንድ አምላክ ያለማመንና በሦስትዮሽ አማልክት ማመንን የመሥረተ ድርጊቷ ኢየሱስን አምላክ አድርጋለች። ስለዚህም ክርስትና መለኮታዊ ሳይሆን ሰው ሠራሽ ሃይማኖት ነው። ኢየሱስ ራሳቸውን አምላክ ነኝ ወይም የአምላክ ልጅ ነኝ ብለው ጠርተው ጭራሽ አያውቁም። ብዙውን ጊዜ ራሳቸውን የሰው ልጅ እያሉ ይጠቅሱ ነበር (ማቴ.17፥22፤ ማቴ.18፥11)።

ብዙ ጊዜ ከብዙ ሙስሊሞች እንደ ሰልፍ እየተከታተለ የሚመጣ አንድ ጥያቄ ኢየሱስ እርሱ፥ 'እኔ አምላክ ነኝ፤ አምልኩኝ ብሎአል ወይ?' የሚል ነው። ይህንን ጥያቄ ከዚህ በፊት (ባለፈው ዕዝራ የጥያቄና መልስ ክፍል) እንዳልኩት፥ ኢየሱስ፥ 'እኔ ነቢይ ብቻ ነኝ፤ እኔ የአላህ ቃል ነኝ፤ እኔ የአላህ መልክተኛ እንጂ አምላክ አይደለሁም' ብሎ ስላልተናገረ አምላክ ነው ማለት ነው በሚል አጭር አጸፋ መመለስም ይቻላል። እንደ ጥያቄው አቀራረብ ጥያቄውን በአጸፋ ጥያቄ መመለስ ካስፈለገ ማለቴ ነው። ኢየሱስ፥ 'እኔ አምላክ ነኝ' ብሎ በቀጥታ መናገሩ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጻፈም። እንዲህ ቢል ኖሮ ይህ አቀራረብ አይሁድ ኢየሱስን

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ
© 2015

በተሳሳተ መልኩ እንዲያዩትና በማንነቱ እንዳይቀበሉት የሚያደርጋቸው ነው። ኢየሱስ፥ 'እኔ አምላክ ነኝ፤ አምልኩኝ' ብሎ እያስተማረ ቢመጣ በአይሁድ መረዳት ኢየሱስን እንደ አብ መውሰድ ሊሆን ነው። ኢየሱስ ደግሞ ወልድ እንጂ አብ አይደለም። ስለ እርሱም ሆነ ስለ ሥላሴያዊው ስነ መለኮት ትክክለኛው መረዳት እንዲኖራቸው እርሱ ወልድ መሆኑን እና አብም አብ መሆኑን ነው ደጋግሞ ያስተማረው። በግልጽና በዝርዝር ኢየሱስ ይህንን አስተምሮአል። የገባቸው ሲሰግዱለትም ሆነ ስለ እርሱ እውነቱን ሲመሰክሩ አላገዳቸውም። አይደለሁም ብሎ አልተከላከለም።

የኢየሱስ አምላክነት በወንጌላት ውስጥ በገሃድ ይታያል። በዮሐ. 8፥59 እና 10፥33 አይሁድ ኢየሱስን ሊወግሩት ድንጋይ ማንሣታቸው ተጽፎአል። ይህን ያደረጉት ኢየሱስ ራሱን ከአብ ጋር በማስተካከሉ ነው። ለአይሁድ መውገር የሞት ቅጣትን መቅጣት ነው። (በሐዋ. 8 እስጢፋኖስን እንደወገሩት። እስጢፋኖስን የወገሩት ኢየሱስን በመስበኩ ብቻ ሳይሆን ኢየሱስን በአብ ቀኝ ቆሞ አየሁ በማለቱ ነው። እራሱን ከአብ ጋር ያስተካከለውንማ እንዴት አይወግሩት! ይህ በቀኝ መቆም ኢየሱስንና አብን ማስተካከል ወይም ኢየሱስን እግዚአብሔር እንደሆነ መግለጥ ነው።) አይሁድ ኢየሱስን ለመውገር ድንጋይ ያነሡት ኢየሱስ፥ *አብርሃም ከመወለዱ በፊት እኔ፣ እኔ ነኝ* ስላላቸው ነበር (ቁጥር 58)። ይህ ዘላለማዊነቱን መናገሩ ሲሆን ዘላለማዊነት ደግሞ የመለኮት ብቻ ባህርይ ነው። በተለይ በዮሐ 10፥33 ለምን ሊወግሩት እንደሚፈልጉ ሲጠይቃቸው የመለሱት መልስ የማንነቱ ገላጭ ነው። መልሳቸው፥ *አይሁድም፥ ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ* ብለው መለሱለት። ይላል። ቀጥሎ ባሉት ጥቅሶች ኢየሱስ የመለሰላቸው ይህንን እውነት የሚያጠነክር እንጂ የሚያስተባብል አይደለም። ለአይሁድ ኢየሱስ ያለውና የተናገረው ጉበቶአቸዋል። ሊወግሩት የፈለጉትና ኃላም እንዲሰቀል ያስደረጉት ስለዚህ ነው።

ኢየሱስ በእርግጥ፥ በቀጥታ አምላክ ስለመሆኑ የተናገረውን አንድ ክፍል እንይ። ይህንን ከቁርአን አሳብ ጋር ለማነጻጸር ከራሱ ከቁርአን እንጀምር። በ57 (በሱረቱ አል-ሐዲድ)፥3 ላይ፥

እርሱ ፊትም ያለ ኋላም ቀሪ፤ ግልጽም ስውርም ነው፤ እርሱም ነገሩን ሁሉ አዋቂ ነው።

ይላል። ይህ ማለት አላህ ፊተኛም ኋላኛም ነው ማለት ነው። ኋላ ቀሪና ኋለኛ ተመሳሳይ ቃላት ናቸው። ከአምላክ በቀር ሌላ ማንም ፊተኛና ኋለኛ ሊሆን የሚችል የለም። ሰው ይህንን ካለ ያ ሰው ወይ አምላክ ነው፤ ወይም ቀጣፊና ዕብድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ያህዌህ ፊተኛና ኋለኛነት እንዲሁ ተመሳሳይ ነገር ያስተምራል። በኢሳ. 44፥6፥ *የእስራኤል ንጉሥ እግዚአብሔር፥ የሚቤዠውም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔ ፊተኛ ነኝ እኔም ኋለኛ ነኝ፥ ከእኔ ሌላም አምላክ የለም።* በ48፥2 ደግሞ፥ *ያዕቆብ ሆይ፥ የጠራሁህም እስራኤል ሆይ፥ ስማኝ እኔ ነኝ እኔ ፊተኛው ነኝ እኔም ኋለኛው ነኝ።* ይላል። ከእግዚአብሔር በቀር ይህንን መሆን የሚችል ማንም የለም። ፊተኛ ማለት ከፊቱ የነበረ ማንም የለም። ከእርሱ በኋላም የሚመጣ ምንም የለም። በእርግጥ ይህ የመለኮት ባህርይ ነው።

ይህ የሚደንቅ ቃል በአዲስ ኪዳንም ተጽፎ እናገኛለን። በራእ. 1፥17-18 እንዲህ የሚል ቃል አለ። *ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ። ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ፦ አትፍራ፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፥ ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ።* ይህ ቃል ኢየሱስ የተናገረው ቃል ነው። ኢየሱስ እርሱ ፊተኛውና ኋለኛው በ22፥13ም ይህንኑ ቃል ይደግመዋል፤ እንዲህ ሲል፥ *አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።* በግልጽ ኢየሱስ ይህንን ካለ እርሱ በብሉይ ኪዳን፥ እኔ ፊተኛና ኋለኛው ነኝ ካለው ጋር አንድ ነው ማለት ነው። ፊተኛና ኋለኛነት የመለኮት ብቻ ባህርይ ከሆነ ኢየሱስ መለኮት ነው ማለት ነው። ይህንን የተናገረው ደግሞ ሰው ወይም መልአክ ወይም ሌላ ፍጡር ሳይሆን ኢየሱስ ራሱ ነው። ኢየሱስ ስለ አምላክነቱ አልተናገረም ማለት የስንፍና ቃል ነው።

ቤተ ክርስቲያን ብሉይ ኪዳንን እና አዲስ ኪዳንን በመጻረር የሦስትዮሽ አማልክት ማምለክን በመምረጥ ኢየሱስን አምላክ አላደረጉችም። ፊተኛውና ኋለኛው እኔ ነኝ ያለውን ፊተኛና ኋለኛ የሆነውን አስተውላ አውቃ አመለከች እንጂ ያላለውን ነህ ብላ አምላክነት አልሾመችም። ደግሞም ዶ/ር ሙሐመድ፣ "ኢየሱስ ራሳቸውን አምላክ ወይም የአምላክ ልጅ ነኝ ብለው ጠርተው ጭራሽ አያውቁም" ሲል አለማወቅ ሳይሆን ማሳሳትና ክህደት ነው።

አምላክ ስለሚለው አሳብ ከላይ ተመልክተናል። ስለ ልጅነቱ ደግሞ ኢየሱስ እግዚአብሔርን አብ፥ አባት፥ አባቴ እያለ መጥራቱ ምስክር ነው። ከላይ ስለ ጸሎት ማውሳታችን እንዳለ ሆኖ ሲጸልይ ምን እያለ ይጸልይ እንደነበር ብናጤን ይህንን እውነት በትክክል መርዳት እንችላለን። ለምሳሌ፥ *አባ አባት ሆይ፥ ሁሉ ይቻልሃል፤ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን አንተ የምትወደው እንጂ እኔ የምወደው አይሁን አለ።* ማር. 14፥36። ደግሞም በብዙ ቦታዎች ሲጸልይ፥ ለምሳሌ፥ ሉቃ. 22፥41፤ 23፥34፥ 46፤ ዮሐ. 11፥41፤ 12፥27-28፤ 17 በሙሉ፤ ወዘተ ጸሎቱ እግዚአብሔርን አባት በማለት ነው። ስለ እግዚአብሔር ሲገልጥ፥ 'አባቴ' እያለ ነው። ዮሐ. 14 እና 15። አንዴ ኢየሱስን፥ *እንግዲህ፥ አባትህ ወዴት ነው? አሉት።* ኢየሱስ መልሶ፦ *እኔንም ወይም አባቴንም አታውቁምን፤ እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር አላቸው።* ዮሐ. 8፥19። ደግሞም ዮሐ. 5፥18 *እንግዲህ ሰንበትን ስለ ሻረ ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካከሎ፥ እግዚአብሔር አባቴ ነው ሰላለ፥ ስለዚህ* አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር። ይላል። ልጅ አይደለም ወይም ነኝ አላለም ማለት እንግዲህ ቅጥፈት እንጂ ሌላ አይደለም። ብሏልና።

አዳም ባጠፋ ኢየሱስ ተጠፋ

ዶ/ር ሙሐመድ የክርስቶስን የቤዛነት ሥራ ክርስቲያናዊ ትረካ ብሎ ይጠራዋል።

> ክርስትና አዳም የተከለከለውን ዛፍ በመብላቱ ኃጢአት ፈጽሟል፣ ስለዚህም አዳም እስከ አጥንቶቹ መቅኒ ድረስ ኃጢአተኛ ነው፣ የሰው ልጆች በሙሉም ከአባታቸው ከአዳም በውርስ በተላለፈባቸው ኃጢአት ምክንያት ኃጢአተኞች ናቸው ይላል። በክርስትና ትምህርት መሠረት እግዚአብሔር አንድያ ልጁ ኢየሱስን ወደ መስቀያው የላከው የሰውን ልጅ ከዚህ በውርስ ከተቀበለው ኃጢአት ለማዳን ነው።

አዳም በመተላለፉ ምክንያት ኃጢአተኛ መሆኑን በዚያም ኃጢአት ሳቢያ ሌሎችም መጎዳታቸውን በትክክል መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል። ለነገሩ ቁርአንም ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች መሆናቸውን ያስተምራል፤ ለምሳሌ፥ 35፥45

አላህም ሰዎችን በሰሩት ኀጢያት ቢይዝ ኖሮ በወለሏ (በምድር) ላይ ምንም ተንቀሳቃሽ ባልተወ ነበር፤ ግን እተወሰነ ጊዜ ድረስ ያቆያቸዋልና፤ ጊዜያቸውም በመጣ ወቅት (በኀጢያታቸው ይቀጣቸዋል)፤ አላህ በባሮቹ ሁኔታ ተመልካች ነውና።

ይላል። ምንም ካልተተወ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል ማለት ነው። ማንም ሕጻን ሆነ አዋቂ ተንቀሳቃሽ የተባለ ሁሉ የሚተርፍ የለም። አዳማዊነት ወደ ተከታዩ ትውልድ የማያልፍ ኖሮ ቢሆን አዳምና ሔዋን የተሰጣቸው ዕድል ለቃየንና አቤልም፥ ከዚያ በኋላ ላለው ትውልድም ሁሉ መሰጠት በተገባው ነበር። እውነትም እንደ ዶ/ር ሙሐመድ አገላለጥ አዳም እስከ አጥንቶቹ መቅኒ ድረስ ኃጢአተኛ ከሆነ ከኃጢአተኛ መቅኒ ቅዱስ ዘር ሊወጣ አይችልም። ምንጩ ከተመረዘ ጅረቱ ንጹሕ ሊሆን አይችልም። ይህንን ሁኔታ ነው ውድቀት ብለን የምንጠራው።

ሮሜ. 5፥14 *ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ፤ አዳም ይመጣ*

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ © 2015

ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና ይላል። ይህ የወደቀ ሰው እንደምን ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚታረቅ እግዚአብሔር ገና ከመጀመሪያም መንገድን አዘጋጅቶ፥ ተስፋን ሰጥቶ ነበር። እነ አዳም ገና ከመውደቁ ጀምሮ ከሴቲቱ የሚወጣው ዘር የሰይጣንን ራስ የሚቀጠቅጠው መሆኑ ተገለጠ። ኢየሱስ ከወንድ ሳይሆን ከሴቲቱ ዘር መሆኑ በግልጽ መጻፉ ይህንን የሚያበስር ነው። ገላ. 4፥4 *ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ* እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ፤ ይላል። ይህ ከሴት የተወለደው ኋለኛው አዳም የተባለውም ነው። *እንዲሁ ደግሞ፥ ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፎአልና፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ።* 1ቆሮ. 15፥45።

ለነዶ/ር ሙሐመድ ከሴቲቱ ዘር የመጣው እርሱ የተሰፋው ዘር መሆኑን ቁራኣን ራሱም ኢየሱስን ኢብን መርየም በማለት መጥራቱ ትንሽ ፍንጭ ሊሰጣቸው በተገባ ነበር። ይህ አጠራር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባይሆንም።

> በሌላ አገላለጽ አዳም እገዳውን ጥሰው ከገቱ በሱና ኢየሱስ ከብዙ ሺ ዓመታት በኋላ በአዳም ኃጢአት ተሰቀሉ። አዳም ኃጢአት ፈጸሙ ፣ ኢየሱስ አዳም በፈጸሙት ወንጀል ተቀጡ። ይህ ነው እንግዲህ ክርስቲያናዊ ትረካ።

የክርስቶስ ሞት ክርስቲያናዊ ትረካ ሳይሆን የትንቢት ፍጻሜና በእርግጥም ተውላጣዊ ሞት ነው። *ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደ ሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዲጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ይገባዋል።* ዮሐ. 3፥14-15። የሰው ልጅ ሊሰቀል የተገባው በእርሱ የሚያምን በደሙ ስርየት የዘላለምን ሕይወት እንዲያገኝ ነው። የሰው ልጅ ሳይሰቀል ሰዎች የዘላለም ሕይወትን የሚቀዳጁ ኖረው ቢሆን የኢየሱስ መሞት ባላስፈለገም ነበር። ግን ለኃጢአት ስርየት የደም መፍሰስ ግድ ነበረና መሞት ኖረበት። ይህ ክርስቲያናዊ ትረካ ሳይሆን የጌታ ኢየሱስ የራሱ ቃል ነው። ይህን ቃል እርሱ ራሱ ነው ለኒቆዲሞስ የተናገረው።

ተአምር ማድረግ የማይችል አናጺ?

> ወንጌሎች ውስጥ ብዙ ጊዜ ራሳቸውን የሰው ልጅ ብለው የገለጹ ቢሆንም ክርስትና ግን ኢየሱስን እምላክ ቁጥር 2 ያደረጋቸዋል። የፈጸሟቸው ተአምርችም በገዛ ራሳቸው ኃይልና ችሎታ ያልተፈጸሙ መሆናቸውንም ኢየሱስ አበክረው ተናግረዋል። በገዛ ራሳቸው ምንም መሥራት የማይችሉ መሆናቸውንም ገልጸዋል (ዮሐ. 5፥30) ። ቤተክርስቲያን ግን የኢየሱስን ፍላጐት በመ

አምላክ ቁጥር 2! ስም ጠፍቶ ዶ/ር ሙሐመድ አምላክን በቁጥር ሲሰይምና ስያሜውን የክርስቲያኖች ሲያደርግ ሙያ መስሎታል። ዐውድን ጥሎ ጥቅስን አንጠልጥሎ ስሕተት ለመጠቆም መሞከር የራስን ስሕተት የሚገልጥ መሆኑ እውነት ነው። ከላይ በተጠቀሰው ዮሐ. 5፥30 ኢየሱስ *እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤* ሲል ከአብ ጋር ስላለው ቁርኝት እየተናገረ መሆኑን ዐውዱ ይገልጠዋል። ሰው በመሆኑ፥ በሥጋ በመወሰኑ፥ ሥልጣኑን ያለገደብ አልተጠቀመም። ወደ ላይ ከፍ፥ ወደ ታችም ዝቅ ብለን ምንባቡን ስንመለከት ግን ይህንን ዶ/ር ሙሐመድ ያለውን እንዳላለ ግልጽ ነው። ኢየሱስ በራሱ ተአምራትን እንደሚያደርግ በንጽጽር የተናገረውን ከዚያው ምዕራፍ እንኳ ብናይ በቁ. 21 ላይ፥ *አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው፥ እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል* ይላል። ሙታንን ከማስነሣትና ሕይወትን ከመስጠት በላይ ተአምር ይኖር ይሆን? ይህ፥ 'ኢየሱስ በገዛ ራሳቸው ምንም መሥራት የማይችሉ መሆናቸውን ገልጸዋል' የሚባል ነው? አይደለም። ያደረጋቸውን ተአምራት ሁሉ ስንመለከትም ኢየሱስ ራሱ ያደረጋቸው ናቸው።

ዶ/ር ሙሐመድ አናጺ ወይስ አምላክ በሚል ንዑስ ርእስ ስር የተረከው ሌላ ነገር ኢየሱስ አናጺ መሆኑን የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችና ቤተ ክርስቲያን መደበቋን ነው። ይህ ጉዳይ የተደበቀውም አናጺ ብሎ አምላክ ማለት የሚያሳፍር ስለሆነ ነው። ይህ ድንቅ ነው! ዶ/ር ሙሐመድ የኢየሱስን አናጺነት አብሮት ጣውላ እየጠረበ የከረመ ያህል አብራርቶ ሲጽፍ ይህን ያገኘበትን ምንጭ ግን አልጠቀሰም።

> ወንጌሎች ግን ኢየሱስ በዚህ ዘመን (በእሥራ ስምንቱ ዓመት) ስላሳለፉት ሕይወት ምንም ነገር አይተነፍሱም። ስለ ሕይወታቸውና ስለ ልደታቸው ማውራት የሚጀምሩት እስከ እሥራ ሁለተኛ ዓመታቸው ድረስ ብቻ ነው። ከዚያ
>
> አይደለምን? ምናልባት ኢቨንጀሊስቶቹ እነኛን የኢየሱስ የሕይወት ዓመታት አልዘለሉ ይሆናል፤ የጻፉት ነገር ተፈላጊ ያልሆኑ የጽሑፉን ክፍሎች ሆን ብሎ ለመሰረዝና ለማስወጣት ለተካሄደው የማጣመም የማዛባትና የመበረዝ እደጋ ተጋልጦም ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ የወንጌል አሪጂናል ቅጂዎች ያን
>
> ለማንኛውም ግን ያ ዘመን፣ እምላካችን ወይም የእግዚአብሔር ልጅ የሚሏቸውን ኢየሱስን አናጺ አድርገው እንዳያሳዩ ስላልፈለጉ ወይ ተዘሏል፤ አለበለዚያም ተሰርዟል። ከኢየሱስ የሕይወት ዘመን ውስጥ እኒያ ዓመታት ተሰማሚ ሆነው አልተገኙም ማለት ነው። አናጺው ኢየሱስ ከእግዚአብሔሩ ወይም ከእግ

አዲስ ኪዳን ኢየሱስ ጸራቢ መሆኑን አልደበቀም፤ የሚደብቅበት ምክንያትም የለም። ጸራቢነትም ሆነ ማናቸውም ሙያ አሳፋሪነት ከቶም የለበትም።

ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስን ከጸራቢነት ወደ አምላክነት ከፍ አላደረገችም። ለነገሩ ወደ አምላክነት ከፍ ሊደረግ የሚችል ምንም ሙያ የለም። ጸራቢም፥ ነጋዴም፥ ንጉሥም አምላክ መሆን አይችልም። አምላክ ግን ከፈለገ ሰው ሆኖ እረኛ ወይም ጸራቢም ቢሆን ይቻለዋል። መሆን አያቅተውማ!

ቤተ ክርስቲያንና የወንጌላት ጸሐፊዎች ታሪክን ሲጽፉ እንዲጽፉ የሚመራቸው መንፈስ ቅዱስ ነውና አስፈላጊውንና አላስፈላጊውን ያውቁታል። አንድ የሕይወት ክፍል ቢዘለል ያ ክፍል የሚጨምረው ወይም የሚቀንሰው ጉልህ ነገር ስለሌለ ነው። ዶ/ር ሙሐመድ ያን ያህል ዘርዝሮና የወንጌል ጸሐፊዎች ምስጢር አድርገው ደበቁት ብሎ የጻፈው ነገር ቢኖር የኢየሱስ አናጺነት ነው። በቃ ሌላ የለም፤ ይኸው ነው። ይህ ደግሞ በወንጌል ውስጥ ያልተጠቀሰ ነገር አይደለም። ማር. 6፥3 *ይህስ ጸራቢው የማርያም ልጅ የያቆብም የዮሳም የይሁዳም የስምዖንም ወንድም አይደለምን? እኅቶቹስ በዚህ በእኛ ዘንድ አይደሉምን?* አሉ፤ *ይሰናከሉበትም ነበር* ይላል። ዶ/ር ሙሐመድ ራሱም የኢየሱስን ጸራቢነት ከዚህ ሳያገኘው አይቀርም። ሌሎች ባለታሪኮችም ጽፈውታል። ምኑን ድብቅ ሆነ ታዲያ? ኢየሱስ የሠራቸው ወንበሮችና ጠረጴዛዎችና መስኮቶች ለምን አልተጻፉም ማለቱ ሳይሆን አይቀርም። ይህ ደግሞ አስፈላጊ አልነበረምና አልተጻፈም። እነዚህ ዘመናት ቢያስፈልጉ ኖሮ በተጻፉልን ነበር።

ስለነዚህ የኢየሱስ ያልተጻፉ ዓመታት የተደረሱ በርካታ ድርሳኖች አሉ። እነዚህ ድርሳናት፥ ዶ/ር ሙሐመድ እንዳለው፥ እነዚያ ከ13-29 ዓመቱ ድረስ ያሉት ዘመናት የታሸጉ የመሰላቸው ሰዎች የጻፏቸው ናቸው። አሕመዲያ ሙስሊሞች ይህንን በተመለከተ ከተጻፉት ታሪኮች አንዱን እንዳለ በመውሰድ ኢየሱስ በነዚያ ያልታወቁ ዓመታት ወደ ሩቅ ምሥራቅ ሄዶ ኖሮ እንደተመለሰ፥ ኋላም በመስቀል ላይ እንዳልሞተ፥ አገግሞ እንደዳነና ከእናቱ ከማርያም፥ ከሚስቱ ከመግደላዊት ማርያምና ከደቀ መዝሙሩ ቶማስ ጋር ወደ ሕንድ ሄዶ እንደኖረ፥ እዚያ ሞቶ ካሽሚር የሚባል ቦታ እንደተቀበረ መሪያቸው ጽፎላቸው ይህን ይቀበላሉ። ይህን የመሰሉ ጥቂት ያልሆኑ ተረቶች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ነገር መከበር እንደሚገባው ዝም ባለባቸው ቦታዎችም ዝምታው ሊከበር ይገባዋል እንጂ ዝምታውን በመጎትጎት ያልተናገረውን ማናገር ወይም በራሳችን ምናብ በፈጠርናቸው ተረቶች ጠቅጥቀን ልንሞላ የተገባን አይደለንም።

ይቀጥላል።

ዘላለም መንግሥቱ © 2015 (፪ሺህ፭) ዕዝራ ስነ ጽሑፍ አገልግሎት

ዕዝራ ስነ ጽሑፍ © 2015